# ሒሳብ

## የተማሪ መጽሐፍ
## 3ኛ ክፍል

አዘጋጆች
አብዩ አንተነህ
ይብሬ አህመድ
ፍቅረ አሰፋ

አርታኢ እና ገምጋሚዎች:-
ሙስጠፋ ከድር
ሮዳስ ድሪባ
ገስጥ አሰፋ

ግራፊክስ ዲዛይን
ግርማ ዳርጌ
ኃ/ጊዮርጊስ ተመስገን

አስተባባሪ
ጌታቸው ታለማ አጥናፉ

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

© 2015 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱትን ጥቅሶችና ሥዕሎች በምንጭነት
የተጠቀመባቸውን ሁሉ እናመሰግናለን፡፡

## ምስጋና

ይህን የትምህርት መጽሐፍ ከዝግጅት ጀምሮ በውጤት እንዲጠናቀቅ፣ የካበተ ልምዳቸውን በማካፈል፣ በፓናል ውይይት ሃሳብ በማፍለቅና በማቅረብ፣ በከተማችን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲዘጋጅ በማድረግ፣ አስፈላጊውን በጀት በማስፈቀድ እንዲሁም በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲመራ በማድረጋቸው ላደረጉት ከፍተኛ ድጋፍ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ዘላለም ሙላቱ የላቀ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

ለስራችን መሳካት ሁልጊዜ አብረውን በመሆን ፣ በሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት፣ የአፈጻጸም ሂደቱን በመከታተል፣ በመገምገም እንዲሁም የዝግጅቱ ስራ ቁልፍ ስራ መሆኑን ተረድተው ትኩረት በመስጠት ከጎናችን ለነበሩ የትምህርት ቢሮ የማኔጅመንት አባላት የስርዓተ ትምህርት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አድማሱ ደቻሳ፣ የትምህርት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳኛው ገብሩ፣ የመምህራን ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሳምሶን መለሰ፣ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አማካሪ ወ/ሮ አበበች ነጋሽ፣ የትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ እንዳለ፣ የቴክኒክ አማካሪ አቶ ደስታ መርሻ ላበረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በመጨረሻም መጽሐፉ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን ለስራው ልዩ ትኩረት በመስጠት አዘጋጅ መምህራንን ስለላካችሁልንና የሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁም ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

ማዉጫ ገጽ

ምዕራፍ 1

እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችና ቅደም ተከተላቸዉ ...................... 1

1.1 በ100 እና በ1000 መቁጠር ........................................................ 1

1.2 እስከ 10,000 ያሉ ቁጥሮችን የቤት ዋጋ ............................................ 3

1.3 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደር .................................. 6

1.4 ቁጥሮችን በቁጥር ቤት ዋጋቸው ማጠጋጋት .................................... 9

1.5 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ10፣በ100 እና በ1,000 ቤት ማጠጋጋት .......................................................... 11

የምዕራፍ 1 ማጠቃለያ ................................................................ 15

የምዕራፍ 1 የማጠቃለያ መልመጃ .................................................. 16

ምዕራፍ 2

እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች መደመር እና መቀነስ.......... 17

2.1 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር ................................ 17

2.2 እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ.................................... 21

2.3 ሙሉ ቁጥሮችን መደመር እና መቀነስ የያዙ የቃላት ፕሮብሌሞች ........ 26

የምዕራፍ 2 ማጠቃለያ ................................................................ 29

የምዕራፍ 2 ማጠቃለያ መልመጃ .................................................... 30

ምዕራፍ 3

እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት ................................ 31

3.1 የ10 እና የ100 ብዜቶችን በባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮች ማባዛት ................ 31

3.2 የማባዛት ውጤታቸው ከ1000 ያነሱ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ማባዛት ...................................................... 33

3.3 እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት መሰረት ያደረጉ የቃላት ፕሮብሌሞች ........................................................ 38

የምዕራፍ 3 ማጠቃለያ ................................................................ 40

የምዕራፍ 3 ማጠቃለያ መልመጃ .................................................... 41

ምዕራፍ 4 42
እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማካፈል ......................................
4.1 እኩል ክፍፍል እና ማካፈልን በተደጋጋሚ 42
መቀነስ መስራት ........................................................................ 45
4.2 እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ2 ማካፈል ...................................... 48
4.3 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ2 እና በ10 ማካፈል ......................... 51
4.4 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ1 ማካፈል ..................................... 52
4.5 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ3፣4፣5፣6፣7 8 እና 9 ማካፈል....... 65
4.6 ማባዛት እና ማካፈል ያላቸው ዝምድና............................................... 68
የምዕራፍ 4 ማጠቃለያ ....................................................................... 69
የምዕራፍ 4 የማጠቃለያ መልመጃ ..........................................................
ምዕራፍ 5 70
ጎነ ሶስቶች እና ጎነ አራቶች ........................................................ 70
5.1 ግማሽ፣ሲሶና ሩብ ........................................................................ 75
5.2 ከ 1/2 እስከ 1/10 ያሉ አሃዳዊ ክፍልፋዮች ...................................... 78
5.3 ግማሽ እና ሩብ ........................................................................ 79
5.4 ክፍልፋዮችን መግለፅ ................................................................. 82
የምዕራፍ 5 ማጠቃለያ ....................................................................... 83
የምዕራፍ 5 ማጠቃለያ መልመጃ ........................................................
ምዕራፍ 6 84
6.1 ቀጣይነት ያላቸውን ንድፎች መለየት ............................................ 84
6.1 ተደጋጋሚ ንድፎችን ማጠቃለል ....................................................... 86
6.2 እያደገ ያለ ስዕላዊ ንድፍ ማስቀጠል ..................................................
6.3 ቀጣይነትና ተደጋጋሚነት ያላቸዉን የሩቅ አባላት 90
ንድፎችን መተንበይ ..................................................................... 97
የምዕራፍ 6 ማጠቃለያ ....................................................................... 98
የምዕራፍ 6 የማጠቃለያ መልመጃ ..........................................................

**ምዕራፍ 7**
**እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት እና ማካፍል............... 99**
7.1 የ1,000 ብዜቶችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ማባዛት .................... 99
7.2 የ10 እና የ100 ብዜቶችን በባለ አንድ ሆሄ ማካፈል ............................ 100
7.3 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማባዛት ........................................................................ 101
7.4 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ እና በ10 ማካፈል ........................................................................ 104
የምዕራፍ 7 ማጠቃለያ ........................................................................ 107
የምዕራፍ 7 ማጠቃለያ መልመጃዎች ........................................................ 108
**ምዕራፍ 8**
**መረጃ አያያዝ ........................................................................ 109**
8.1 ስዕላዊ ግራፎች ........................................................................ 109
8.2 ስዕላዊ ግራፎችን ማንበብና መፃፍ ................................................ 112
የምዕራፍ 8 ማጠቃለያ ........................................................................ 122
የምዕራፍ 8 ማጠቃለያ መልመጃ ........................................................ 123
**ምዕራፍ 9**
**የጂኦሜትሪ ምስሎች ........................................................................ 127**
9.1 ማንሸራተት፣ማዞር እና ማንፀባረቅ በታወቀ ማዕዘን መተግበር ................. 127
9.2 ምጥጥን ቅርፅ ያላቸው እና የሌላቸውን መለየት .................................. 129
9.3 በጎናቸው መሰረት የጂኦሜትሪ ምስሎችን መለየት እና መሰየም ............... 132
9.4 የጂኦሜትሪ ቅርፆችን ባህሪያት ማደራጀትና መሰየም .............................. 135
የምዕራፍ 9 ማጠቃለያ ........................................................................ 139
የምዕራፍ 9 ማጠቃለያ መልመጃ ........................................................ 140
**ምዕራፍ 10**
**ልኬት፣ ርዝመት፣ መጠነቁስ እና ይዘት............................................ 141**
10.1 ርዝመትን ፣በሚ.ሜ፣በሳ.ሜ፣በሜ እና በኪ.ሜ መለካት.......................... 141
10.2 የርዝመት አሀዶችን ወደ አንስተኛ አሀድ መቀየር ................................ 143
10.3 መጠነቁስ በሚሊግራም፣ ግራም፣ ኪሎ ግራም እና በኩንታል መለካት 145

10.4 የመጠነቁስ አሀዶችን ወደ አነስተኛ አሀድ መቀየር ........................... 146
10.5 ይዘትን በሚሊ ሊትር እና በሊትር መለካት .................................. 148
የምዕራፍ 10 ማጠቃለያ .................................................................... 152
የምዕራፍ 10 ማጠቃለያ መልመጃ ........................................................ 153
ምዕራፍ 11
የኢትዮጵያ ገንዘብ .............................................................................. 154
11.1 የገንዘብ ምንዛሬ ምድብ መቀያየር ...................................................... 155
11.2 ገንዘብን ማወዳደር ......................................................................... 161
የምዕራፍ 11 ማጠቃለያ .................................................................... 165
የምዕራፍ 11 ማጠቃለያ መልመጃ ........................................................ 166
ምዕራፍ 12
የኢትዮጵያ ጊዜ ................................................................................. 167
12.1 ሰዓቶችን ማንበብ ......................................................................... 167
12.2 ሰዓትና ደቂቃዎች ......................................................................... 170
12.3 ቀናት፣ ሳምንታት፣ ወራትና ዓመታት................................................ 172
12.4 የኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር.............................................................. 174
የምዕራፍ 12 ማጠቃለያ .................................................................... 180
የምዕራፍ 12 ማጠቃለያ መልመጃ ........................................................ 181

# ምዕራፍ 1 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችና ቅደም ተከተላቸዉ

የመማር ማስተማር ውጤቶች: ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፣

- የሙሉ ቁጥሮች የቤት ዋጋ ትረዳላችሁ::
- እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ማወዳደር እና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ትረዳላችሁ::

## 1.1 በ100 እና በ1000 መቁጠር

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት

- በ100 እና በ1000 መቁጠር

**ተግባር ሀ**

1. ሰባት ልጆች እያንዳንዳቸው አንድ መቶ ብር ቢኖራቸው በአጠቃላይ ስንት ብር ይኖራቸዋል?
2. በ4500 ስንት መቶዎች እና ሺዎች አሉ?
3. ከታች ያሉትን ክቦች በመመልከት ስንት መቶዎች እና ሺዎች አሉ? ቁጥሩን በፊደል እና በአሃዝ ፃፉ::

ሀ




ለ



ምሳሌ ሀ

1. የሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ስንት ሺዎች ፣ ስንት መቶዎች እና ስንት አንዶች አሉት?

   ሀ.5600

   5 ሺዎች እና 6 መቶዎች አሉ::

   ለ.6780

   6 ሺዎች፣ 7 መቶዎች፣ 8 አስሮች እና 0 አንዶች

2. የሚከተሉን ሙሉ ቁጥሮች በአሃዝ ፃፉ::

   ሀ. 5 መቶዎች፣7 አስሮች

   5x100+7x10=570

   ለ. 6 ሺዎች፣7 መቶዎች፣3 አስሮች፣ 4 አንዶች

   6x1000+7x100+3x10+4=6734

   ሐ. 2 ሺዎች፣5 አስሮች እና 7 አንዶች

   2x1000+5x10+7 = 2057

3. ከታች ያሉትን ክቦች በመመልከት ስንት አንዶች፣ስንት አስሮች፣ስንት መቶዎች እና ስንት ሺዎች አሉት? ቁጥሩን በአሃዝ ፃፉ::

ሀ




በክብ ሞደሉ እንደምንመለከተው

2 ሺዎች፣3 መቶዎች እና 2 አንዶች

= 2302

ለ




በክብ ሞደሉ እንደምንመለከተው

1ሺ፣3 መቶዎች፣4 አንዶች

=1304

## መልመጃ ሀ

1. የሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ስንት ሺዎች ፣ ስንት መቶዎች እና ስንት አንዶች አሉት?

   ሀ.5621 ለ.9082 ሐ.6640

2. የሚከተሉን ሙሉ ቁጥሮች በአሃዝ ፃፉ፡፡

   ሀ.8 ሺዎች፣4 መቶዎች፣4 አስሮች እና 9 አንዶች ያሉት ቁጥር፡፡

   ለ.1 ሺዎች፣6 መቶዎች፣8 አስሮች እና 2 አንዶች ያሉት ቁጥር፡፡

   ሐ. 5ሺዎች፣2 መቶዎችእና 8 አንዶች ያሉት ቁጥር፡፡

3. ከታች ያሉትን የክብ ሞዴሎችን በመመልከት ስንት አንዶች፣ስንት አስሮች፣ ስንት መቶዎች እና ስንት ሺዎች አሉት? ቁጥሩን በአሃዝ ፃፉ፡፡

ሀ




ለ




### 1.2 እስከ 10000 ያሉ ቁጥሮችን የቤት ዋጋ

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት

- እስከ 10000 ያሉ ቁጥሮችን የቤት ዋጋ መለየት

**ማስታወሻ**

የሙሉ ቁጥሮችን የቤት ዋጋ ለማወቅ ከቀኝ ወደ ግራ በቅደም ተከተል

- የአንድ ቤት
- የአስር ቤት
- የመቶ ቤት
- የሺ ቤት እና
- የአስር ሺ ቤት በማለት በቅደም ተከተል እንሰይማለን፡፡

ምሳሌ ሀ

ለሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ለእያንዳንዱ ሆሄ የቤት ዋጋ ፃፉ::

ሀ. 5437 ለ.657

ሐ. 8086 መ. በ4356 ሆሄ——የመቶ ቤት ነው::

መፍትሔ

ሀ.

| ሺ ቤት | የመቶ ቤት | የአስር ቤት | የአንድ ቤት |
|---|---|---|---|
| 5 | 4 | 3 | 7 |

ይህም በፊደል ሲፃፍ አምስት ሺ አራት መቶ ሰላሳ ሰባት ነው::

5000፣400፣30 እና 7

ለ.

| የመቶ ቤት | የአስር ቤት | የአንድ ቤት |
|---|---|---|
| 6 | 5 | 7 |
| 6 መቶዎች | 5 አስሮች | 7 አንዶች |

ይህም በፊደል ሲፃፍ ስድስት መቶ ሀምሳ ሰባት ነው::

600፣50 እና 7

ሐ.

| የሺ ቤት | የመቶ ቤት | የአስር ቤት | የአንድ ቤት |
|---|---|---|---|
| 8 | 0 | 8 | 6 |
| 8 አንድ ሺዎች | 0 መቶዎች | 8 አስሮች | 6 አንዶች |

ይህም በፊደል ሲፃፍ ስምንት ሺ ሰማንያ ሀምሳ ስድስት ነው::

ይህም ማለት ቁጥሩ ሲተነተን 8000፣0፣80 እና 6 ናቸው::

መ. በ4356 የመቶ ቤት ከግራ ወደ ቀኝ ሶስተኛው ሆሄ ስለሆነ 3 የመቶ ቤት ነው::

<u>ምሳሌ ለ</u> የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች በአሃዝ ፃፉ።

ሀ· አምስት መቶ ስልሳ ሁለት ለ· ሁለት ሺ አምስት መቶ ሰማንያ አምስት

ሐ· አራት ሺ አራት መቶ ስድስት መ· ስምንት ሺ ሰባ ስድስት

መፍትሔ

ሀ. 562 ለ. 2585 ሐ. 4406 መ. 8076

## መልመጃ ለ

1.ለሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች የእያንዳንዳቸውን ቁጥሮች የቤት ዋጋ ፃፉ::

ሀ.34512 ለ.3098 ሐ.129 መ.2305

2.የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች በአሃዝ ፃፉ።

ሀ. ሁለት ሺ አምስት መቶ አስራ ሶስት

ለ. ሶስት ሺ አምስት መቶ ሶስት

ሐ. ዘጠኝ ሺ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አንድ

መ. አንድ ሺ ስምንት መቶ አስራ ስድስት

3. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች በፊደል ፃፉ::

ሀ· 3526 ለ· 908 ሐ. 9984

4. በግራ በኩል ያሉትን በአሀዝ የተፃፉ ሙሉ ቁጥሮች በቀኝ በኩል በፊደል ከተፃፉ ጋር አዛምዱ::

| <u>ሀ</u> | <u>ለ</u> |
|---|---|
| —1. 6855 | ሀ. ሦስት ሺ ስምንት መቶ ዘጠና አምስት |
| —2. 4560 | ለ. ስድስት ሺ አራት መቶ ሃምሳ አምስት |
| —3. 3240 | ሐ. አራት ሺ አምስት መቶ ስልሳ |
| —4. 6455 | መ. ስድስት ሺ ስምንት መቶ ሃምሳ አምስት |
| —5. 3895 | ሠ. ሦስት ሺ ሁለት መቶ አርባ |
| —6. 4980 | ረ. አራት ሺ ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ |

## 1.3 እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደር

**የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት**

- እስከ 10000 ድረስ ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደር

<u>ምሳሌ ሀ</u>

ከታች ያለውን ስዕል በማየት የማወዳደር ሀሳብን መረዳት ይቻላል::

ሀ. ለ. ሐ.



4 > 2 3 = 3 2 < 4

**ማስታወሻ**

ሁለት ሙሉ ቁጥሮችን ለማወዳደር የሚከተሉትን ምልክቶች እንጠቀማለን::

- " > " ምልክቱ ይበልጣል ይባላል : :
- " < " ምልክቱ ያንሳል ይባላል : :
- "= " ምልክቱ እኩል ይሆናል ይባላል።

<u>ምሳሌ ለ</u>. 4 < 15 ለ. 90 > 8 ሐ. 60 = 60

ሀ. ሁለት የተለያየ ሆሄ ብዛት ያላቸው ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደር

**ማስታወሻ**

ሁለት ሙሉ ቁጥሮች የሆሄያት ብዛት የተለያዩ ከሆነ ብዙ ሆሄያት የያዘው ሙሉ ቁጥር ይበልጣል::

<u>ምሳሌ ሐ</u> የሚከተሉትን ቁጥሮች " < " ፣ " >" ወይም "=" በመጠቀም አወዳድሩ::

ሀ. 34 ___123 ለ. 286 ___98 ሐ. 346____3477

መፍትሔ ፡

ሀ. 34 < 123 ምክንያቱም 34 ባለሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥር ሲሆን 123 ደግሞ ባለሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥር ነው፡፡

ለ. 286 > 98 ምክንያቱም 286 ባለሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥር ሲሆን 98 ደግሞ ባለሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥር ነው፡፡

ሐ. 346 < 3477 ምክንያቱም 346 ባለሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥር ሲሆን 3477 ደግሞ ባለአራት ሆሄ ሙሉ ቁጥር ነው፡፡

**መልመጃ ሀ**

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች "<" ፣ ">" ወይም "=" በመጠቀም አወዳድሩ፡፡

ሀ. 567___ 5677 ለ. 989 ___ 99

ሐ. 3888 _____ 880 መ. 760 ___ 7600

ሠ.4562 ___4562 ረ. 8970 _____999

ለ. ሁለት እኩል የሆሄያት ብዛት ያላቸው ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደር

ተግባር ሀ

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች "<" ፣ ">" ወይም "=" በመጠቀም አወዳድሩ፡፡

ሀ. 20 —30 ለ. 36 —16 ሐ .57—95

መ. 28 —25 ሠ. 72 —74

ምሳሌ መ  የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አወዳድሩ : :

ሀ.2345 እና 4561

| የሺ ቤት | የመቶ ቤት | የአስርቤት | የአንድ ቤት |
|---|---|---|---|
| 2 | 3 | 4 | 5 |
| 4 | 5 | 6 | 1 |

ሺዎችን ማወዳደር

4000 ከ2000 ይበልጣል ስለዚህ4561 >2345

ለ.4353 እና4358




መፍትሔ

የሁለቱም ቁጥሮች የሺ ቤት እኩል ነው፤

የመቶ ቤቱም እኩል ነው:: የአስር ቤቱም ቁጥር እኩል ነው

ግን የአንድ ቤቱን ስንመለከት 3 ከ 8 ያንሳል::

ስለዚህ 4353<4358::

**ማስታወሻ**

ቁጥሮችን የማወዳደሪያ ዘዴዎች

የእያንዳንዱን ቁጥር ሆሄያት ብዛት በማየት ማወዳደር ::

- ✓ ብዙ ሆሄያትያለው ሙሉ ቁጥር ይበልጣል:: ምሳሌ 45 < 765
- ✓ የሚወዳደሩ ቁጥሮች እኩል የሆሄያት ብዛት ካላቸው ከግራ ወደ ቀኝ የቤት ዋጋበመጀመር ተራ በተራ ማወዳደር::

ምሳሌ 235>219 ምክንያቱም የአስር ቤት3>1

7599 < 7692 ምክንያቱም የመቶ ቤት 5 < 6

### መልመጃ ለ

1.በሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች ላይ የ" < "፣ " > " ወይም " =" ምልክቶችን በመጠቀም ቁጥሮችን አወዳድሩ::

ሀ. 456 ____3567 ለ. 2908____2899

ሐ. 4567 _____4589 መ. 5009—5109

2.የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አወዳድሩ::

ሀ.486 እና 691 ለ. 542እና 534

ሐ. 891 እና 896 መ.4879 እና4859

## 1.4 እስከ10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት

- እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ

### ተግባር ሀ

1.የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተል አስቀምጡ::

ሀ.1234፣345፣5677 እና 6578

ለ.89፣1002፣2345፣9087 እና 1400

2.የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተል አስቀምጡ::

ሀ.78፣3421፣9008፣8909 እና 4459

ለ.890፣980፣4250፣4255 እና 25554

<u>ምሳሌ ሀ</u>

1.የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተል አስቀምጡ::

ሀ.456፣567፣345 እና 1239

ለ.3400፣450፣5060 እና 6005

2. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተል አስቀምጡ::

ሀ.8943፣2456፣488 እና 2465 ለ.456፣12፣3450 እና 10000

መፍትሄ ሀ. ቁጥሮችን ስናወዳድር የ ቁጥር ቤት ዋጋን መሰረት ማድረግ አለብን::

በመጀመሪያ ብዙ ሆሄያት የያዘው ቁጥር ይበልጣል:: በመቀጠል ደግሞ እኩል ሆሄያት ያላቸውን ስንመለከት 5 ትልቁ፣4 ደግሞ ከ3 ይበልጣል:: ስለዚህ ከትንሽ ወደ ትልቅ ሲደረደሩ345፣456፣567፣1239 ነው::

| የሺ ቤት | የመቶ ቤት | የአስር ቤት | የአንድ ቤት |
|---|---|---|---|
| | 4 | 5 | 6 |
| | 5 | 6 | 7 |
| | 3 | 4 | 5 |
| 1 | 2 | 3 | 9 |

ለ. መፍትሔ : ሁሉም ቁጥሮች እኩል ሆሄያት ስላላቸው ከግራ ወደ ቀኝ በቤት ዋጋቸው እናወዳድራለን::

በዚህም መሰረት የሺ ቤት 6 ከ5 እና 3 ይበልጣል:: 5 ደግሞ ከ3 ይበልጣል::450 ደግሞ የሆሄያት ብዛት ስለሚያንስ ከሁሉም ያነሰ ቁጥር ነው::
ስለዚህ ከትንሽ ወደ ትልቅ ሲደረደሩ 450፣ 3400፣5060 እና 6005 ነው::

| የሺ ቤት | የመቶ ቤት | የአስር ቤት | የአንድ ቤት |
|---|---|---|---|
| 3 | 4 | 0 | 0 |
| | 4 | 5 | 0 |
| 5 | 0 | 6 | 0 |
| 6 | 0 | 0 | 5 |

2. ከላይ ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተል ለማስቀመጥ በተጠቀምነው ስልት መሰረት እያንዳንዱን ቁጥር ካወዳደርን በኋላ እንደሚከተለው ከትልቅ ወደ ትንሽ ይደረደራሉ::

ሀ.8943፣2465፣2456 እና 488 ለ. 10000፣3450፣456 እና 12

## መልመጃ ሀ

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ከትንሹ ወደ ትልቁ በቅደም ተከተል አስቀምጡ፡፡

   ሀ. 491፣ 831፣ 591፣ 521　　　ለ. 832፣ 28፣ 3598፣ 7582

   ሐ. 6548፣ 2301፣1009፣ 5988

2. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ከትልቁ ወደ ትንሹ በቅደም ተከተል አስቀምጡ፡፡

   ሀ. 345፣ 389፣ 487፣ 425፣1986　　　ለ.999፣125፣1000፣ 8000

3. የሚከተሉት 5 ተማሪዎች በአንድ ክፍል የሚማሩ የ3ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ተማሪዎቹ በሒሳብ ትምህርት ከመቶ ያገኙት ዉጤት ለማ 96 ፤ሜሮን 99 ፤አቤል 94፣ሃያት 100 እና አሊ 97 ነው፡፡የፈተና ውጤታቸውን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

ሀ.በሒሳብ ት/ም ከፍተኛ ያመጣው/ችው ተማሪ ስም________ ነው/ነች፡፡

ለ.በሒሳብ ት/ም ዝቅተኛ ያመጣው/ችው ተማሪ ስም________ ነው/ነች፡፡

## 1.5 እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ10፣በ100 እና በ1000 ቤት ማጠጋጋት

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት

- እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ10፣በ100 እና በ1000 ቤት ማጠጋጋት

### ተግባር ሀ

1.የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በቡድን በመሆን ተወያዩ፡፡

ሀ.27 ከ30 እና ከ20 ለየትኛው ቁጥር የቀረበ ነው?

ለ.693 ከ600 እና ከ700 ለየትኛው የቀረበ ነው?

ሐ.4237 ከ4000 እና ከ5000 ለየትኛው ቁጥር የቀረበ ነው?

ማስታወሻ

1. አንድን ቁጥር በ10 ቤት ለማጠጋጋት የአንድ ቤት ሆሄው ከ5 ካነሰ በዜሮ እንተካዋለን ነገር ግን 5 እና ከ5 በላይ ከሆነ ከአስር ቤት ሆሄው አንድ ደምረን የአንድ ቤት ሆሄውን በዜሮ እንተካለን:: ውጤቱንም የአቅራብ ዋጋ እንለዋለን::

ምሳሌ ሀ

የሚከተሉትን ቁጥሮች 10 ቤት አጠጋጉ::

ሀ.2364 ለ. 5678

ሐ. 9823 መ. 625

መፍትሔ

ሀ.2364

2364 በ10 ቤት ለማጠጋጋት 4ከ5 ስለሚያንስ በዜሮ እንተካዋለን ስለዚህ 2364 አቅራብ ዋጋ 2360 ይሆናል::

ለ. 5678

5678 በ10 ቤት ለማጠጋጋት 8ከ5 ስለሚበልጥ በዜሮ ከተካነው በኋላ ከአስር ቤት ሆሄው 7+1 = 8 ይሆናል:: ስለዚህ 5678 አቅራብ ዋጋ 5680 ይሆናል::

ሐ. 9823

9823 በ10 ቤት ለማጠጋጋት 3ከ5 ስለሚያንስ በዜሮ እንተካዋለን ስለዚህ 9823 አቅራብ ዋጋ 9820 ይሆናል::

መ. 658

625 በ10 ቤት ለማጠጋጋት የአንድ ቤት ሆሄው 5 ስለሆነ በዜሮ ከተካነው በኋላ ከአስር ቤት ሆሄው 2+1 = 3 ይሆናል:: ስለዚህ 625 አቅራብ ዋጋ 630 ይሆናል::

ማስታወሻ

1. አንድን ቁጥር በ100 ቤት ለማጠጋጋት የአስር ቤት ሆሄው ከ5 ካነሰ የአንድ ቤት እና የአስር ቤት ቁጥሮችን በዜሮ እንተካቸዋለን ነገር ግን 5 እና ከ5 በላይ ከሆነ የመቶ ቤት ሆሄው ጋር አንድ ደምረን የአንድ እና የአስር ቤት ሆሄውን በዜሮ እንተካለን:: ውጤቱንም የአቅራብ ዋጋ እንለዋለን::
2. አንድን ቁጥር በ1000 ቤት ለማጠጋጋት የመቶ ቤት ሆሄው ከ5 ካነሰ የአንድ ቤት ፣ የአስር ቤት እና የመቶ ቤት ሆሄያትን በዜሮ እንተካቸዋለን ነገር ግን 5 እና ከ5 በላይ ከሆነ የሺ ቤት ሆሄው ጋር አንድ ደምረን የአንድ ፣ የአስር ቤት እና የመቶ ቤት ሆሄዎችን በዜሮ እንተካለን:: ውጤቱንም የአቅራብ ዋጋ እንለዋለን::

ምሳሌ ለ

1.የሚከተሉትን ቁጥሮች 100 ቤት አጠጋጉ::

ሀ.4681 ለ.1837

2.የሚከተሉትን ቁጥሮች 1000 ቤት አጠጋጉ::

ሀ.3678 ለ.7288

መፍትሔ

1. ሀ. 4681

4681 በ100 ቤት ለማጠጋጋት የአስር ቤት ሆሄው 8ከ 5 ስለሚበልጥ የአንድ እና የአስር ቤት ሆሄውን በዜሮ ከተካነው በኋላ ከመቶ ቤት ሆሄው 6+1 = 7 ይሆናል:: ስለዚህ 4681 አቅራብ ዋጋ 4700 ይሆናል::

ለ.1837

1837 በ100 ቤት ለማጠጋጋት የአስር ቤት ሆሄው 3ከ 5 ስለሚያንስ የአንድ እና የአስር ቤት ሆሄውን በዜሮ እንተካዋለን::ስለዚህ 1837 አቅራብ ዋጋ 1800 ይሆናል::

2. ሀ. 3678

3678 በ1000 ቤት ለማጠጋጋት የመቶ ቤት ሆሄው 6ከ 5 ስለሚበልጥ የአንድ ፣ የአስር ቤት እና የመቶ ቤት ሆሄውን በዜሮ ከተካነው በኋላ ከሺ ቤት ሆሄው 3+1 = 4 ይሆናል:: ስለዚህ 3678 አቅራብ ዋጋ 4000 ይሆናል::

ለ.7288

7288 በ1,000 ቤት ለማጠጋጋት የአስር ቤት ሆሄው 2ከ 5 ስለሚያንስ የአንድ ፣ የአስር ቤት እና የመቶ ቤት ሆሄውን በዜሮ እንተካዋለን::ስለዚህ 7288 አቅራብ ዋጋ 7000 ይሆናል::

## መልመጃ ሀ

1. የሚከተለውን ሰንጠረዥ አሟሉ::

| ቁጥር | በ10 ቤት ሲጠጋ | በ100 ቤት ሲጠጋ | በ1000 ቤት ሲጠጋ |
|---|---|---|---|
| 6789 | | | |
| 4327 | | | |
| 2149 | | | |

## የምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ

- ሁለት ሙሉ ቁጥሮች የሆሄያት ብዛት የተለያዩ ከሆነ ፤ ብዙ ሆሄያት የያዘው ሙሉ ቁጥር ይበልጣል፡፡
- የሚወዳደሩ ቁጥሮች እኩል የሆሄያት ብዛት ካላቸው ከግራ ወደ ቀኝ የቤት ዋጋ በመጀመር ተራ በተራ ማወዳደር:: አንድ ሙሉ ቁጥር የ100 ብዜት የሚባለው ቢያንስ የመጨረሻ ሁለት ሆሄው ዜሮ ከሆነ ነው፡፡
- በመጨረሻም የማወዳደሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም እስከ 10000 ያሉ ሙሉቁጥሮችን ከትንሽ ወደ ትልቅ እና ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደም ተከተል መፃፍ ይቻላል፡፡

## የምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ መልመጃ

ሀ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ አክብቡ፡፡

1. በ8206 ስንት ሺዎች እና ስንት መቶዎች በተከታታይ አሉት?

   ሀ.3እና4 ለ.4 እና 5 ሐ. 8 እና 2 መ. 6 እና9

2. አንድ ሺ ስልሳ አምስት በአሃዝ ሲፃፍ የቱ ነው?

   ሀ. 10065 ለ. 1065 ሐ.1000605 መ.1650

3. ከ5612 የ6 ቤት ዋጋ ከሚከተሉት ውስጥ የቱ ነው?

   ሀ.የሺ ቤት ለ.የአስር ቤት ሐ.የመቶ ቤት መ.የአንድ ቤት

4. ከ4683 የሺ ቤት ዋጋ ያለው ሆሄ የትኛው ቁጥር ነው፡፡

   ሀ.4 ለ.6 ሐ.8 መ.3

ለ. የሚከተሉት ባዶ ቦታዎች "<"፣ ">" ወይም "=" በመጠቀም ሙሉ::

5. 412____7098
6. 2389______2379
7. 1948______1942
8. የ6759 የእያንዳንዳቸውን የቤት ዋጋ ፃፉ፡፡
9. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደምተከተል አስቀምጡ::

   987፣452፣4512 እና 4562

10. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ከትልቅ ወደ ትንሽ በቅደምተከተል አስቀምጡ::

    1062፣1068፣1120፣1099 እና890

11. የጎደለውን ሙሉ::

    ሀ.5687=____ሺዎች+_______መቶዎች+_____አስሮች+________አንዶች

    ለ.4098=____ሺዎች+_______መቶዎች+_____አስሮች+________አንዶች

12. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች በ10 ፣በ100 እና በ1000 ቤት አጠጋጉ::

    ሀ.2964 ለ.3498 ሐ.9025

# ምዕራፍ 2 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች መደመር እና መቀነስ

**የመማር ማስተማር ውጤቶች:**

- እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች መደመር እና መቀነስ ትረዳላችሁ።
- እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በመደመር እና መቀነስ ተግባራዊ ፕሮብሌሞች ትሰራላችሁ።

**መግቢያ**

መደመር እና መቀነስ ከመሰረታዊ የሒሳብ ስሌቶች መካከል በእለት ተእለት ህይወታችን ላይ በከፍተኛ ደረጃ የምንተገብራቸው ናቸው።መደመር ማለት በአጠቃላይ ያሉትን ቁስ አካል ፣መጠን፣ልኬትና ሌሎችንም መቀላቀል ማለት ሲሆን መቀነስ ደግሞ በሁለት ቁሶች ያለውን ልዩነት ለማስላት እንጠቀምበታለን። እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር እና መቀነስ በሁለተኛ ክፍል ላይ የተማራችሁ ሲሆን በዚህ ምዕራፍ ደግሞ እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር እና መቀነስ ትማራላችሁ።

## 2.1 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት

- እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር

**ተግባር ሀ**

1. እስከ 1000 ያሉ የ100 ብዜት ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ፃፉ።
2. እስከ 1000 ካሉ ሙሉ ቁጥሮች ትንሹንና ትልቁን የ100 ብዜት ፃፉ።
3. የሚከተሉትን ቁጥሮች በቃላችሁ ደምሩ።

ሀ. 300 + 500 ሐ. 600 + 400 ለ. 400 +200 መ. 600 + 500

ማስታወሻ

- የ1000 ብዜት የምንላቸው ሙሉ ቁጥሮች ከቁጥሩ በስተቀኝ ቢያንስ ሶስት ዜሮዎች ሲኖሩት ነው::
- ሁለት ከ10000 የሚያንሱ የ1000 ብዜት ቁጥሮችን በቃል ስትደምሩ፤ በሺ ቤት የሚገኙትን ሆሄያት ደምራችሁ በቀኝ በኩል ሦስት ዜሮዎችን መጻፍ ነው::

ምሳሌ ሀ

1 ከሚከተሉት ቁጥሮች የ1000 ብዜቶችን ለዩ ::

4000 ፣ 6000፣ 2200፣ 1500 እና 3000

2 የሚከተሉትን ቁጥሮች በቃላችሁ ደምሩ::

ሀ. 5000 + 4000 ለ. 3000 + 6000 ሐ. 7000 + 1000

መፍትሔ

1. 4000፣ 6000 እና 3000 የ1000 ብዚቶች ሲሆኑ 2200 እና1500 የ1000 ብዜቶች አይደሉም
2. ሀ. በ5000 ውስጥ በሺ ቤት የሚገኘው ሆሄ 5 እና በ4000 ውስጥ በሺ ቤት የሚገኘው ሆሄ 4 ስለሆነ በሺ ቤት የሚገኙት ሆሄያት ድምር 9 ይሆናል ስለዚህ የ4000 እና 5000 ድምር 9000 ነው::

   ለ. በ3000 ውስጥ በሺ ቤት የሚገኘው ሆሄ 3 እና በ6000 ውስጥ በሺ ቤት የሚገኘው ሆሄ 6 ስለሆነ በሺ ቤት የሚገኙት ሆሄያት ድምር 9 ይሆናል:: ስለዚህ የ 3000 እና 6000 ድምር 9000 ነው::

   ሐ. በ7000 ውስጥ በሺ ቤት የሚገኘው ሆሄ 7 እና በ1000 ውስጥ በሺ ቤት የሚገኘው ሆሄ ስለሆነ በሺ ቤት የሚገኙት ሆሄያት ድምር 8 ነው::

ስለዚህ የ7000 እና የ1000 ድምር 8000 ነው::

## ሀ. ባለሁለት እና ባለሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር

ምሳሌ ለ

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች ወደ ጎን በመተንተን ደምሩ::

ሀ . 543 +75 ለ. 846 + 39

2. የሚከተሉትን ቁጥሮች ቁልቁል ደምሩ::

ሀ . $\begin{array}{r}456\\+\ 45\\\hline\end{array}$ ለ. $\begin{array}{r}678\\+\ 79\\\hline\end{array}$

መፍትሔ :

1. ሀ. 543+75 =500+40+3+70+5
=500+110+8
=500+100+10+8
= 600 + 18 = 618

ለ. 846+39 = 800+40+6+30+9
= 800 +70+15
= 800 +70+10+5
=800 + 80 + 5 = 885

2. ሀ . $\begin{array}{r}456\\+\ 45\\\hline 501\end{array}$ ለ. $\begin{array}{r}678\\+\ 79\\\hline 757\end{array}$

**ማስታወሻ**

ከአንድ ቤት በመጀመር ሆሄዎችን መደመር: በአለኝታ የሚደመሩ ከሆነ አለኝ የሚለውን ቁጥር ከሚቀጥለው ትልቅ ቁጥር ቤት ሆሄያት ጋር መደመር

## ለ. የባለሦስት ሆሄ ቁጥሮች ከባለአራት ሆሄ ቁጥሮች ጋር መደመር

ምሳሌ ሐ

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች ወደ ጎን በመተንተን ደምሩ::

ሀ . 5230 + 759 ለ. 8446 + 379

2. የሚከተሉትን ቁጥሮች ቁልቁል ደምሩ::

ሀ . $\begin{array}{r}3456\\+\ 480\\\hline\end{array}$ ለ . $\begin{array}{r}6228\\+\ 456\\\hline\end{array}$

መፍትሔ :

1. ሀ. 5230 + 759
 = 5200+30+6+700+50+9
 =5200+700+80+15
 = 5900+80+10+5 = 5995

 ለ. 8446 + 379
 = 8400+40+6 + 300+70 + 9
 = 8400+300+40+70+6+9
 = 8400+300+110+15
 = 8400+300+100+10+5 = 8815

2. ሀ. $\begin{array}{r}3456\\+\ 480\\\hline 3936\end{array}$   ለ . $\begin{array}{r}6228\\+\ 456\\\hline 6684\end{array}$

## መልመጃ ሀ

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች ደምሩ::

 ሀ· 5000 + 2000   ሐ· 7000 + 2000

 ለ· 4000 + 4000   መ· 8000 + 2000

2. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ወደ ጎን ደምሩ::

 ሀ. 4481 + 234   ለ. 7356 + 2478

 ሐ. 5750 + 276   መ. 6297+2970

3. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ቁልቁል ደምሩ::

 ሀ. $\begin{array}{r}686\\+\ 18\\\hline\end{array}$   ለ. $\begin{array}{r}8552\\+\ 673\\\hline\end{array}$   ሐ. $\begin{array}{r}1248\\+\ 562\\\hline\end{array}$   መ. $\begin{array}{r}8890\\+\ 1256\\\hline\end{array}$

4. የሚከተለውን ሰንጠረዥ አሟሉ::

| ሀ | በ | ሀ+በ |
|---|---|---|
| 3400 | 470 | |
| 4500 | 4530 | |
| 7800 | 2458 | |
| 230 | 8800 | |

## 2.2 እስከ 10000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት

እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ

ሀ.ከባለ ሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ ባለሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ

ተግባር ሀ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን ስሩ፡፡

1.በአንድ ክፍል ካሉ 32 ተማሪዎች ውስጥ 4ቱ ከት/ቤት ቢቀሩ በክፍል ውስጥ ስንት ተማሪዎች ይኖራሉ?

2. አፍሪቃ ውስጥ ካሉ 55 ሀገራት 37 ሀገራት አረንጓዴ፣ቢጫ እና ቀይ ቀለማትን ይጠቀማሉ፡፡ከእነዚህ 55 ሀገራት ውስጥ ስንቶቹ ናቸው አረንጓዴ፣ቢጫ እና ቀይ ቀለማት የማይጠቀሙት?



ማስታወሻ

ከባለሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ ባለሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ስንቀንስ በሁለት መንገድ ሊሰሩ ይችላሉ፡፡

- አንደኛው አሰራር ቁጥሮችን ተንትኖ መቀነስ ሲሆን፡፡
- ሁለተኛው አሰራር ደግሞ ቁጥሮቹን በቁጥር ቤት ዋጋቸው ቁልቁል ዕፎ ሆሄያትን በየቤታቸው መቀነስ ነው፡፡

ምሳሌ ሀ

1.የሚከተሉትን ቁጥሮች በመተንተን ቀንሱ፡፡

ሀ. 678-56 ለ. 456-28

መፍትሔ:

ሀ. 678-56 = 600+70+8-(50+6)

= 600+(70-50) +(8-6)

= 600+20+2 = 622

ለ. 456-28 = 400+50+6-20-8

= 400+(40-20)+(16-8)

= 400+20+8 = 428

2. ቁጥሮችን በቁጥር ቤት ዋጋቸው ቁልቁል በመፃፍ ቀንሱ፡፡

ሀ . $\begin{array}{r} 896 \\ -\ 74 \\ \hline \end{array}$ በመጀመሪያ በአንድ ቤት ያሉትን መቀነስ 6-4 = 2 እና

ውጤቱን በ አንድ ቤት መፃፍ በመቀጠል በአስር ቤት ያሉትን

መቀነስ

9 -7 = 2 በመቶ ቤት ያለውን ሆሄ 8 እንዳለ በመቶ ቤት መፃፍ ምክንያቱም የታችኛው ቁጥር የመቶ ቤት ስለሌለው ነው፡፡

ስለዚህ $\begin{array}{r} 896 \\ -\ 74 \\ \hline 822 \end{array}$ ይሆናል ማለት ነው፡፡

ለ. $\begin{array}{r} 544 \\ -\ 78 \\ \hline \end{array}$ በዚህ ምሳሌ ደግሞ በአንድ ቤት ያሉትን ሆሄያት ስናወዳድር 4< 8 ፤

ስለዚህ ከ10 ቤት አንድ 10 ወስዶ ከ4 ጋር መደመር ፤ከድምሩ መቀነስ፡፡

10+4 - 8 = 14 - 8 = 6 ውጤቱን በአንድ ቤት ስር መፃፍ ከዋናው 10 ቤት የቀረን 3 ነው፡፡

አሁንም 3 < 7 ከመቶ ቤት አንድ 10 ወስዶ ከ 3 ጋር መደመር 10+3 = 13

ከዚያም 13 - 7 = 6 ውጤቱን በአስር ቤት ስር መፃፍ፡፡

ከዋናው መቶ ቤት የቀረው 4ን በመቶ ቤት ስር መፃፍ፡፡

ስለዚህ $\begin{array}{r} 544 \\ -\ 78 \\ \hline 466 \end{array}$ ይሆናል ማለት ነው፡፡

ማስታወሻ

ሀ፣ ለ እና መ ሙሉ ቁጥሮች ሲሆኑ ሀ > ለ እና ሀ - ለ = መ ከሆነ

ሀ = ዋና ፤ ለ = ተቀናሽ ፤ መ = ልዩነት ይባላሉ፡፡

## ለ. ከባለሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ ባለሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ

ከባለሶስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ ባለሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ ከአሁን በፊት የተማራችሁትን በማስታወስ በተመሳሳይ መንገድ ባለሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ከባለሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች መቀነስ ትችላላችሁ፡፡ከዚህ በፊት እንዳያችሁት ቁጥሮችን በቁጥር ቤት ዋጋቸው በመተንተን እና በቁጥር ቤት ዋጋቸው ቁልቁል ፅፎ በቤት በቤታቸው መቀነስ ይቻላል፡፡

ማስታወሻ

የሁለት ሙሉ ቁጥሮችን ልዩነት ስንፈልግ ከትልቁ ቁጥር ትንሹን በመቀነስ ነው፡፡ ይህ ማለት አንድ ሙሉ ቁጥር ከሌላው ሙሉ ቁጥር በስንት እንደሚበልጥ ወይንም እንደሚያንስ የሚታወቀው ከትልቁ ላይ ትንሹን በመቀነስ ይሆናል፡፡

ምሳሌ ለ

ሀ. የ357 እና 686 ልዩነት ስንት ነው?

ለ. ሊያ 920 ብር ቢኖራት እና ሰኢድ ደግሞ 870 ብር ቢኖረው ባላቸው የብር መጠን መካከል የስንት ብር ልዩነት አለ?

መፍትሔ:

ልዩነት የምናገኘው ትንሹን ቁጥር ከትልቁ በመቀነስ ስለሆነ

ሀ. $\begin{array}{r} 686 \\ -\ 357 \\ \hline 329 \end{array}$

ለ. $\begin{array}{r} 920 \text{ ብር} \\ -\ 870 \text{ ብር} \\ \hline 50 \text{ ብር} \end{array}$

## መልመጃ ሀ

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ልዩነት ፈልጉ፡፡

ሀ.450 - 42 ለ.568 - 79 ሐ . 892 - 678

2. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች በመተንተን ቀንሱ፡፡

ሀ . 876 - 45 ለ. 312 - 76 ሐ. 987-296 መ. 650-322

3. የሚከተሉትን ቁጥሮች ቁልቁል ቀንሱ፡፡

ሀ. $\begin{array}{r} 536 \\ -\ 24 \\ \hline = \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 780 \\ -\ 50 \\ \hline = \end{array}$ ሐ. $\begin{array}{r} 645 \\ -\ 424 \\ \hline = \end{array}$ መ. $\begin{array}{r} 989 \\ -\ 435 \\ \hline = \end{array}$

4. የሚከተሉትን ቁጥሮች ቁልቁል ቀንሱ፡፡

ሀ. $\begin{array}{r} 185 \\ -\ 79 \\ \hline = \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 456 \\ -\ 84 \\ \hline = \end{array}$ ሐ. $\begin{array}{r} 786 \\ -\ 188 \\ \hline = \end{array}$ መ. $\begin{array}{r} 546 \\ -\ 438 \\ \hline = \end{array}$

5. ከታች ያለውን ሰንጠረዥ አሟሉ፡፡

| ዋና | ተቀናሽ | ልዩነት |
|---|---|---|
| 456 | 78 | |
| 296 | 288 | |
| | 480 | 240 |
| 984 | | 820 |

## ሐ. ከባለአራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ ባለሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ

**ተግባር ለ**

በቡድን በቡድን በመሆን ለሚከተሉት ጥያቄዎች መፍትሄ ፈልጉ፡፡

1. በተለያዩ ከተሞች በተደረገ የኤች አይቪ ቫይረስ ግንዛቤ ስልጠና በጂማ 2270፡ በባህር ዳር 2400 እና በሐዋሳ 230 ሰዎች ስልጠናዎች የወሰዱ ሲሆን፡

ሀ. በባህር ዳር እና በሐዋሳ የሰለጠኑ ሰዎች ልዩነት ስንት ነው?

ለ .በሐዋሳ እና በጂማ የሰለጠኑት ሰዎች ልዩነት ስንት ነው?

ምሳሌ ሐ የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አስሉ፡፡

ሀ. 8864 - 653 ለ. $\begin{array}{r} 4563 \\ -\ 876 \\ \hline \end{array}$

መፍትሔ:

ሀ.8864 - 653 = 8000+800+60+4-(600+50+3)

= 8000+ (800 - 600) + (60 - 50) + (4-3)

= 8000+200+10+1 = 8211

ለ. $\begin{array}{r} 4563 \\ -\ 876 \\ \hline 3687 \end{array}$

**መ. ከባለአራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ላይ ባለአራት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ**

**ተማሪዎች ከባለፈው ርዕስ ላይ ባለሦስት ሙሉ ቁጥሮች ከባለአራት ሙሉ ቁጥሮች መቀነስ ተምራችኋል ፡፡ በተመሳሳይ መንገድ አሁን ደግሞ ባለአራት ሙሉ ቁጥሮችከባለአራት ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ ትማራላችሁ፡፡**

ምሳሌ መ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን ስሩ፡፡

ሀ. 8420-6210 ለ. $\begin{array}{r} 5283 \\ -\ 4876 \\ \hline \end{array}$

መፍትሔ

ሀ.8420 - 6210 በመተንተን መስራት

8420 - 6210 = 8000+400+20-6000-200-10

= 2000+200+10

= 2210

ለ. $\begin{array}{r} 5283 \\ -\ 4876 \\ \hline 407 \end{array}$

6ን ከ 3 መቀነስ ስለማይቻል ከአስር ቤት ትበደራለች 8 ወደ 7 ይቀንሳል፡፡

10+3 = 13 - 6 = 7

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | 7 | 13 |
| 5 | 2 | 8 | 3 |
| 4 | 8 | 7 | 6 |
| | | | 7 |

8 የነበረው የአስር ቤት 7 ስለሆነ

7-7=0

| | | | |
|---|---|---|---|
| 5 | 2 | 7 | 3 |
| 4 | 8 | 7 | 6 |
| | | 0 | 7 |

በመቀጠል 8ን ከ2 መቀነስ ስለማይቻል ከሺ ቤት ትበደራለች 5 ወደ 4 ይቀንሳል፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| 4 | 12 | | |
| 5 | 2 | 7 | 3 |
| 4 | 8 | 7 | 6 |
| 0 | 4 | 0 | 7 |

10+2 - 8 = 12-8 = 4

407 የመጨረሻ መስመሩን መፃፍ፡፡

**መልመጃ ለ**

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመተንተን መልሱ፡፡

ሀ. 6786 - 4362 ለ. 8760 - 2084

2. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ቁልቁል ቀንሱ፡፡

ሀ. $\begin{array}{r} 9740 \\ -\ 2370 \\ \hline \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 5632 \\ -\ 1248 \\ \hline \end{array}$ ሐ. $\begin{array}{r} 7860 \\ -\ 4358 \\ \hline \end{array}$ መ. $\begin{array}{r} 8900 \\ -\ 4300 \\ \hline \end{array}$

## 2.3 ሙሉ ቁጥሮችን መደመር እና መቀነስ የያዙ የቃላት ፕሮብሌሞች

**የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት**

- ሙሉ ቁጥሮችን በመጠቀም ተግባራዊ ፕሮብሌሞችን መፍታት

ማስታወሻ፡- የቃላት ፕሮብሌሞች መፍትሄ ለመፈለግ መጀመሪያ ፕሮብሌሙን ደጋግሞ ማንበብና መረዳት፤ በመቀጠል የተሰጠውን እና የሚፈለገውን ለይቶ ማወቅ፤ በስተመጨረሻ መፍትሔውን ማግኘት

ምሳሌ ሀ

1. በአንድ ት/ቤት ውስጥ 890 ወንድ እና 950 ሴት ተማሪዎች ቢኖሩ::

ሀ. አጠቃላይ የተማሪዎች ብዛት ስንት ነው?

ለ. ሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች በስንት ይበልጣሉ?

2. በረከት ከገዛቸው 9000 እንቁላሎች 250 እንቁላሎች ቢሰበሩበት ስንት ያልተሰበሩ እንቁላሎች ይቀሩታል?

መፍትሔ

ሀ. የሴት ተማሪዎች ብዛት=950

የወንድ ተማሪዎች ብዛት= 890

$$\begin{array}{r} 890 \text{ ተማሪ} \\ +\ 950 \text{ ተማሪ} \\ \hline 1840 \text{ ተማሪ} \end{array}$$

ስለዚህ ጠቅላላ ያለው ተማሪ ብዛት 1840 ይሆናል

ለ. የሴት ተማሪዎች ከወንድ ተማሪዎች በስንት እንደሚበልጡ ለማወቅ መቀነስ ይሆናል ::

$$\begin{array}{r} 950 \\ -\ 890 \\ \hline 60 \end{array}$$

ስለዚህ በ60 ይበልጣሉ

2. በረከት ከገዛቸው 9000 እንቁላሎች ውስጥ 250 ሲበላሹ፤ ያልተበላሹ እንቁላሎች ብዛት ለማግኘት መቀነስ ይሆናል::

$$\begin{array}{r} 9000 \\ -\ 250 \\ \hline 8750 \end{array}$$

ስለዚህ 8750 ያልተበላሹ እንቁላሎች ይቀራሉ

**ማስታወሻ**

ሁለት ሙሉ ቁጥሮችን በመቀነስ የሚገኘውን መልስ በመደመር ማረጋገጥ ይቻላል::

ሁለት ሙሉ ቁጥሮችን በመደመር የተገኘ ዋጋ በመቀነስ ማረጋገጥ ይቻላል::

ምሳሌ ለ : የሚከተሉትን አስሉ እና አረጋግጡ::

ሀ. 458 - 46 ለ. 5640 - 430

መፍትሔ: ቁልቁል መቀነስ የተሻለ እና ቀላሉ መንገድ ስለሆነ

ሀ. $\begin{array}{r} 458 \\ -\ 46 \\ \hline 412 \end{array}$ ማረጋገጫ ዋና = ተቀናሽ + ልዩነት $\begin{array}{r} 412 \\ +\ 46 \\ \hline 458 \end{array}$

ለ. $\begin{array}{r} 5640 \\ -\ 430 \\ \hline 5210 \end{array}$ ማረጋገጫ ዋና = ተቀናሽ + ልዩነት $\begin{array}{r} 5210 \\ +\ 430 \\ \hline 5640 \end{array}$

## መልመጃ ሀ

1. የሚከተሉትን አስሉ እና አረጋግጡ፡፡

ሀ. $\begin{array}{r} 678 \\ -\ 560 \\ \hline \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 1240 \\ -\ 450 \\ \hline \end{array}$ ሐ. $\begin{array}{r} 3460 \\ +\ 2400 \\ \hline \end{array}$ መ. $\begin{array}{r} 6890 \\ +\ 234 \\ \hline \end{array}$

2. በኢትዮጵያ ሃምሌ 22 / 2013 ዓ.ም በ24 ሰዓት ለ 6803 ሰዎች በተደረገ የላብራቶሪ ምርመራ 467 ላይ የኮሮና ቫይረስ እንዳለባቸው ተረጋገጠ፡፡ ከተመረመሩ ሰዎች መካከል በኮሮና ቫይረስ ያልተያዙ ሰዎች ብዛት ስንት ነው?

3. በቤተ መፅሐፍት ውስጥ ካሉ የመፅሐፍት መደርደሪያዎች 1500 የሒሳብ ፣ 2000 የአማረኛ እና 800 እንግሊዘኛ መፅሐፍት ቢኖሩ በመፅሐፍ መደርደሪያው ያሉት አጠቃላይ መፅሐፍት ብዛት ስንት ነው?

4. ተማሪዎች 600 የብርቱካን ችግኞች እና 3400 የአቮካዶ ችግኞች ቢተክሉ ተማሪዎች በአጠቃላይ ስንት ችግኞችን ተከሉ?





5. መስከረም 2011 ዓ.ም በመስቀል አደባባይ የመስቀል በዓልን ለማክበር ከተገኙ 9000 የውጭ ጎብኝዎች መካከል 3200 ጎብኝዎች የተለያዩ የሀገር ባህል ልብሶች የለበሱ ነበሩ፡፡ የሀገር ባህል ልብስ ያለበሱ ጎብኝዎች ብዛት ስንት ነበሩ?

## ምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ

- ሁለት የ1000 ብዜቶችን በቀላሉ ለመደመር የሁለቱን ቁጥሮች በሺ ቤት የሚገኙ ሆሄያቶችን ደምሮ ከተገኘው ውጤት ላይ ሦስት ዜሮዎችን በስተቀኝ መጨመር ነው፡፡
- በአለኝታ ስንደምር ከቁጥሮቹ ከአንድ ቤት በመጀመር በቅደም ተከተል በቤት በቤታቸው የሚገኙትን ደምሮ አለኝ የሚለውን ከሚቀጥለው የቁጥር ቤት ሆሄያትጋር መደመር ነው፡፡
- ድምራቸው 10000 የማይበልጡትን ሁለት ሙሉ ቁጥሮች በመደመር የሚገኝ መልስ በመቀነስ ማረጋገጥ ሲሆን በመቀነስ የሚገኝ መልስ በመደመር ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ መልመጃ

1) ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ውስጥ የ567 እና 6789 ልዩነት የሆነው የቱ ነው? ሀ.7356 ለ.6222 ሐ.6890 መ. 0

2) 5300+200= ____.

ሀ. 5500 ለ.5100 ሐ. 5700 መ.7300

3) 689 - 342=__________

ሀ.400 ለ.476 ሐ.47 መ. 347

4) 40+700+70=__________

ሀ.810 ለ.710 ሐ.144 መ.81

5) የሚከተሉትን አስሉ፡፡

ሀ. $\begin{array}{r} 30 \\ +\ 521 \\ \hline \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 7430 \\ +\ 50 \\ \hline \end{array}$ ሐ. $\begin{array}{r} 23 \\ -\ 500 \\ \hline \end{array}$ መ. $\begin{array}{r} 6721 \\ -\ 5280 \\ \hline \end{array}$ ሠ. $\begin{array}{r} 4721 \\ +\ 6580 \\ \hline \end{array}$

6) ሰንጠረዡን አሟሉ፡፡

| ዋና | ተቀናሽ | ልዩነት |
|---|---|---|
| 5912 | 5678 | 234 |
| 9800 | | 450 |
| | 1200 | 5500 |
| 7200 | | 660 |
| | 3004 | 3888 |

7) የሁለት ሙሉ ቁጥሮች ልዩነት እንዴት እናገኛለን?

8) ማርታ 168 ገፅ ያለው መፅሀፍ አላት፡፡ 142 ገፅ ብታነብ ስንት ገፅ ይቀራታል?

9) የትልቁ ባለሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥር እና የትንሹ ባለሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥር ልዩነቱ ስንት ነው?

# ምዕራፍ 3 እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት

የመማር ማስተማር ውጤቶች፣ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ ፣

- እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ያባዛሉ፣ የ100 ብዜቶችንም ትገነዘባላችሁ::
- እስከ 1000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች ማባዛት ተግባራዊ ያደረገ ፕሮብሌሞችን ትፈታላችሁ::

## 3.1 የ10 እና የ100 ብዜቶችን በባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮች ማባዛት

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት፣

- የ10 እናየ100 ብዜቶችን በባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮች ማባዛት

መግቢያ

በምዕራፍ አንድ እንደተማራችሁት አንድ ሙሉ ቁጥር የመቶ ብዜት የሚባለው ቢያንስ የሙሉ ቁጥሩ የአንድ ቤት ሆሄና የአስር ቤት ሆሄ ዜሮ ሲሆኑ ነው:: ወይም ቢያንስ የመጨረሻ ሁለት ሆሄቻው ዜሮ የሆኑ ሙሉ ቁጥሮች የ100 ብዜት ናቸው:: ለምሳሌ 100፣200፣300፣400፣500፣600፣ 700፣ 800 እና 1100 ከ100 ብዜት ሙሉ ቁጥሮች የተወሰኑት ናቸው::

**ተግባር ሀ**

1. በ0 እና1000 መካከል የሚገኙ የ100 ብዜቶችን በቅደም ተከተል ዘርዝሩ::
2. ከሚከተሉት ቁጥሮች የ10 ብዜት የሆኑትን ለዩ ::

   ሀ. 2390 ለ. 1500 ሐ. 3004 መ. 7070 ሠ. 9900

3. የሚከተሉት ቁጥሮች የ10 እና የ100 ብዜት ፈልጉ::

   ሀ. 50 ለ. 34 ሐ. 49 መ. 58

ማስታወሻ:-የተመሳሳይ ቁጥሮች መደመር ድግግሞሽ ማባዛት ነው::

**ምሳሌ ሀ**

ሀ. 100+100+100+100 = 400

4×100= 400

ለ. 1000+1000+1000+1000+1000=5000

5×1000=5000

ሐ. 10+10+10+10 = 40

4×10 = 40

መ. 200+200+200=600

3×200=600

ሠ. 0+0+0+0+0+0+0 = 0 = 7×0 =0 ይህ የሚያሳየው ማንኛውም ቁጥር በዜሮ ስናባዛ ውጤቱ ምንጊዜም ዜሮ ነው ::

ማስታወሻ

የ100 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮች ሲባዙ

- ከተሰጠው የ100 ብዜት ቁጥር ዜሮ ያልሆነውን ሆሄ ከባለ አንድ ሆሄው ጋር አባዝቶ ካገኘነው ውጤት ላይ በስተቀኝ የነበሩትን ዜሮዎች መፃፍ ነው::

የ10 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ቁጥሮች ሲባዙ

- ከተሰጠው የ10 ብዜት ቁጥር ዜሮ ያልሆነውን ሆሄ ከባለ አንድ ሆሄው ጋር አባዝቶ ካገኘነው ውጤት ላይ በስተቀኝ የነበሩትን ዜሮዎች መፃፍ ነው::

**ምሳሌ ሐ**

የሚከተሉትን አባዙ::

ሀ . 300×2 ለ. 200×4 ሐ.1200×3

መ.320×6 ሠ. 130×8

መፍትሔ

ሀ . 300×2 ይህን ማባዛት ለመስራት 3 በ 2 አባዝቶ ከውጤቱ በስተቀኝ ሁለት ዜሮዎችን መፃፍ ስለሆነ 3×2 = 6 ስለዚህ 300×2 =600

ለ. 200×4 ይህን ማባዛት ለመስራት 2 በ 4 አባዝቶ ከውጤቱ በስተቀኝ ሁለት ዜሮዎችን መፃፍ ስለሆነ 2×4 =8 ስለዚህ 200×4 =800

ሐ. 1200×3 ዜሮ ያልሆነው ሆሄ 12×3=36 ስለዚህ 1200×3=3600

መ. 320×6 ዜሮ ያልሆነው ሆሄ 32×6=192 ስለዚህ 320×6=1920

ሠ. 1300×8 ዜሮ ያልሆነው ሆሄ 13×8=94 ስለዚህ 1300×8=9400

**መልመጃ ሀ**

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች አባዙ፡፡

ሀ. 4×100 ለ.3× 300 ሐ. 6×100 መ. 5×200

ሠ. 8×100 ረ. 500×4 ሸ. 800×0 ቀ. 1200×2

2.ለሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች የ10 እና የ100 ብዜቶች ፈልጉ::

ሀ. 23 ለ.120 ሐ.25 መ.10

## 3.2 የማባዛት ውጤታቸው ከ1000 ያነሱ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ማባዛት

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት

- የማባዛት ውጤታቸው ከ1000 ያነሱ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ማባዛት

**ተግባር ለ**

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አባዙ::

   ሀ. 212×4    ለ. 43×8    ሐ.355× 2

   መ.64×3    ሠ. 8×49    ረ. 10×51

## *ሀ. የማባዛት ውጤታቸው እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማባዛት*

**ማስታወሻ**

የማባዛት ውጤታቸው እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች ያለአለኝታ ከባለአንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር ጋር ሲባዙ፤ መጀመሪያ የአንድ ቤት ሆሄን አባዝቶ የሚገኘውን ውጤት በአንድ ቤት መፃፍ፤ ቀጥሎ የ10 ቤት ሆሄን አባዝቶ ውጤቱን በ10 ቤት መፃፍ፤በመጨረሻ የመቶ ቤት ሆሄ አባዝቶ በ100 ቤት እንፅፋለን::

<u>ምሳሌ መ</u> ቁልቁል ማባዛት

ሀ.

  234
 X 2

አሰራር

| የ100 ቤት | የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|---|
| 2 | 3 | 4<br>X2 |
| 4 | 6 | 8 |

ከአንድ ቤት ካለው 4 ስንጀምር 4x2=8 8ን በአንድ ቤት እንፅፋለን:: በመቀጠል የአስር ቤት ካለው 3x2=6 6ን ደግሞ በአስር ቤት እንፅፋለን:: በመጨረሻ የ100 ቤት 2x2=4 4ን በመቶ ቤት እንፅፋለን ::ስለዚህ 234x2=468 ይሆናል::

ለ. 231

X 3

| የ100 ቤት | የ10 ቤት | የ10 ቤት |
|---|---|---|
| 2 | 3 | 1 |
| | | X3 |
| 4 | 9 | 3 |

ስለዚህ 231x3=493

## መልመጃ ለ

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ስንጠረዥ በመጠቀም አባዙ፡፡

ሀ. $\begin{array}{r}142\\ \times\ 2\\ \hline\end{array}$ ለ. $\begin{array}{r}112\\ \times\ 4\\ \hline\end{array}$ ሐ. $\begin{array}{r}434\\ \times\ 2\\ \hline\end{array}$ መ. $\begin{array}{r}100\\ \times\ 9\\ \hline\end{array}$ ሠ. $\begin{array}{r}104\\ \times\ 2\\ \hline\end{array}$

2. ትንሹ ባለሦስት ሆሄ ሙሉ ቁጥር በ6 ሲባዛ ስንት ይሆናል?

3. ማንኛውም ሙሉ ቁጥር በዜሮ ስናባዛ ውጤቱ እራሱ ቁጥሩነው፡፡

ሀ . እውነት ለ. ሀሰት

**ማስታወሻ**

የማባዛት ውጤታቸው ከ1000 ያነሱ ሙሉ ቁጥሮች በባለአንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር በአለኝታ ሲባዙ

- የአንድ ቤት ሆሄን አባዝቶ የሚገኘውን ውጤት የአንድ ቤት ሆሄውን በአንድ ቤት መፃፍና የ10 ቤት የሆነውን አለኝ እንላለን::
- ቀጥሎ የ 10 ቤት ሆሄን አባዝቶ ውጤቱን አለኝ ካልነው ቁጥር ጋር እንደምር እና የ10 ቤት ሆሄውን በ10 ቤት መፃፍ የ100 ቤት ሆሄውን አለኝ እንላለን::
- በመጨረሻ የመቶ ቤት ሆሄውን አባዝተን አለኝ ካልነው ቁጥር ጋር እንደምራለን ውጤቱንም በመቶ ቤት እና ከአስር በላይ ከሆነ በሺ ቤት እንፅፋለን ::

ምሳሌ ሠ

ሀ. 136

X 6

| የ100 ቤት | የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|---|
| 2 | 3 | |
| 1 | 3 | 6 |
| | | X6 |
| 8 | 1 | 6 |

**አሰራር**

1ኛ የአንድ ቤት ካለው 6 በመጀመር 6x6=36 ይሆናል : : 6ን በአንድ ቤት ፅፈን 3 በአስር ቤት ሳጥን አለኝ በማለት እንፅፋለን::

2ኛ የአስር ቤት 3x6=18 አለኝ ካልነው 3 ጋር እንደምራለን:: 18+3=21:: 1ን በአስር ቤት ፅፈን 2ን በመቶ ቤት ሳጥን አለኝ በማለት እንፅፋለን::

3ኛ የመቶ 1x6=6 አለኝ ካልነው 2 ጋር እንደምራለን::6+2=8:: 8ን በመቶ ቤት እንፅፋለን::

ስለዚህ

$$\begin{array}{r} 136 \\ \underline{\times 6} \\ 816 \end{array}$$

ለ. 734

X 4

| የ100 ቤት | የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|---|
| 1 | 1 | |
| 7 | 3 | 4 |
| | | X4 |
| 29 | 3 | 6 |

አሰራር

1ኛ የአንድ ቤት ካለው 4 በመጀመር 4x4=16 ይሆናል : : 6ን በአንድ ቤት ፅፈን በአስር ቤት ሳጥን አለኝ በማለት እንፅፋለን::

2ኛ የአስር ቤት 3x4=12 አለኝ ካልነው 1 ጋር እንደምራለን:: 12+1=13:: 3ን በአስር ቤት ፅፈን 1ን በመቶ ቤት ሳጥን አለኝ በማለት እንፅፋለን::

3ኛ የመቶ 7x4=28 አለኝ ካልነው 1 ጋር እንደምራለን::28+1=29:: 29ን በመቶ ቤት እንፅፋለን::

ስለዚህ
```
  734
X   4
-----
 2936
```
ይሆናል::

ሐ.
```
  824
X   5
```

| የ100 ቤት | የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|---|
| 1 | 2 | |
| 8 | 2 | 4 |
| | | X5 |
| 41 | 2 | 0 |

አሰራር

1ኛ የአንድ ቤት ካለው 4 በመጀመር 4x5=20 ይሆናል : : 0ን በአንድ ቤት ፅፈን 2 በአስር ቤት ሳጥን አለኝ በማለት እንፅፋለን::

2ኛ የአስር ቤት 2x5=10 አለኝ ካልነው 2 ጋር እንደምራለን:: 10+2=12:: 2ን በአስር ቤት ፅፈን 1ን በመቶ ቤት ሳጥን አለኝ በማለት እንፅፋለን::

3ኛ የመቶ 8x5=40 አለኝ ካልነው 1 ጋር እንደምራለን::40+1=41:: 41ን በመቶ ቤት እንፅፋለን::

ስለዚህ
```
  824
X   5
-----
 4120
```
ይሆናል::

## መልመጃ ሐ

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ስንጠረዥ በመጠቀም አባዙ፡፡

ሀ. $\begin{array}{r}142\\ \times\ 5\\ \hline\end{array}$ ለ. $\begin{array}{r}247\\ \times\ 2\\ \hline\end{array}$ ሐ. $\begin{array}{r}108\\ \times\ 4\\ \hline\end{array}$

መ. $\begin{array}{r}112\\ \times\ 6\\ \hline\end{array}$ ሠ. $\begin{array}{r}102\\ \times\ 9\\ \hline\end{array}$ ረ. $\begin{array}{r}682\\ \times\ 8\\ \hline\end{array}$

## 3.3 እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት መሰረት ያደረጉ የቃላት ፕሮብሌሞች

**ተግባር መ**

1. ዮሃንስ 35 የአፍ እና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭንብል፤ እያንዳንዱን በ8 ብር ቢሸጣቸው ምን ያክል ብር ያገኛል?
2. አንድ የእግር ኳስ ቡድን 4 ኳሶችን ለመግዛት ቢፈልግና የእያንዳንዱ ዋጋ 232 ብር ቢሆን አጠቃላይ ኳሱን ለመግዛት ስንት ብር ያስፈልጋቸዋል?
3. ሁሉም የክፍላችሁ ተማሪዎች እያንዳንዳችሁ አምስት አምስት መፅሀፍት ብትገዙ፣በአጠቃላይ የሁላችሁም መፅሀፍት ብዛት ስንት ይሆናል?

<u>ምሳሌ ሸ</u>

1. ዑስማን፣ናትናኤል፣ሃዊ፣ሩት እና ቴዎድሮስ ለአባይ ግድብ የሚሆን እያንዳንዳቸው 160 ብር ቢያዋጡ አጠቃላይ ምን ያክል ገንዘብ ይሰበስባሉ?
2. አንድ ባለሃብት ለ4 ት/ቤቶች ረዳት ለሌላቸው ተማሪዎች የሚሆን ለእያንዳንዳቸው ት/ቤቶች 200 ደብተሮች ቢሰጡ በአጠቃላይ ባለሃብቱ ስንት ደብተሮችን ሰጡ?
3. አና በየቀኑ 2 ኩባያ ወተት ብትጠጣ ፣በ14 ቀን ምን ያህል ኩባያ ወተት ትጠጣለች?

<u>መፍትሔ</u>

1. እያንዳንዱ ያዋጡት ገንዘብ=160

   ብዛታቸው ደግሞ =5

   ስለዚህ አጠቃላይ የተዋጣው ገንዘብ ብዛት = 5×160ብር = 800ብር

2. የደብተሮች ብዛት=200

   የት/ቤቶች ብዛት =4

   ስለዚህ አጠቃላይ የደብተሮች ብዛት = 4×200 = 800

3. አና በየቀኑ 2 ኩባያ ወተት ብትጠጣ

   የቀኖች ብዛት =14

   አጠቃላይ በ 14 ቀን ውስጥ የጠጣችው ወተት = 14×2 = 28 ኩባያ

**መልመጃ መ**

1 .8 ልጆች እያንዳንዳቸው 4 የመጫወቻ ፊኛዎች ቢኖራቸው፣ የ8ቱ ልጆች አጠቃላይ የፊኛዎች ብዛት ስንት ነው?

2. በአንድ የ3ኛ ክፍል ውስጥ 34 ተማሪዎች ቢኖሩ እያንዳንዳቸው ለበጎ አድራጎት የሚውል 6ብር ቢያዋጡ አጠቃላይ ምን ያክል ገንዘብ ይሰበስባሉ?

3. 7 የግር ኳስ ቡድኖች እያንዳንዳቸው 18 ተጫዋቾች አሏቸው:: አጠቃላይ የተጫዋቾች ብዛት ስንት ይሆናል?

### ምዕራፍ ሦስት ማጠቃለያ

- የ100 ብዜት የሆኑ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ስናባዛ ከተሰጠው የ100 ብዜት ቁጥር ዜሮ ያልሆነውን ሆሄ ከባለ አንድ ሆሄው ጋር አባዝቶ ካገኘነው ውጤት ላይ በስተቀኝ የተቀሩትን ዜሮዎችን መፃፍ ነው፡፡
- ባለሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ያለአለኝታ ከባለአንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር ጋር ሲባዙ መጀመሪያ የአንድ ቤት ሆሄን አባዝቶ የሚገኘውን ውጤት በአንድ ቤት መፃፍ፡፡ቀጥሎ የ 10 ቤት ሆሄን አባዝቶ ውጤቱን በ10 ቤት ወይም በ10 እና በ100 ቤቶች መፃፍ
- ባለሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች በባለአንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር በአለኝታ ሲባዙ፤ የአንድ ቤት ሆሄን አባዝቶ የሚገኘውን ውጤት የአንድ ቤት ሆሄውን በአንድ ቤት መፃፍና የ10 ቤት የሆነውን ሆሄ በ10 ቤት መፃፍ፡፡ ቀጥሎ የ 10 ቤት ሆሄን አባዝቶ ውጤቱን የ10 ቤት ሆሄውን በ10 ቤት መፃፍ የ100 ቤት ሆሄውን በ100 ቤት መፃፍ፡፡ በየቤቱ የተፃፉትን ቁጥሮች ቁልቁል በየተጻፉበት ቤት ደምሮ ውጤቱን መፃፍ፡፡

## ምዕራፍ ሦስት ማጠቃለያ መልመጃ

ለሚከተሉት ጥያዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

1. ከሚከተሉት ውስጥ የ100 ብዜት የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. 680 ለ. 405 ሐ. 700 መ. ሁሉም

2. ከሚከተሉትውስጥ 100×3 ጋር እኩል የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. 3000 ለ. 300 ሐ. 30 መ. 100

3. የሚከተሉትን ቁጥሮች ሰንጠረዥ በመጠቀም አባዙ፡፡

   ሀ. $\begin{array}{r}132\\ \times\ \ \ 3\\ \hline\end{array}$ ለ. $\begin{array}{r}221\\ \times\ \ \ 4\\ \hline\end{array}$ ሐ. $\begin{array}{r}254\\ \times\ \ \ 8\\ \hline\end{array}$ መ. $\begin{array}{r}822\\ \times\ \ \ 3\\ \hline\end{array}$

4. በተማሪዎች መማሪያ ክፍል ውስጥ 20 አግዳሚ ወንበሮች ቢኖሩ፣በእያንዳንዱ አግዳሚ ወንበር ላይ 3 ተማሪዎች ቢቀመጡ፣ በሁሉም አግዳሚ ወንበሮች ላይ ስንት ተማሪዎች ሊቀመጡ ይችላሉ?

5. የአንድ ፓርክ ዙሪያ 850ሜትር ቢሆን፣ልዑል 4 ዙር ቢሮጥ፣አጠቃላይ ስንት ሜትር ሮጠ?

# ምዕራፍ 4 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማካፈል

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኂላ ተማሪዎች:

- እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ 1፣2፣3፣4፣5፣6፣7፣8፣9 እና10 በቀሪና ያለቀሪ ማካፈልን ትረዳላችሁ::
- እስከ 100 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች ማካፈልን ተግባራዊ ያደረገ ፕሮብሌሞች ትፈታላችሁ::

መግቢያ

ማካፈል ከአራቱ መሰረታዊ የሒሳብ ስሌቶች አንዱ ሲሆን፤የቀሩት ሶስቱ ደግሞ መደመር ፣መቀነስ እና ማባዛት ናቸው::ማካፈል ማለት ነገሮችን እኩል መከፋፈል ማለት ነው::የማካፈል ዋናው አላማ የተለያየ ቡድን እንዴት ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እኩል መከፋፈል እንዳለበት የሚያሳይ አጭር ሒሳባዊ ስሌት ነው::የማካፈልን ፅንስ ሀሳብ በመተግበር በአካባቢያችሁ የምታገኙትን ነገር ለምሳሌ፡ ስምንት ዳቦ ለአራት እኩል ልጆች ቢካፈል እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ዳቦ ይደርሳቸዋል:: ይህም በሂሳባዊ አገላለፅ 8÷4 = 2 እንለዋለን::

## 4.1 እኩል ክፍፍል እና ማካፈልን በተደጋጋሚ መቀነስ መስራት

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃቶች

- እኩል ክፍፍል እና ማካፈልን በተደጋጋሚ መቀነስ መስራት

ተግባር ሀ

1. ሀ. ከታች ካለው ስዕል ያሉትን ብዮች ለ 2 ተማሪ እኩል ብናካፍላቸው ስንት ስንት ይደርሳቸዋል?



ለ. 8 ÷2 = ____

ምሳሌ ሀ

1. አንድ እናት 12 ቸኮሌቶችን ገዝታ ለ4 ልጆቿ እኩል ብታካፍላቸው፤ ለእያንዳንዳቸው ስንት ስንት ቸኮሌት ይደርሳቸዋል?





ማስታወሻ

ማካፈል ማለት የመቀነስ ድግግሞሽ አጭር ስሌት ነው፡፡

<u>ምሳሌ ለ</u>

ሀ. 30 ÷ 5 = ————ድርሻውን በመቀነስ ፈልጉ::

መፍትሔ : - ከ30 ላይ በተደጋጋሚ 5 መቀነስ::መቀነስ የሚሰራው 30 እስከ ሚያልቅ ድረስ ይቀጥላል::

ድርሻውን ለማወቅ ስንት ጊዜ እንደቀነስን ቁጠሩ::

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 30 | 25 | 20 | 15 | 10 | 5 |
| -5 | -5 | -5 | -5 | -5 | -5 |
| 25 | 20 | 15 | 10 | 5 | 0 |
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 |

5 ስንት ጊዜ ቀነስን?

ከላይ እንደምንመለከተው ከ30 ፤5ን 6 ጊዜ በተደጋጋሚ ስንቀንስ 0 ላይ ደረስን ::

ስለዚህ 30 ÷ 5 =6

ለ. 32 ÷ 8 = ————ድርሻውን በመቀነስ ፈልጉ::

| | | | |
|---|---|---|---|
| 32 | 24 | 16 | 8 |
| -8 | -8 | -8 | -8 |
| 24 | 16 | 8 | 0 |

8 ስንት ጊዜ ከ32 ቀነስን?

ከላይ እንደምንመለከተው ከ32 ፤8ን 4 ጊዜ በተደጋጋሚ ስንቀንስ 0 ላይ ደረስን ::

ስለዚህ 32 ÷ 8 =4

## መልመጃ ሀ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መቀነስ በመጠቀም ድርሻዎችን ፈልጉ::

ሀ. 48 ÷ 8 = ____ ለ. 33 ÷ 3 =______ ሐ 56÷7=______

መ. 24 ÷4 = ____ ሠ. 84÷6 ___ ረ. 75÷5 = ___

2. ፋጡማ 5 ፓኬት እርሳሶች አሏት፤ እያንዳንዱ ፓኬት 12 እርሳሶችን ቢይዝ፣ በአጠቃላይ ፋጡማ ያሏት እርሳሶች ብዛት ስንት ናቸው?

## 4.2 እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ2 ማካፈል

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት

- እስከ 20 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ2 ማካፈል

### ተግባር ሀ

1. ሀ. ከታች ካለው ስዕል ያሉትን ብዮች ለ 2 ተማሪ እኩል ብናካፍላቸው ስንት ስንት ይደርሳቸዋል?



ለ. 8 ÷2 = ____

2. ሀ.ከታች ካለው ስዕል ያሉትን ቲማቲሞች ለ2 ተማሪ እኩል ብናካፍላቸው ስንት ስንት ይደርሳቸዋል?

ለ 10 ÷2 =______



**ምሳሌ ሀ**

1. አለሙ 2 እርሳሶችን ለሁለት ጓደኞቹ እኩል ቢያካፍላቸው____ይደርሳቸዋል::

2. መምህር አልማዝ 4 አዲስ ደብተሮችን እኩል ለ2 ተማሪዎች ብታካፍላቸው ለእያንዳንዳቸው _____ደብተሮች ይደርሳቸዋል::

3. ለማ 6 እሽግ ብስኩቶችን ገዝቶ ለ 2 ልጆቹ እኩል ቢያካፍላቸው ስንት ስንት ብስኩት ይደርሳቸዋል?

<u>መፍትሄ</u>

ማካፈል ማለት ከላይ እንዳየነው ደጋግሞ መቀነስ ማለትነው:: ስለሆነም

1. 2 ÷ 2 = 1 ምክንያቱም ሁለቱን እርሳሶች ለሁለት ሲያካፍላቸው አንድ አንድ ይደርሳቸዋል::

2. 4÷2 = 2 ምክንያቱም 4 ደብተሮችን ለ2 ተማሪዎች ስታካፍል ሁለት ሁለት ይደርሳቸዋል::

3. 6÷2 =3 ምክንያቱም 6 ብስኩቶችን ለ2 ልጆቹ ሲያካፍል ሶስት ሶስት ይደርሳቸዋል::

<u>ምሳሌ ለ</u>

የሚከተሉትን ተካፋይ አካፋይና ድርሻ በማለት ለዩ::

ሀ. 8÷2 =4    ለ. 10÷2 = 5    ሐ. 12 ÷ 2 = 6

መፍትሄ

| ሀ. 8 | ÷ 2 | = 4 | ለ. 10 | ÷ 2 | = 5 | ሐ. 12 | ÷ 2 | = 6 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ↑ | ↑ | ↑ | ↑ | ↑ | ↑ | ↑ | ↑ | ↑ |
| ተካፋይ | አካፋይ | ድርሻ | ተካፋይ | አካፋይ | ድርሻ | ተካፋይ | አካፋይ | ድርሻ |

**ተግባር ለ**

1. 5 እርሳሶችን ለ2 ልጆች እኩል ቢካፈሉ ለእያንዳንዳቸው ስንት ስንት እርሳሶች ይደርሳቸዋል?

2. አንድ የግብርና ተቋም 13 በጎችን ለ2 ግለሰቦች እኩል ቢያካፍል፤

ሀ. ግለሰቦቹ ስንት ስንት በጎች ይደርሳቸዋል?

ለ. ሳይካፈሉት የሚቀሩ በጎች ስንት ናቸው?

ምሳሌ መ 1. ናታን እና ቤተልሄም የኢክራም የክፍል ጓደኞች ናቸው:: ኢክራም 7 ቸኮሌት ገዝታ ለናታንና ቤተልሄም እኩል ብታካፍላቸው፤

ሀ. እያንዳንዳቸው ስንት ስንት ቸኮሌት ይደርሳቸዋል?

ለ. ሳይካፈሉት የሚቀር ስንት ቸኮሌት አለ?

2. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች በቀሪ አካፍሉ::

ሀ. 3÷2= __ ለ. 9÷2= __ ሐ. 15 ÷2=___ መ. 17÷2=___

መፍትሔ:-

1·ሀ. ናታን እና ቤተልሄም እያንዳንዳቸው 3 ቸኮሌት ደርሷቸው 1ቸኮሌት ትርፍ ይቀራል

ለ. 1 ቸኮሌት ይቀራል ምክንያቱም አንዷን ለሁለት እኩል መክፈል ስለሚያስቸግር:: የተረፈው 1 ቸኮሌት ቀሪ ይባላል::

ይህ በሌላ አገላለፅ 7÷2 = 3 ደርሶ 1 ቀሪ ይሆናል

| 7 | = | 2 | × | 3 | + | 1 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ↑ | | ↑ | | ↑ | | ↑ |
| ተካፋይ | = | አካፋይ | × | ድርሻ | + | ቀሪ |

2. ሀ 3÷2 = 1 ደርሶ 1 ቀሪ ይሆናል ለ. 9÷2 = 4 ደርሶ 1 ቀሪ ይሆናል

ሐ. 15÷2 = 7 ደርሶ 1 ቀሪ ይሆናል መ. 17÷2 = 8 ደርሶ 1 ቀሪ ይሆናል

**ማስታወሻ:**

አንድ ሙሉ ቁጥር ለ2 ሲካፈል የሙሉ ቁጥሩ የአንድ ቤት ሆሄ 0፣2፣4፣6 ወይም 8 ከሆነ ቁጥሩ ያለ ቀሪ ይካፈላል:: አንድ ሙሉ ቁጥር ለ 2 ሲካፈል ቀሪ ካለው ቀሪው 1 ነው::

## መልመጃ ሀ

1. የሚከተሉትን ተካፋይ አካፋይና ድርሻ በማለት ለዩ፡፡

ሀ. 12÷2 = 6  ለ. 14÷2 = 7  ሐ. 16÷2 = 8  መ. 18÷2 =9

2. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍላችሁ ቀሪውን ፈልጉ፡፡

ሀ. 13÷2  ለ. 11÷2  ሐ. 19÷2  መ. 15÷2

## 4.3 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ2 እና በ10 ማካፈል

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት

- እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ2 እና በ10 ማካፈል

**ተግባር ሀ**

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ፡፡

ሀ. 28÷ 2  ለ. 79 ÷ 2  ሐ. 40÷ 10  መ. 92÷ 10

2. አዳነ 90 የማንጎ ችግኞች ለ10 አርሶ አደሮች ቢያከፋፍል እያንዳንዱ አርሶ አደር ስንት የማንጎ ችግኝ ይደርሳቸዋል?

**ምሳሌ ሀ**

1. አቶ መለሰ 26 ብስኩት ጋግሮ በ2 ሳህን እኩል ክፍሎ ማስቀመጥ ቢፈልግ ከ እያንዳንዱ ሳህን ላይ ምንያክል ብስኩት ማስቀመጥ ይችላል?

**መፍትሔ**

ከእያንዳንዱ ሳህን ላይ 13 ብስኩቶች ማስቀመጥ አለበት፡፡

ይህ ማለት 26÷2 = 13 ምክንያቱም 2×13 = 26 ስለሆነ፡፡

**ምሳሌ ለ**

የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ፡፡

ሀ. 34 ÷ 2=__  ለ. 78÷2 =__

መፍትሔ፡

ሀ

ከግራ በኩል ካለው 3 እንጀምራለን:: 3ን ለ2 እናካፍላለን::ድርሻውንም 1 ሲሆን ከ10 ቤት በላይ ባለው ቁጥር ትክክል እንፅፋለን::

ከዚያም ድርሻውን በ2 አባዝቶ በ3 ስር እንፅፋለን:: ከ3 ላይ 2ን እንቀንሳለን::1 ይሆናል::

```
   17
2 |34
   2
   14
   14
    0
```

በመቀጠል ከ1 ጎን 4 በመፃፍ 14ን እናገኛለን:: 143 ለ2 ስናካፍል 7 ይሆናል:: ከመጀመሪያው ካገኘነው 1 ጎን እንፅፋለን:: በመቀጠልም 7x2=14ን ከመጀመሪያው 14 ስር እንፅፋለን:: ስንቀንስ 0 ይቀራል:: ማካፈሉ አለቀ እንላለን

ስለዚህ 34 ÷2 =17

ለ. 78÷2

ከግራ በኩል ካለው 7 እንጀምራለን:: 7ን ለ2 እናካፍላለን::ድርሻውንም 3 ሲሆን ከ10 ቤት በላይ ባለው ቁጥር ትክክል እንፅፋለን::

ከዚያም ድርሻውን በ2 አባዝተን 2x3=6ን በ7 ስር እንፅፋለን:: ከ7 ላይ 6ን እንቀንሳለን::1 ይሆናል::

```
   39
2 |78
   6
   18
   18
    0
```

በመቀጠል ከ1 ጎን 8 በመፃፍ 18ን እናገኛለን:: 18ን ለ2 ስናካፍል 9 ይሆናል:: ከመጀመሪያው ካገኘነው 2 ጎን እንፅፋለን:: በመቀጠልም 9x2=18ን ከመጀመሪያው 18 ስር እንፅፋለን:: ስንቀንስ 0 ይቀራል:: ማካፈሉ አለቀ እንላለን::

ስለዚህ 78 ÷2 =39

ማስታወሻ

የአንድ ሙሉ ቁጥር የአንድ ቤት ሆሄ 0 ከሆነ ቁጥሩ ያለቀሪ ለ10 ይካፈላል፡፡

ተግባር ለ

1.የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ለ10 አካፍሉ፡፡

ሀ. 80÷ 10   ለ. 70÷ 10   ሐ. 38÷ 10   መ. 54÷10

ማስታወሻ

ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥር ለ10 ሲካፈል የቁጥሩ የአንድ ቤት ሆሄ 0 ከሆነ ቁጥሩ ያለቀሪ መካፈል ሲችል ድርሻውም ከቁጥሩ ከአስር ቤት ሆሄው ጋር እኩል ይሆናል፡፡ ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥር ለ10 ሲካፈል የቁጥሩ የአንድ ቤት ሆሄ ከ 0 የተለየ ከሆነ ቁጥሩ በቀሪ የሚካፈል ሲሆን ቀሪው ከቁጥሩ የአንድ ቤት ሆሄ ጋር እኩል ሲሆን ድርሻው ደግሞ ከቁጥሩ ከአስር ቤት ሆሄው ጋር እኩል ይሆናል፡፡

<u>ምሳሌ ሐ</u>

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ፡፡

ሀ. 60÷ 10   ለ. 49÷ 10

መፍትሔ

ሀ. 60÷ 10 = 6 ምክንያቱም 10× 6 = 60 ወይም የ 60 አንድ ቤት ሆሄ 0 ሲሆን ቁጥሩ ያለቀሪ መካፈል ሲችል ድርሻውም ከ60 የአስር ቤት ሆሄ ማለትም ከ6 ጋር እኩል ይሆናል፡፡

ለ. 49÷ 10 = 4 ደርሶ ቀሪ 9 ምክንያቱም 49 = 10× 4 + 9 ወይም የ49 የአንድ ቤት ሆሄ ከ0 የተለየ ስለሆነ ቁጥሩ በቀሪ የሚካፈል ሲሆን ቀሪው የ49 የአንድ ቤት ሆሄ ማለትም ከ9 ጋር እኩል ሲሆን ድርሻው ደግሞ የ49 የአስር ቤት ሆሄው ማለትም ከ4 ጋር እኩል ይሆናል፡፡

ማስታወሻ

ለ10 ያለቀሪ የሚካፈል ማንኛውም ሙሉ ቁጥር ለ2 ያለቀሪ ይካፈላል:: 0 ለ 2 እና ለ10 ሲካፈል ምንጊዜም ውጤቱ 0 ነው::

መልመጃ ሀ

1. የሚከተሉትን የማካፈል ጥያቄዎች ድርሻ ባዶ ቦታው ላይ ሙሉ::

ሀ. 88÷ 2 =___  ለ. 64÷ 2 =____  ሐ. 30÷10 ____

መ. 10÷ 10 =___  ሠ. 28÷2 =___  ረ. 100÷10=____

2. .የሚከተሉትን የማካፈል ጥያቄዎች ድርሻና ቀሪ አስሉ::

ሀ. 85÷ 2  ለ. 73÷ 2  ሐ. 43 ÷10

መ. 14÷ 10  ሠ. 57÷2  ረ. 94÷10

2. መምህር አሚናት 14 ጣፋጮችን ለተማሪ ሰናይትና ብሩክ እኩል ብታካፍላቸው እያንዳንዳቸው ምን ያክል ጣፋጮች ይደርሳቸዋል?

## 4.4 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ1 ማካፈል

የንዑስ ርዕስ የመማር ብቃት:

- እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ1 ማካፈል

ተግባር ሀ

1. ተናኘ 58 ዶሮዎችን ለዳውድ ብትሰጠው ዳውድ ስንት ዶሮዎች ይኖሩታል?

2. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ለ1 አካፍሉ::

ሀ .5÷ 1  ለ. 70÷ 1  ሐ. 93 ÷ 1

ማስታወሻ

ማንኛውም ሙሉ ቁጥር ለ 1 ሲካፈል እራሱ ሙሉ ቁጥሩን ይሰጣል፡
፡

ምሳሌ ሀ

1. ደረጀ 20 ኩንታል ሩዝ አለው፡፡ ደረጀ 20 ኩንታሉን ለአንድ ወፍጮ ቤት ባለቤት ቢሸጥ የወፍጮ ቤቱ ባለቤት ምን ያክል ኩንታል ሩዝ ከደረጀ ገዛ?

2. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ለ1 አካፍሉ፡፡

ሀ. 48÷ 1 ለ. 90÷ 1 ሐ. 0 ÷1

መፍትሔ

1. 20 ÷1 = 20

2. ሀ. 48÷ 1 =48 ለ. 90÷ 1 = 90 ሐ. 0 ÷1 =0

መልመጃ ሀ

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ለ1 አካፍሉ፡፡

ሀ. 98÷ 1 ለ. 40÷ 1 ሐ. 100 ÷1

## 4.5 እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ3፣4፣5፣6፣7 8እና9 ማካፈል

የንዑስ ርዕስ የመማር ብቃት

- እስከ መቶ ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ3፣4፣5፣6፣7፣8 እና 9 በቀሪ እና ያለ ቀሪ ማካፈል

**ተግባር ሀ**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በቡድን በመሆን ስሩ፡፡

1. 18 እርሳሶችን በክፍል ውስጥ ሰብስቡ፡፡

   ሀ. የሰበሰባችሁትን 18 እርሳሶች እኩል 3 ወንበሮች ላይ ክፈሏቸው፡፡ ከእያንዳንዱ ወንበር ላይ ስንት እርሳሶችን አስቀመጣችሁ?

   ለ. የሰበሰባችሁትን 18 እርሳሶች እኩል 6 ወንበሮች ላይ ክፈሏቸው፡፡ ከእያንዳንዱ ወንበር ላይ ስንት እርሳሶች አስቀመጣችሁ?

   ሐ. የሰበሰባችሁትን 18 እርሳሶች እኩል 4 ወንበሮች ላይ ክፈሏቸው፡፡ከእያንዳንዱ ወንበር ላይ ስንት እርሳሶች አስቀመጣችሁ? ለመመደብ ያስቸገራችሁ ስንት እርሳስ ቀራችሁ?

   መ. የሰበሰባችሁትን 18 እርሳሶች እኩል 5 ወንበሮች ላይ ክፈሏቸው፡፡ከእያንዳንዱ ወንበር ላይ ስንት እርሳሶች አስቀመጣችሁ? ለመመደብ ያስቸገራችሁ ስንት እርሳስ ቀራችሁ?

2. በ80 እና በ100 መካከል ያሉትን የ3 ብዜቶችን ዘርዝሩ፡፡

3 የሚከተሉትን ጥያቄዎች አስሉ፡፡

ሀ. 27÷3 ለ. 81÷3 ሐ. 18÷3 መ. 99÷3

## ሀ. እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ3 ያለ ቀሪ ማካፈል

**ማስታወሻ**

አንድ ሙሉ ቁጥር ያለ ቀሪ ለ3 መካፈል የሚችለው ሙሉ ቁጥሩ የ3 ብዜት ከሆነ ብቻ ነው፡፡

ምሳሌ ሀ አለሙ 6 የአፕል ፍሬዎችን እኩል ለ3 ተማሪዎች ቢያካፍላቸው እያንዳንዱ ተማሪ ስንት የአፕል ፍሬዎች ይደርሳቸዎል?



መፍትሔ :

6÷3 = 2 እያንዳንዳቸው 2 የአፕል ፍሬዎች ይደርሳቸዋል



ምሳሌ ለ

1. እስከ 90 ያሉትን የ3 ብዜት ዘርዝሩ፡፡
2. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ፡፡

ሀ. 3÷3 ለ. 9÷3 ሐ. 12÷3 መ. 0÷3

መፍትሔ 1.

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1×3 =3 | 6×3 =18 | 11×3 =33 | 16×3 =48 | 21×3 =63 | 26×3 =78 |
| 2×3 =6 | 7×3 =21 | 12×3 =36 | 17×3 =51 | 22×3 =66 | 27×3 =81 |
| 3×3 =9 | 8×3 =24 | 13×3 =39 | 18×3 =54 | 23×3 =69 | 28×3 =84 |
| 4×3 =12 | 9×3 =27 | 14×3 =42 | 19×3 =57 | 24×3 =72 | 29×3 =87 |
| 5×3 =15 | 10×3 =30 | 15×3 =45 | 20×3 =60 | 25×3 =75 | 30×3 =90 |

2. ሀ. 3÷3 = 1 ምክንያቱም 3× 1 = 3 ስለሆነ

ለ. 9÷3 = 3 ምክንያቱም 3× 3 = 9 ስለሆነ

ሐ. 12÷3 = 4 ምክንያቱም 3× 4 = 12 ስለሆነ

መ. 0÷3 = 0 ምክንያቱም 3× 0 = 0 ስለሆነ

**ማስታወሻ**

ዜሮን ከ0 በተለየ ማንኛውም ሙሉ ቁጥር ብናካፍል ውጤቱ ዜሮ ነው።

## መልመጃ ሀ

የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ።

ሀ. 21÷3 ለ. 15÷3 ሐ. 63÷3 መ. 78÷3 ሠ. 84÷3 ረ. 96÷3

## ለ. እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ3 በቀሪ ማካፈል

**ተግባር ለ**

ከታች ያሉትን 7 ዶሮዎች ለ3 ሰዎች እኩል ስናካፍል ስንት ዶሮዎች ቀሪ ይሆናሉ?



2. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች ሙሉ፡፡

ሀ. 10÷ 3 = ድርሻ _____ እና _____ ቀሪ አለው

ለ. 74÷ 3 = ድርሻ _____ እና _____ ቀሪ አለው

**ማስታወሻ**

የ3 ብዜት ያልሆነ ማንኛውም ሙሉ ቁጥር ለ3 በቀሪ ይካፈላል፡፡

<u>ምሳሌ ሐ</u>

1. የሚከተሉትን ማካፈሎች አስሉ፡፡

ሀ. 11÷3 ለ. 91÷3

መፍትሔ ፡

ሀ. 11÷3 = 3 ደርሶ ቀሪ 2 አለ ምክንያቱም

$$11 = 3 \times 3 + 2$$

↑ ↑ ↑ ↑

ተካፋይ = አካፋይ×ድርሻ +ቀሪ

ለ. 91÷3 = 30 ደርሶ ቀሪ 1 አለ ምክንያቱም

$$91 = 3 \times 30 + 1$$

ተካፋይ = አካፋይ× ድርሻ + ቀሪ

### መልመጃ ለ

1. የሚከተሉትን የማካፈል ጥያቄዎችን ድርሻና ቀሪ አስሉ፡፡

ሀ. 17÷3  ለ. 55÷3  ሐ. 73÷3  መ. 88÷3

ሠ. 94÷3  ረ. 100÷3

## ሐ. እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ4 ያለ ቀሪ እና በቀሪ ማካፈል

**ተግባር ሐ**

1. ከ80 እስከ 100 ያሉትን የ4 ብዜቶች ዘርዝሩ፡፡

2. ከታች ያለውን የብርቱካን ፍሬ ስዕል በመመልከት

ሀ. በስዕሉ ላይ ስንት የብርቱካን ፍሬዎች አሉ?

ለ. ስዕሉ ላይ ያሉትን የብርቱካን ፍሬዎች 4 ቦታ ብንመድባቸው እያንዳንዱ ምድብ ስንት የብርቱካን ፍሬዎች ይኖሩታል?



ማስታወሻ፡- አንድ ሙሉ ቁጥር ያለ ቀሪ ለ4 መካፈል የሚችለው ሙሉ ቁጥሩ የ4 ብዜት ከሆነ ብቻ ነው፡፡ የ4 ብዜት ያልሆነ ማንኛውም ሙሉ ቁጥር ለ4 በቀሪ ይካፈላል፡፡

ምሳሌ መ

1. እስከ 80 ያሉትን የ4 ብዜቶች ዘርዝሩ፡፡

2. የሚከተሉትን አስሉ፡፡

ሀ. 4÷4 ለ. 36÷4 ሐ. 48÷4 መ. 100÷4

3. ከታች በሳጥኑ ውስጥ ያሉትን 8 እንጆሪዎች እኩል ለ4 ልጆች ብናካፍል እያንዳንዱ ልጅ ስንት እንጆሪ ይደርሰዋል?



መፍትሔ፡ 1.

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1×4 = 4 | 6×4 = 24 | 11×4 = 44 | 16×4 = 64 |
| 2×4 = 8 | 7×4 = 28 | 12×4 = 48 | 17×4 = 68 |
| 3×4 = 12 | 8×4 = 32 | 13×4 = 52 | 18×4 = 72 |
| 4×4 = 16 | 9×4 = 36 | 14×4 = 56 | 19×4 = 76 |
| 5×4 = 20 | 10×4 = 40 | 15×4 = 60 | 20×4 = 80 |

2. ሀ. 4÷4 = 1 ምክንያቱም 4× 1 = 4 ስለሆነ

ለ. 36÷4 = 9 ምክንያቱም 4× 9 = 36 ስለሆነ

ሐ. 48÷4 = 12 ምክንያቱም 4× 12 = 48 ስለሆነ

መ. 100÷4 = 25 ምክንያቱም 4× 25 = 100 ስለሆነ

3. 8 እንጆሪዎች እኩል ለ4 ልጆች ብናካፍል እያንዳንዱ ልጅ 2 እንጆሪ ይደርሰዋል



ምሳሌ ሠ

የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ፡፡

ሀ. 9÷4 ለ. 23÷4 ሐ. 82÷4

መፍትሔ

ሀ. 9÷4 = 2 ደርሶ ቀሪ 1 አለ ምክንያቱም 9 = 4 × 2 + 1

ተካፋይ =አካፋይ × ድርሻ + ቀሪ

ለ. 23÷4 = 5 ደርሶ ቀሪ 3 አለ ምክንያቱም 23 = 4 × 5 + 3

ተካፋይ =አካፋይ × ድርሻ + ቀሪ

ሐ. 82÷4 = 20 ደርሶ ቀሪ 2 አለ ምክንያቱም 82 = 4 × 20 + 2

ተካፋይ = አካፋይ × ድርሻ + ቀሪ

## መልመጃ ሐ

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ

ሀ. 16 ÷4 ለ. 64÷4 ሐ. 21÷4 መ. 83÷4

*መ. እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ5 እና 6 ያለ ቀሪ እና በቀሪ ማካፈል*

**ማስታወሻ**

አንድ ሙሉ ቁጥር ያለ ቀሪ ለ5 መካፈል የሚችለው ሙሉ ቁጥሩ የ5 ብዜት ከሆነ ብቻ ነው፡፡ የ5 ብዜት ያልሆነ ማንኛውም ሙሉ ቁጥር ለ5 በቀሪ ይካፈላል፡፡

አንድ ሙሉ ቁጥር ያለ ቀሪ ለ6 መካፈል የሚችለው ሙሉ ቁጥሩ የ6 ብዜት ከሆነ ብቻ ነው፡፡ የ6 ብዜት ያልሆነ ማንኛውም ሙሉ ቁጥር ለ6 በቀሪ ይካፈላል፡፡

ምሳሌ ረ

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ፡፡

ሀ. 15÷5  ለ. 65÷5  ሐ. 24÷6  መ. 96÷6

መፍትሔ

ሀ. 15÷5 = 3  ምክንያቱም 5×3 = 15 ስለሆነ

ለ. 65÷5 = 13  ምክንያቱም 5×13 = 65 ስለሆነ

ሐ. 24÷6 = 4  ምክንያቱም 6×4 = 24 ስለሆነ

መ. 96×6 = 16  ምክንያቱም 6× 16 = 96 ስለሆነ

ማስታወሻ

- የአንድ ሙሉ ቁጥር የአንድ ቤት ሆሄ 0 ወይም 5 ከሆነ ቁጥሩ ያለቀሪ ለ5 ይካፈላል፡፡የአንድ ባለ ሁለት ሆሄ ሙሉ ቁጥር የአንድ ቤት ሆሄ ከ0 ወይም ከ5 የተለየ ከሆን ቁጥሩ ለ5 ሲካፈል ቀሪ ይኖረዋል፡፡
- አንድ ሙሉ ቁጥር ለ2 እና ለ3 ያለቀሪ መካፈል ከቻለ ሙሉ ቁጥሩ ለ6 ያለቀሪ ይካፈላል፡፡

ምሳሌ ሰ የሚከተሉትን ማካፈሎች አስሉ፡፡

ሀ. 34 ÷5  ለ. 43÷6

መፍትሔ

ሀ. 34÷ 5 = 6 ደርሶ ቀሪ 4 አለ ምክንያቱም 34 = 5 × 6 + 4

ተካፋይ = አካፋይ × ድርሻ + ቀሪ

ለ. 93÷6 = 15 ደርሶ ቀሪ 3 አለ ምክንያቱም 93 = 6 × 15 + 3

ተካፋይ = አካፋይ × ድርሻ + ቀሪ

## መልመጃ መ

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ፡፡

ሀ. 25÷5 ለ. 60÷5 ሐ. 54÷6 መ. 66÷6

ሠ. 80÷5 ረ. 90÷5 ሰ. 72÷6 ሸ. 90÷6

2. የሚከተሉትን ማካፈሎች አስሉ፡፡

ሀ. 28÷5 ለ. 81÷5 ሐ. 94÷6 መ. 46÷6

ሠ. 72÷5 ረ. 93÷5 ሰ. 62÷6 ሸ. 20÷6

### ሠ. እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ7 ያለ ቀሪ እና በቀሪ ማካፈል

**ተግባር መ**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በቡድን በመሆን ስሩ፡፡

1. እስከ 20 ያሉትን የ7 ብዜት ዘርዝሩ፡፡

2. ከታች ያለውን የአሳማ ስእሎች በማየት ጥያቄዎችን መልሱ፡፡



ሀ. የአሳማዎች ብዛት ስንት ነው?

ለ. የአሳማዎችን ብዛት ከ7 ቦታ ብንመድበው እያንዳንዱ ምድብ ስንት ይደርሰዋል?

ሐ. ስንመድብ የቀሩ የአሳማዎች ብዛት ስንት ነው?

**ማስታወሻ**

አንድ ሙሉ ቁጥር ያለ ቀሪ ለ7 መካፈል የሚችለው ሙሉ ቁጥሩ የ7 ብዜት ከሆነ ብቻ ነው፡፡

የ7 ብዜት ያልሆነ ማንኛውም ሙሉ ቁጥር ለ7 በቀሪ ይካፈላል፡፡

<u>ምሳሌ ረ</u>

1. እስከ 100 ያሉትን የ7 ብዜት ዘርዝሩ፡፡
2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች አስሉ፡፡

ሀ. $7 \div 7$ ለ. $42 \div 7$ ሐ. $70 \div 7$ መ. $91 \div 7$

መፍትሔ 1.

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| $1\times7 = 7$ | $4\times7 = 28$ | $7\times7 = 49$ | $10\times7 = 70$ | $13\times7 = 91$ |
| $2\times7 = 14$ | $5\times7 = 35$ | $8\times7 = 56$ | $11\times7 = 77$ | $14\times7 = 98$ |
| $3\times7 = 21$ | $6\times7 = 42$ | $9\times7 = 63$ | $12\times7 = 84$ | |

2. ሀ. $7 \div 7 = 1$ ምክንያቱም $7\times1 = 7$ ስለሆነ

ለ. $42 \div 7 = 6$ ምክንያቱም $7\times6 = 42$ ስለሆነ

ሐ. $70 \div 7 = 10$ ምክንያቱም $7\times10 = 70$ ስለሆነ

መ. $91 \div 7 = 13$ ምክንያቱም $7\times13 = 91$ ስለሆነ

ምሳሌ ሰ

ሀ. $18 \div 7 = 2$ ደርሶ ቀሪ 4 አለ ምክንያቱም $18 = 7 \times 2 + 4$

ለ. $82 \div 7 = 11$ ደርሶ ቀሪ 5 አለ ምክንያቱም $82 = 7 \times 11 + 5$

## መልመጃ ሠ

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ፡፡

ሀ. 28÷7 ለ. 84÷7 ሐ. 14÷7 መ. 63 ÷7

ሠ. 52÷7 ረ. 13÷7 ሰ. 62÷7 ሸ. 20÷7

## ረ. እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ8 እና በ9 ያለ ቀሪ እና በቀሪ ማካፈል

ተግባር ሠ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በቡድን በመሆን ስሩ፡፡

1. እስከ 20 ያሉትን የእያንዳንዳቸዉን የ8ና 9 ብዜቶች ዘርዝሩ፡፡

2. ከታች ያለውን የአበባ ስእሎች በማየት ጥያቄዎችን መልሱ፡፡



ሀ. የአበባዎች ብዛት ስንት ነው?

ለ. አበባዎችን ከ8 ቦታ ብንመድባቸው እያንዳንዱ ምድብ ስንት አበባዎች ይይዛል? ስንመድብ የቀሩ የአበባዎች ብዛት ስንት ናቸው?

ሐ. አበባዎችን ከ9 ቦታ ብንመድባቸው እያንዳንዱ ምድብ ስንት አበባዎች ይይዛል?

**ምሳሌ ረ** እስከ 100 ያሉት የ8 ብዜት፡፡

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1×8 = 8 | 3×8 = 24 | 5×8 = 40 | 7×8 =56 | 9×8 = 72 | 11×8 = 88 |
| 2×8 = 16 | 4×8 = 32 | 6×8 = 48 | 8×8 =64 | 10×8 =80 | 12×8 = 96 |

2. እስከ 100 ያሉት የ9 ብዜት፡፡

$1\times9 = 9$ $3\times9 = 27$ $5\times9 = 45$ $7\times9 = 63$ $9\times9 = 81$ $11\times9 = 99$

$2\times9 = 18$ $4\times9 = 36$ $6\times9 = 54$ $8\times9 = 72$ $10\times9 = 90$

**ማስታወሻ**

- አንድ ሙሉ ቁጥር ያለ ቀሪ ለ8 መካፈል የሚችለው ሙሉ ቁጥሩ የ8 ብዜት ከሆነ ብቻ ነው፡፡ የ8 ብዜት ያልሆነ ማንኛውም ሙሉ ቁጥር ለ8 በቀሪ ይካፈላል፡፡
- አንድ ሙሉ ቁጥር ያለ ቀሪ ለ9 መካፈል የሚችለው ሙሉ ቁጥሩ የ9 ብዜት ከሆነ ብቻ ነው፡፡ የ9 ብዜት ያልሆነ ማንኛውም ሙሉ ቁጥር ለ9 በቀሪ ይካፈላል፡፡

ምሳሌ ቀ

ሀ. $48\div 8 = 6$ ምክንያቱም $8\times6 = 48$

ለ. $63\div 9=7$ ምክንያቱም $9\times7 = 63$

ሐ. $77\div 8 = 9$ ደርሶ 5 ቀሪ ምክንያቱም $77 = 8\times9 + 5$

መ. $91\div 9 = 10$ ደርሶ 1 ቀሪ ምክንያቱም $91 = 9\times10 + 1$

## መልመጃ ረ

1. የሚከተሉትን ማካፈሎች አስሉ፡፡

ሀ. $88\div8$ ለ. $64\div8$ ሐ. $32\div8$ መ. $99\div9$

ሠ. $52\div8$ ረ. $14\div8$ ሰ. $71\div9$ ሸ. $20\div9$

## 4.6 ማባዛት እና ማካፈል ያላቸው ዝምድና

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት

ማባዛት እና ማካፈል ያላቸው ዝምድና

**ማስታወሻ**

1. ሀ፣ለ እና መ ሙሉ ቁጥሮች ቢሆኑ ሀ ÷ ለ = መ እውነት ከሆነ ሀ = መ× ለ ሁልጊዜ እውነት ነው፡፡"ሀ" ተካፋይ፣ "ለ" አካፋይ፣ "መ" ድርሻ ይባላሉ፡፡

   ተካፋይ ÷ አካፋይ = ድርሻ ወይም ተካፋይ = አካፋይ × ድርሻ

2. ሀ፣ለ፣መ እና በ ሙሉ ቁጥሮች ቢሆኑ ሀ ÷ ለ = መ ቀሪ በ ከሆነ ሀ =መ ×ለ +በ ሁልጊዜም እውነት ነው::"ሀ" ተካፋይ፣ "ለ" አካፋይ፣ "መ" ድርሻ እና "በ" ቀሪ ይባላሉ::

   ይህም ማለት ማካፈል በማባዛት ይረጋገጣል ማለት ነው::

<u>ምሳሌ ሐ</u>

የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉና መልሳችሁን በማባዛት አረጋግጡ፡፡

ሀ. 12 ÷2 =____ ለ. 18÷3=______ ሐ. 50÷4=______

መፍትሔ :-

ሀ. 12 ÷2 = 6 ምክንያቱም 12 = 2×6 በመሆኑ ነው፡፡

ስለዚህ ተካፋይ = 12፣ አካፋይ = 2 እና ድርሻ = 6 ናቸው፡፡

ለ. 18 ÷3 = 6 ምክንያቱም 18 = 3×6 በመሆኑ ነው፡

ስለዚህ ተካፋይ = 18፣ አካፋይ = 3 እና ድርሻ = 6 ናቸው፡፡

ሐ. 50÷4= 12 ቀሪ 2 ምክንያቱም 4x12+2=50

ስለዚህ 50 ተካፋይ=50 አካፋይ=4 ድርሻ =12 እና ቀሪ 2 በመሆኑ ነው::

## መልመጃ ሀ

የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉና መልሳችሁን በማባዛት አረጋግጡ፡፡

ሀ . 24 ÷3  ለ.40 ÷5  ሐ. 84 ÷8  መ. 65 ÷3

### *እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማካፈልን የያዘ የቃላት ፕሮብሌሞችን መስራት*

- እስከ 100 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማካፈል የያዙ የቃላት ፕሮብልሞችን መፍታት

**ተግባር ሀ**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በመሆን ስሩ፡፡

1. 24 ከረሜላዎችን ለ8 ቡድን ብናከፋፍል እያንዳንዱ ቡድን ምን ያህል ከረሜላ ይደርሳቸዋል?



2. 28 ልጆች 4 የእግር ኳስ ቡድን መሰረቱ፡፡ ሁሉም ቡድኖች እኩል ልጆችን ቢይዙ አንዱ የእግር ኳስ ቡድን ምንክህል ልጆችን ይዟል?

**ማስታወሻ**

የቃላት ፕሮብሌሞችን ስንሰራ መከተል ያለብን ዘዴዎች

1. ፕሮብሌሙን በጥንቃቄ አንብቦ መረዳት
2. ፕሮብሌሙን ወደ ቁጥር መቀየር
3. ወደ ቁጥር የተቀየረውን ማስላት
4. ያገኘነውን መልስ ከቃላት ፕሮብሌሙ ጋር መጣጣሙን ማረጋገጥ

ምሳሌ ሀ

1. የ 10 ፍሬዎች ብርቱካን ዋጋ 90 ብር ቢሆን የአንዱ ፍሬ ብርቱካን ዋጋ ስንት ይሆናል?

**መፍትሔ :**

90 ብር የ10 ፍሬዎች ብርቱ ካን ዋጋ ነው:: ስለዚህ 90 ብር ለ10ፍሬ ብርቱካን ሲካፈል የአንዱን ፍሬ ብርቱካን ዋጋ ይሰጣል:: ይህ ማለት $90 \div 10 = 9$

የአንድ ፍሬ ብርቱካን ዋጋ 9 ብር ይሆናል ማለት ነው ::

ምክንያቱም 10 ፍሬ ብርቱካን × 9 ብር = 90 ብር

2. 30 ቸኮሌቶችን ለ5 ልጆች እኩል ቢከፋፈሉ ለእያንዳንዳቸው ልጆች ምንክህል ቸኮሌት ይደርሳቸዋል?

**መፍትሔ :** 30 ቾኮሌት ÷ 5 = 6 ቸኮሌት ምክንያቱም $5 \times 6 = 30$

## መልመጃ ሀ

የሚከተሉትን የቃላት ፕሮብሌሞች ስሩ::

1. 24 ጣፋጭ ኬኮችን ለ6 ልጆች እኩል ቢከፋፈሉ እያንዳንዳቸው ምን ያህል ጣፋጭ ኬኮች ይደርሳቸዋል?
2. የ8 ፓኬቶች እርሳስ ዋጋ 96 ብር ቢሆን የአንዱ ፓኬት እርሳስ ዋጋ ስንት ብር ይሆናል?
3. 50 ከወተት የተሰሩ ከረሚላዎች ለ5 ተማሪዎች እኩል ተከፋፈሉ፤ አንዱ ተማሪ ምን ያህል ከወተት የተሰራ ከረሜላዎች ይደርሰዋል?
4. 45 ሬኖዎች ለ9 ህፃናቶች እኩል ቢካፈሉ እያንዳንዳቸው ህፃናት ምንያክል ሬኖ ይደርሰቸዋል?
5. 21 ሻማዎች ለ3 ቤቶች እኩል ቢከፋፈሉ አንዱ ቤት ምንያክል ሻማ ይደረሰዋል?
6. ሰብለ አንድ ብርጭቆ የብርቱካን ጭማቂ ለማዘጋጀት 6 የብርቱካን ፍሬዎች ያስፈልጋታል:: ሰብለ 96 የብርቱካን ፍሬዎች ቢኖራት ስንት ብርጭቆ የብርቱካን ጭማቂ ማዘጋጀት ትችላለች?

## የምዕራፍ አራት ማጠቃለያ

- ማካፈል ማለት የመቀነስ ድግግሞሽ አጭር ስሌት ነው
- ተካፋይ ÷ አካፋይ =ድርሻ ወይም ተካፋይ = አካፋይ × ድርሻ፡፡ ማካፈል በማባዛት ይረጋገጣል፡፡
- የአንድ ሙሉ ቁጥር የአንድ ቤት ሆሄ ከ0፣ከ2፣ከ4፣ ከ6 ወይም ከ8 አንዱን ከሆነ ቁጥሩ ያለ ቀሪ ለ2 ይካፈላል፡፡
- ለ10 ያለቀሪ የሚካፈል ማንኛውም ሙሉ ቁጥር ለ2 ያለቀሪ ይካፈላል፡፡
- ማንኛውም ሙሉ ቁጥር ለ1 ሲካፈል እራሱ ሙሉ ቁጥሩን ይሰጣል፡፡
- አንድ ሙሉ ቁጥር ያለ ቀሪ ለ3 መካፈል የሚችለው ሙሉ ቁጥሩ የ3 ብዜት ከሆነ ብቻ ነው፡፡
- አንድ ሙሉ ቁጥር ያለ ቀሪ ለ4 መካፈል የሚችለው ሙሉ ቁጥሩ የ4 ብዜት ከሆነ ብቻ ነው፡፡
- የ4 ብዜት ያልሆነ ማንኛውም ሙሉ ቁጥር ለ4 በቀሪ ይካፈላል፡፡
- አንድ ሙሉ ቁጥር ያለ ቀሪ ለ5 መካፈል የሚችለው ሙሉ ቁጥሩ የ5 ብዜት ከሆነ ብቻ ነው፡፡
- አንድ ሙሉ ቁጥር ያለ ቀሪ ለ6 መካፈል የሚችለው ሙሉ ቁጥሩ የ6 ብዜት ከሆነ ብቻ ነው፡፡
- የ7 ብዜት ያልሆነ ማንኛውም ሙሉ ቁጥር ለ7 በቀሪ ይካፈላል
- አንድ ሙሉ ቁጥር ያለ ቀሪ ለ8 መካፈል የሚችለው ሙሉ ቁጥሩ የ8 ብዜት ከሆነ ብቻ ነው፡፡
- አንድ ሙሉ ቁጥር ያለ ቀሪ ለ9 መካፈል የሚችለው ሙሉ ቁጥሩ የ9 ብዜት ከሆነ ብቻ ነው፡፡

## የምዕራፍ አራት ማጠቃለያ መልመጃ

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች ከአካፈላችሁ በኋላ ተካፋይ፣ አካፋይ፣ ድርሻቸውን እና ቀሪውን ለይታችሁ ፃፉ::

   ሀ.84÷ 3 ለ. 96÷ 6 ሐ. 59÷ 7 መ.54÷2 ሠ. 415÷2

2. የሚከተሉትን ቁጥሮች አካፍሉና መልሳችሁን በማባዛት አረጋግጡ::

   ሀ.24÷3 ለ.84÷ 6 ሐ.91÷7 መ.76÷ 4

   ሠ.53÷ 1 ረ.88÷5 ሸ. 94÷3

3. አንድ የጫማ ፋብሪካ በ7 ሰዓት ውስጥ 98 ጫማዎችን ቢያመርት በ1 ሰዓት ምን ያህል ጫማዎችን ያመርታል?

4. ማንኛውም የ10 ብዜት ለ5 ተካፋይ ነው? ሀ. እውነት ለ. ሀሰት

# ምዕራፍ 5 ክፍልፋዮች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች:

- ክፍልፋዮች የሙሉ ቁጥሮች ክፍሎች እንደሆኑ ትረዳላችሁ::
- በክፍልፋዮች ተግባራዊ የሚሆኑ መልመጃዎችን ትሰራላችሁ::

**መግቢያ**

ክፍልፋይ ማለት የአንድ ሙሉ ነገርን ክፋይ የሚገልፅ ነው:: ክፍልፋይ ሁለት ቁጥሮችን በመጠቀም የሚፃፍ ሲሆን፤ከላይ እና ከታች ቁጥሮች ተፅፈው ይገለፃል፤ከላይ ያለው ቁጥር ላዕል ሲባል ከታች ያለው ቁጥር ደግሞ ታህት ይባላል::

$$\frac{1}{3}$$

1 ← ላዕል

3 ← ታህት

## 5.1 ግማሽ፣ሲሶና ሩብ

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት

- ግማሽ፣የሲሶ እና የሩብ ምንነትን መለየት፣ማወዳደር መቻል

### *ሀ . ግማሽ፣የሲሶ እና የሩብ ምንነትን መለየት*

## ተግባር ሀ

የሚከተሉትን ስዕሎች በመመልከት ከታች ያሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡




1. ሀ ላይ ያለው ስዕል ስንት ክፍሎች አሉት?
2. ሀ ላይ ያለው ስዕል ስንት የተቀባ ክፍሎች አሉት?
3. ለ ላይ ያለው ስዕል ስንት የተቀባ ክፍሎች አሉት?
4. ሐ ላይ ያለውን ስዕል ጠቅላላ ክፍሎችና የተቀባውን ክፍል በቁጥር ግለፁ፡፡

<u>ምሳሌ ሀ</u>

ከታች ያሉትን ክቦች ተመልከቱ እና ጥያቄዎችን መልሱ፡




1. ሀ ላይ ያለውን ስዕል ጠቅላላ ክፍሎችና የተቀባውን ክፍል ስንት ነው?
   የተቀባውን በክፍልፋይ ግለፁ፡፡
2. ለ ላይ ያለውን ስዕል ጠቅላላ ክፍሎችና የተቀባውን ክፍል ስንት ነው?
   የተቀባውን በክፍልፋይ ግለፁ፡፡
3. ሐ ላይ ያለውን ስዕል ጠቅላላ ክፍሎችና የተቀባውን ክፍል ስንት ነው?
   የተቀባውን በክፍልፋይ ግለፁ፡፡

መፍትሔ

1. ሀ ላይ የተመለከተው ስዕል አንድ ሙሉ ክብ ሁለት እኩል ቦታ ነው የተከፈለው፣ የተቀባው ከሁለቱ አንዱ ክፍል ሲሆን ይህ ክፍል የሙሉ ክፍሉ ግማሽ ነው:: በአሀዛዊ አፃፃፍ : $\frac{1}{2}$ ሲነበብ አንድ ሁለተኛ ተብሎ ይነበባል:: ይህ ማለት የክፍልፋዩ ብዛት = 2 የተቀባው ክፍል ብዛት =1

የተቀባው ብዛት በክፍልፋይ = አንድ ሁለተኛ

2. ለ ላይ ያለው ስዕል ሙሉ ክብ ከሦስት እኩል ቦታ ተከፍሎ አንዱ ክፍል ተቀብቷል::ይህ ክፍል የሙሉ ክቡ አንድ ሦስተኛ አካል ነው::በአሀዛዊ አፃፃፍ: $\frac{1}{3}$ ሲነበብ አንድ ሶስተኛ ተብሎ ይነበባል::

ይህ ማለት የክፍልፋዩ ብዛት = 3 የተቀባው ክፍል ብዛት = 1

የተቀባው ብዛት በክፍልፋይ = አንድ ሦስተኛ

3. ሐ ላይ የተመለከትነው ስዕል ሙሉ ክብ ከአ ራት እኩል ቦታ ተከፍሎ አንዱ ክፍል ተቀብቷል::ይህ ክፍል የክቡ አንድ አራተኛ አካል ነው::

በአሀዛዊ አፃፃፍ : $\frac{1}{4}$ ሲነበብ አንድ አራተኛ ተብሎ ይነበባል::

ይህ ማለት የክፍልፋዩ ብዛት = 4 የተቀባው ክፍል ብዛት=1

የተቀባው ብዛት በክፍልፋይ = አንድ አራተኛ

ማስታወሻ:- የተወሰኑት የክፍልፋዮች የተለመደ አጠራር አላቸው እነሱም

- $\frac{1}{2}$ ማለት ግማሽ ይባላል::
- $\frac{1}{3}$ ማለት ሲሶ ይባላል::
- $\frac{1}{4}$ ማለት ሩብ ይባላል::
- $\frac{1}{5}$ ማለት አምሾ ይባላል::
- $\frac{1}{10}$ ማለት አስራት ይባላል::

## መልመጃ ሀ

ስዕሎችን በመመልከት ያልቀለመውን በክፍልፋይ ግለፁ:: መልሳችሁን በአሀዝ እና በፊደል ፃፉ::

ሀ.



ያልቀለመው ብዛት=_______

ያልቀለመው በክፍልፋይ =______

የክፍልፋዮችብዛት= _______

ለ.



ያልቀለመው ብዛት=_______

ያልቀለመው በክፍልፋይ =______

የክፍልፋዮችብዛት= _______

ሐ



ያልቀለመው ብዛት=_______

ያልቀለመው በክፍልፋይ =______

የክፍልፋዮችብዛት= _______

### ትርጉም

አሃዳዊ ክፍልፋይ ማለት ላዕሉ 1 የሆነ ክፍልፋይ ነው::

የክፍልፋዮች የላይኛው ቁጥር ላዕል ሲሆን ታችኛው ደግሞ ታህት ይባላል::

ምሳሌ ለ የ$\frac{1}{4}$ ፣ 1 ላዕል ስትሆን 4 ደግሞ ታህት ነች::

ምሳሌ ሐ ከሚከተሉት ውስጥ አሃዳዊ ክፍልፋይ ያልሆነው የቱ ነው ?

ሀ. $\frac{1}{3}$ ለ. $\frac{1}{5}$ ሐ. $\frac{1}{10}$ መ. $\frac{1}{4}$ ሠ. $\frac{3}{4}$ ረ. $\frac{1}{8}$

**መፍትሔ፡**

ከ$\frac{3}{4}$ በስተቀር ሁሉም ላዕላቸው 1 ነው፡፡ ስለዚህ $\frac{3}{4}$ አሀዳዊ ክፍልፋይ አይደለም፡፡

## ለ. ግማሽ፣የሲሶ እና የሩብ ማወዳደር

**ተግባር ለ**

12 እርሳሶች ቢኖሩ እና በተለያየ መጠን ቢከፋፈሉ

ሀ.ለሁለት ቢካፋሉ ——— ይደርሳል፡፡ ለ. ለሦስት ቢካፈሉ———ይደርሳል፡፡

ሐ. ለአራት ቢካፈሉ——ይደርሳል፡፡ መ. ሀ፣ለ እና ሐ ላይ ያገኛችሁትን አወዳድሩ፡፡

<u>ምሳሌ ሐ</u>

ለሚከተሉት ስዕሎች ክፍልፋዮቻቸውን በመግለፅ ከጠቆሩት ውስጥ የትኛው ክፍል ይበልጣል?



$\frac{1}{4}$ $\frac{1}{3}$ $\frac{1}{2}$

ከስዕሉ እንደምትመለከቱት ቢጫ ቀለሙ ከሁሉም ይሰፋል በመቀጠል ሰማያዊ ቀለሙ ከአረንጓዴው ይሰፋል፤ ይህ የሚያሳየው $\frac{1}{2}$ ከሁሉም ይበልጣል ፣$\frac{1}{3}$ ደግሞ ከ$\frac{1}{4}$ ይበልጣል:: ስለዚህ $\frac{1}{2} > \frac{1}{3}$፤ $\frac{1}{2} > \frac{1}{4}$ ፤ $\frac{1}{3} > \frac{1}{4}$ ወይም ከትንሽ ወደ ትልቅ በቅደም ተከተል ስንፅፋቸው እንደሚከተለው ይሆናል:: $\frac{1}{4}$፣$\frac{1}{3}$ እና $\frac{1}{2}$

## 5.2 ከ $\frac{1}{2}$ እስከ $\frac{1}{10}$ ያሉ አሃዳዊ ክፍልፋዮች

**የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት**

- ከ $\frac{1}{2}$ እስከ $\frac{1}{10}$ ያሉ አሃዳዊ ክፍልፋዮች በቁጥር መስመር ላይ ማንበብና መፃፍ
- የክፍልፋዮችን ሃሳብ አረዳድ ለማሳደግ የአንድ ሙሉ ነገር ክፍል፣ የስብስቦች አካል፣ በቁጥር መስመር ላይ ማመልከት

<u>ምሳሌ ሀ</u> ስዕሎችን በመመልከት የቀለመውን ከክፍልፋዩ ጋር በማስተያየት ክፍልፋዩን በፊደል ግለፁ።




<u>መፍትሔ</u>

ሀ. አንድ አምስተኛ ለ. አንድ ስድስተኛ ሐ. አንድ ሰባተኛ

**መልመጃ ሀ**

ከታች የምትመለከቷቸውን ስንጠረዥች በመጠቀም የተሰጡትን ክፍልፋዮች አጥቁሩ።

ሀ. $\frac{1}{8}$ ለ. $\frac{1}{10}$ ሐ $\frac{1}{9}$







**ማስታወሻ**

ሁለት አሃዳዊ ክፍልፋዮችን ስናወዳድር ትልቅ ታህት ያለው ትንሽ ታህት ካለው ክፍልፋይ ያንሳል።

ምሳሌ: $\frac{1}{4} > \frac{1}{6}$ ይህ ማለት $\frac{1}{4}$ ማለት አንድ ሙሉ ነገር ለ4 ማካፈል ሲሆን $\frac{1}{6}$ ማለት ደግሞ አንድ ሙሉ ነገር ለ6 ማካፈል ነው ።

## መልመጃ ለ

የሚከተሉትን አሃዳዊ ክፍልፋዮች "<" ፣"=" ወይም ">" በመጠቀም አወዳድሩ፡፡

ሀ. $\frac{1}{4}$ ___ $\frac{1}{8}$ ለ. $\frac{1}{8}$ ___ $\frac{1}{6}$ ሐ. $\frac{1}{5}$ ___ $\frac{1}{7}$

መ. $\frac{1}{9}$ ___ $\frac{1}{3}$ ሠ. $\frac{1}{3}$ ___ $\frac{1}{3}$ ረ. $\frac{1}{10}$ ___ $\frac{1}{13}$

ምሳሌ ለ ከአሃዳዊ ክፍልፋዮች በተጨማሪም




የክፍልፋዮች ብዛት=4

የቀለሙት ብዛት=3 የቀለመው በክፍልፋይ = $\frac{3}{4}$

## መልመጃ ሐ

ምሳሌውን በመጠቀም ከተቀባው ክፍል ጋር የሚዛመደውን ክፍልፋይ አክብቡ፡፡



| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. | $\frac{7}{8}$ | $\frac{5}{7}$ | $\frac{6}{8}$ |
| 2. | $\frac{1}{2}$ | $\frac{4}{6}$ | $\frac{2}{3}$ |
| 3. | $\frac{3}{4}$ | $\frac{2}{3}$ | $\frac{3}{6}$ |
| 4. | $\frac{2}{3}$ | $\frac{6}{8}$ | $\frac{1}{2}$ |

**ማስታወሻ** ክፍልፋዮችን በቁጥር መስመር ለማመልከት

- በመጀመሪያ ታህቱን በማየት የቁጥር መስመሩን እኩል በታህቱ ልክ መከፋፈል
- በመቀጠል ደግሞ ከግራ ወደ ቀኝ ክፍልፋዮችን በመቁጠር ማመልከት

### ሐ. ከ $\frac{1}{2}$ እስከ $\frac{1}{10}$ ያሉ አሃዳዊ ክፍልፋዮች በቁጥር መስመር

<u>ምሳሌ መ</u>

ሀ. መስመሩ የሚያመለክተው 1 ሙሉ ነገርን ሲሆን $\frac{1}{2}$ በቁጥር መስመር ለማስቀመጥ በመጀመሪያ ለሁለት እኩል ቦታ መክፈል፡፡በመቀጠል ደግሞ ከግራ ወደ ቀኝ አንድ ክፍል ቆጥረን ማመልከት፡፡




ለ. $\frac{1}{6}$ በቁጥር መስመር ላይ ለማስቀመጥ በመጀመሪያ መስመር በመውሰድ እኩል 6 ቦታ ከፋፍሎ ማስቀመጥ




**መልመጃ መ**

1. የሚከተሉትን ክፍልፋዮች በተሰጠው የቁጥር መስመር ላይ አመልክቱ፡፡
2. ሀ. $\frac{1}{8}$




ለ. $\frac{1}{3}$




ሐ. $\frac{3}{4}$



2. የቁጥር መስመሩን በመሳል የሚከተሉትን ክፍልፋዮች አመልክቱ።

ሀ. $\frac{1}{7}$ ለ. $\frac{1}{4}$

3. ከሚከተሉት የቁጥር መስመር የምትመለከቱትን ክፍል ሀ እና ለን በክፍልፋይ ግለፁ።




## 5.3 ግማሽ እና ሩብ

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃቶች

- አንድ ሙሉ ነገር ግማሽ ማስላት
- አንድ ሙሉ ነገር ሩብ ማስላት
- የሙሉ ቁጥሮችን ተካፋይነት መጠቀም

ሀ. ግማሽ ማለት አንድ ሙሉ ነገርን ለሁለት ስናካፍል የምናገኘው ድርሻ ነው

ለምሳሌ የክቡ የተቀባው ክፍል የክቡ ግማሽ ነው፡፡



ግማሽ በአሃዝ ሲገለፅ $= \frac{1}{2}$

ምሳሌ ሀ ፡ ለሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ግማሽ ፈልጉ?

ሀ .12 ለ.30 ሐ.46 መ. 68

**መፍትሔ**

ሀ.12÷2 = 6 ይህ ማለት የ12 ግማሽ 6 ነው።

ለ. 30÷2= 15 የ30 ግማሽ 15 ነው።

ሐ.46÷2 = 23 የ46 ግማሽ 23 ነው።

መ.68÷ 2= 34 የ68 ግማሽ 34 ነው።

**መልመጃ ሀ**

ለሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ግማሽ ፈልጉ፡፡

ሀ.14 ለ. 98 ሐ. 86 መ. 92

ለ. ሩብ፡ ማለት አንድን ሙሉ ነገር ለአራት ስናካፍል የምናገኘው ድርሻ ነው፡፡

ለምሳሌ በስዕሉ ላይ የተቀባው ክፍል ሩብ ወይም $\frac{1}{4}$ ነው፡፡



ምሳሌ ለ ከዚህ በታች ላሉት ሙሉ ቁጥሮች ሩብ ፈልጉ፡፡

ሀ.8 ለ.24 ሐ.48 መ.72 ሠ.100

መፍትሔ

ሀ.8÷4 = 2 ስለዚህ የ8 ሩብ 2 ነው፡፡

ለ .24÷4 = 6 ስለዚህ የ24 ሩብ 6 ነው፡፡

ሐ. 48÷4 = 12 ስለዚህ የ48 ሩብ 12 ነው፡፡

መ. 72÷4 = 18 ስለዚህ የ72 ሩብ 18 ነው፡፡

ሠ.100÷4 = 25 ስለዚህ የ100 ሩብ 25 ነው፡፡

**መልመጃ ለ**

ለሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ሩብ ፈልጉ፡፡

ሀ. 4 ለ. 16 ሐ. 36 መ. 68 ሠ. 84 ረ. 92

## 5.4 ክፍልፋዮችን መግለፅ

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃቶች

- አቻ ክፍልፋዮች መፈለግ
- የተለመዱ ክፍሉፋዮችን በመጠቀም አቻ ክፍልፋዮችን መረዳት፣ መተንተን
- ከእለት ተእለት ህይወታቸው ጋር የተያያዙ ክፍልፋዮችን እንደ ግማሽ፣ ሲሶ እና ሩብ ፕሮብሌሞችን መስራት

**ተግባር ሀ**

የሚከተሉትን ስዕሎች በመመልከት የተቀባውን ክፍል በክፍልፋይ ፃፉ እና ክፍልፋዮችን አወዳድሩ::



**ምሳሌ ሀ፡**

የሚከተሉትን ስዕሎች በመመልከት የተቀባውን ክፍል በክፍልፋይ ፃፉ እና ክፍልፋዮችን አወዳድሩ::



መፍትሔ

የመጀመሪያው ክብ ከአጠቃላይ 8 ክፍሎች ውስጥ 6ቱ የተጠቆሩት ሲሆኑ በክፍልፋይ ሲፃፍ ስድስት ስምንተኛ ወይም $\frac{6}{8}$ ይሆናል::

የሁለተኛውም ክብ ከአጠቃላይ 4 ክፍሎች ውስጥ 3ቱ የተጠቆሩ ሲሆን በክፍልፋይ ሲፃፍ ሶስት አራተኛ ወይም $\frac{3}{4}$ ይሆናል::

የሁለቱም ክቦች የተጠቆረው ተመሳሳይ ስፋት ያለው ክፍል ቢሆንም ግን የክፍልፋዮች ላዕል እና ታህት የተለያለ ነው:: እነዚህን አይነት ጥንድ ክፍልፋዮች አቻ ክፍልፋዮች እንላቸዋለን::

**ትርጉም፡**

ሁለት ክፍልፋዮች አቻ ክፍልፋዮች የሚባሉት የተለያየ ታህት እና ላዕል ያላቸው ነገር ግን ተመሳሳይ ዋጋ ያላቸው ክፍልፋዮች ናቸው::

ለአንድ ክፍልፋይ አቻ ክፍልፋይ ለማግኘት ታህት እና ላዕሉን በተመሳሳይ መቁጠሪያ ቁጥር ማባዛት ወይም ማካፈል ነው::

ምሳሌ ለ ለሚከተሉት ክፍልፋዮች አቻ ክፍልፋዮችን ፈልጉ::

ሀ .$\frac{1}{4}$ ለ. $\frac{3}{6}$ ሐ. $\frac{2}{4}$ መ. $\frac{8}{12}$

**መፍትሔ**

ሀ. $\frac{1}{4}$ ፤ $\frac{1\times2}{4\times2}=\frac{2}{8}$ ፤ $\frac{1\times3}{4\times3}=\frac{3}{12}$ ፤ $\frac{1\times4}{4\times4}=\frac{4}{16}$

ስለዚህ $\frac{1}{4}$፣ $\frac{2}{8}$፣ $\frac{3}{12}$ እና $\frac{4}{16}$ አቻ ክፍልፋዮች ናቸው።

ለ. $\frac{3}{6}$ ፤ $\frac{3\times2}{6\times2}=\frac{6}{12}$ ፤ $\frac{3\times3}{6\times3}=\frac{9}{18}$ ፤ $\frac{3\times4}{6\times4}=\frac{12}{24}$

ስለዚህ $\frac{3}{6}$ ፣$\frac{6}{12}$፣$\frac{12}{18}$ እና $\frac{12}{24}$ በማባዛት የተገኙ አቻ ክፍልፋዮች ናቸው።

ሐ . $\frac{2}{4}$ ፤ $\frac{2\times2}{4\times2}=\frac{4}{8}$ ፤ $\frac{2\times3}{4\times3}=\frac{6}{12}$ ፤ $\frac{2\times4}{4\times4}=\frac{8}{16}$ ፤ $\frac{2\times5}{4\times5}=\frac{10}{20}$

ስለዚህ $\frac{4}{8}$ ፣$\frac{6}{12}$፣ $\frac{8}{16}$ እና $\frac{10}{20}$ በማባዛት የተገኙ አቻ ክፍልፋዮች ናቸው። ተጨማሪ ታህት እና ላዕላቸው በተመሳሳይ ሙሉ ቁጥር የሚካፈል ከሆነ አቻ ክፍልፋዩ በማካፈልም ማግኘት ይችላል። $\frac{2\div2}{4\div2}=\frac{1}{2}$ በተጨማሪ $\frac{2}{4}$ እና $\frac{1}{2}$ አቻ ክፍልፋዮች ናቸው።

$\frac{1}{2}$፣$\frac{2}{4}$፣$\frac{4}{8}$ ፣$\frac{6}{12}$፣ $\frac{8}{16}$ እና $\frac{10}{20}$ አቻ ክፍልፋዮች ናቸው።

መ. $\frac{8}{12}$ በማባዛት የምናገኛቸው አቻ ክፍልፋዮች

$\frac{8\times2}{12\times2}=\frac{16}{24}$ ፤ $\frac{8\times3}{12\times3}=\frac{24}{36}$ ፤ $\frac{8\times4}{12\times4}=\frac{32}{48}$

በማካፈል የምናገኛቸው ክፍልፋዮች ደግሞ

$\frac{8\div2}{12\div2}=\frac{4}{6}$ ፤ $\frac{8\div4}{12\div4}=\frac{2}{3}$

ስለዚህ $\frac{2}{3}$ ፣ $\frac{4}{6}$ ፣ $\frac{8}{12}$ ፣$\frac{16}{24}$፣ $\frac{24}{36}$ እና $\frac{32}{48}$ የተወሰኑት አቻ ክፍልፋዮች ናቸው።

## መልመጃ ሀ

ለሚከተሉት ክፍልፋዮች ለእያንዳንዳቸው ቢያንስ 3 አቻ ክፍልፋይ ፃፉ።

ሀ. $\frac{1}{3}$ ለ. $\frac{1}{5}$ ሐ. $\frac{3}{4}$ መ. $\frac{6}{8}$ ሠ. $\frac{8}{16}$

## የምዕራፍ 5 ማጠቃለያ

- ክፍልፋይ ማለት አንድን ሙሉ ነገር በተለያየ መጠን መከፋፈል ማለት ነው፡፡
- የክፍልፋዩ የላይኛው ቁጥር ላዕል ሲባል የታችኛው ደግሞ ታህት ይባላል፡፡
- አሃዳዊ ክፍልፋይ ማለት ላዕሉ 1 የሆነ ክፍልፋይ ነው፡፡
- ግማሽ ማለት አንድን ሙሉ ነገርን ለሁለት ስናካፍል የምናገኘው ድርሻ ነው፡፡
- ሩብ ማለት አንድን ሙሉ ነገርን ለአራት ስናካፍል የምናገኘው ድርሻ ነው፡፡
- ሁለት አህዳዊ ክፍልፋዮች ስናወዳድር ታህቱ ትንሽ የሆነው ክፍልፋይ ታህቱ ትልቅ ከሆነው ክፍልፋይ ይበልጣል፡፡
- ሁለት ክፍልፋዮች አቻ ክፍልፋዮች የሚባሉት የተለያየ ታህት እና ላዕል ያላቸው ነገር ግን ተመሳሳይ ዋጋ ያላቸው ቁጥሮች ናቸው፡፡
- ለአንድ ክፍልፋይ አቻ ክፍልፋይ ለማግኘት ታህት እና ላዕሉን በተመሳሳይ ሙሉ ቁጥር በማባዛት ወይም በማካፈል ነው

## የምዕራፍ 5 ማጠቃለያ መልመጃ

1. ለሚከተሉት ስዕሎች በምሳሌው መሰረት ለእያንዳንዳቸው የተጠቆረውን በክፍልፋይ ግለፁ::




2. ምሳሌውን በመጠቀም ከተቀባው ክፍል ጋር የሚዛመደውን ክፍልፋይ አክብቡ::




3. ከሚከተሉት ውስጥ አሃዳዊ ክፍልፋይ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. $\frac{5}{3}$ ለ. . $\frac{2}{3}$ ሐ. $\frac{1}{7}$ መ. $\frac{9}{11}$

4. $\frac{3}{5}$ እና $\frac{9}{15}$ አቻ ክፍልፋዮች ናቸው::

ሀ. እውነት ለ. ሀሰት

5. በቁጥር መስመሩ ላይ የምትመለከቱት ከሚከተሉት ክፍልፋዮች የቱ ነው?




ሀ. $\frac{1}{4}$ ለ. $\frac{1}{5}$ ሐ . $\frac{3}{4}$ መ. $\frac{4}{5}$

6. $\frac{1}{5} < \frac{1}{9}$ ሀ· እውነት ለ· ሀሰት

7. ከሚከተሉት የ30 ሲሶ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. 8 ለ.16 ሐ. 10 መ. ሁሉም

# ምዕራፍ 6 ንድፎች

የመማር ማስተማር ውጤቶች፣ ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ
- ቀጣይነት ያለውን ንድፎች ትረዳላችሁ::
- ተግባራዊ የንድፍ መልመጃዎችን ትሰራላችሁ::

መግቢያ

ንድፍን በተለያየ መንገድ መግለጽ ይቻላል:: የንድፍ ጽንሰ ሀሳብ በውስጡ የነገሮችን ማለትም የቁጥሮችን፣ የስዕሎችን፣ የቀለሞችና የተለያዩ አይነት የቁሶች ተመሳሳይነት ባለው ዘዴ መሰደር ወይም መደርደር እና ማደራጀትን ያካትታል::

## 6.1 ቀጣይነት ያላቸውን ንድፎች መለየት

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት
- እያደገ ያለ ንድፍን መለየት

ምሳሌ ሀ

የንድፍን ሀሳብ የበለጠ ለመረዳት ከታች ያለውን ስዕል ስንመለከት የመጀመሪያው የንድፉ አባል 1ኳስ ሲይዝ ሁለተኛው የንድፍ አባል 3ኳስ ይዟል :: እንዲሁም በሶስተኛው ላይ ያለው የንድፉ አባል 5ኳሶች ሲይዝ በአራተኛ ደረጃ ላይ ያለው አባል 7 ኳሶች ይዟል::



1 ኳስ 3 ኳስ 5 ኳስ 7 ኳስ

በተከታታይ ያሉትን የንድፉን አባላት ስንመለከት አንደኛው አባል ከሌላኛው አባል ያለውን ዝምድና መረዳት ይቻላል:: ይህም የሚያሳየን የንድፉ አባላት

- የመጀመሪያው አባል = 1
- ሁለተኛው አባል = 3 = 1+2
- ሶስተኛው አባል = 5 = 3+2
- አራተኛው አባል = 7 = 5 +2

ቀጣዩን አባል ለማወቅ ቅድሚያ ካለው አባል ላይ ሁለት በመደመር ነው::
የስዕሉን ንድፍ ወደ ቁጥር ንድፍ ስንቀይረው 1፣ 3፣ 5፣ 7፣ .... ይሆናል::
ስለሆነም ንድፉ እያደገ የሚሄድ ንድፍ ይባላል::

ማስታወሻ፡- የአንድ ንድፍ የመጀመሪያው የንድፍ አባል ከቀጣዩ የንድፍ አባል የሚያንስ ከሆነ ንድፉ እያደገ የሚሄድ ንድፍ ይባላል::

ምሳሌ ለ




+1 +2 +3 +4 +5

ከላይ ያለውን ንድፍ ስንመለከት የሚያሳየን የንድፉ አባላት

- የመጀመሪያው አባል = 25
- ሁለተኛው አባል = 26 = 25+1 ይህ ማለት የመጀመሪያው አባል +1
- ሶስተኛው አባል = 28 = 26+2 ይህ ማለት ሁለተኛው አባል + 2
- አራተኛው አባል = 31 = 28+3 ይህ ማለት ሶስተኛው አባል + 3
- አምስተኛው አባል = 35 = 31 + 4 ይህ ማለት አራተኛው አባል + 4
- ስድስተኛው አባል = 40 = 35 + 5 ይህ ማለት ስድስተኛው አባል + 5

የንድፉ አባላት በቅደም ተከተላቸው ሲሰደሩ 25፣ 26፣ 28፣ 31፣ 35፣ 40 ፣ ....ይሆናል:: ስለሆነም ንድፉ እያደገ የሚሄድ ንድፍ ይባላል::

ምሳሌ ሐ

3፣ 6፣ 9፣ 12፣ 15፣ ..... የቁጥር ንድፍ ስንመለከት ቀጣዩን አባል ለማወቅ ቅድሚያ ካለው አባል ላይ ሶስት መደመር ነው፡፡ስለሆነም ንድፉ እያደገ የሚሄድ ንድፍ ይባላል፡፡

**ማስታወሻ**

የተሰደረውን ንድፍ እያደገ የሚሄድ ንድፍ መሆኑን ለመለየት የንድፉን አሰዳደር መገንዘብና በመጀመሪያ ላይ የተቀመጠው የንድፍ አባል ቀጥሎ ከተቀመጠው የንድፍ አባል ያነሰ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

**መልመጃ ሀ**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች እያደጉ የሚሄዱ ንድፎች መሆናቸውን አረጋግጡ፡፡

ሀ. 11፣ 22፣ 33፣ 44፣ 55፣ 66፣ 77...

ለ. 2፣ 4፣6፣ 8፣ 10፣ 12፣ 14...

ሐ. 30፣ 40፣ 50፣ 60፣ 80፣ 90 ....

መ. 1፣ 3፣ 6፣ 10፣ 15 ....

ሠ. 11፣ 17፣ 23፣ 29፣ 35፣ 41፣ 47 ...

## 6.2 እያደገ ያለ ስዕላዊ ንድፍ ማስቀጠል

**የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት**

- እያደገ ያለ ስዕላዊ ንድፍን ማስቀጠል

ስዕላዊ ንድፍ የንድፍ አይነት ሲሆን የንድፍ አባላት በስዕል የተቀመጡ ሆነው አንዱ አባል ከሌላኛው አባል በውስጡ በሚይዘው የስዕል ብዛት ይለያያል፡፡ ቅርጽ ያላቸው ስዕላዊ ነገሮችን በመጠቀም ተመሳሳይነት ባለዉ ዘዴ ስዕላዊ ንድፎችን መፍጠር ይቻላል፡፡

ተግባር ሀ

1. ከታች ያለውን ስዕላዊ ንድፍ መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡



ሀ. በ4ኛ ደረጃ ላይ ያለው አባል

ስንት ድርድር ሳጥን ይዟል? 1ሳጥን 4ሳጥን 7ሳጥን

ለ. በ4ኛ ደረጃ ላይ ያለው አባል በስዕል ግለጹ፡፡

ምሳሌ ሀ.

ከታች ያለው ስዕላዊ ንድፍ መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡



ሀ. በ4ኛ ደረጃ ላይ ያለው አባል ስንት ድርድር ሳጥን ይዟል?

ለ. በ4ኛ ደረጃ ላይ ያለው አባል በስዕል ግለጹ፡፡

**መፍትሔ**

ሀ. የንድፍን ሀሳብ የበለጠ ለመረዳት ከላይ ያለውን ስዕል ስንመለከት የመጀመሪያው የንድፉ አባል 2 ሳጥን፣ ሁለተኛው የንድፍ አባል 4ሳጥን ሲይዝ በሶስተኛ ላይ ያለው የንድፉ አባል 6 ሳጥኖች ይዟል፡፡ ይህም የሚያሳየን በቀዳማዊና በተከታዩ አባላት መካከል የ2 ሳጥኖች ልዩነት ስለሆነ 4ኛ አባላቱ 8 ድርድር ሳጥኖች ይኖሩታል፡፡ ንድፉም እያደገ የሚሄድ ስዕላዊ ንድፍ ነው፡፡

ለ. 

<u>ምሳሌ ለ.</u>

ከታች ያለው ስዕላዊ ንድፍ መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

ሀ. በ5ኛ ደረጃ ላይ የምናገኘው የንድፍ አባል ስንት ማንጎዎች ይኖሩታል?

ለ. በ5ኛ ደረጃ ላይ የምናገኘውን የንድፍ አባል በስዕል ግለጹ፡፡



መፍትሔ

ሀ. ስዕሉን ስንመለከት አንድ የንድፍ አባል እጥፍ ሲሆን ቀጣይ የንድፍ አባሉን እናገኛለን፡፡ ስለዚህ በ5ኛ ደረጃ ላይ ያለው የንድፍ አባል ለማግኘት አራተኛ ደረጃ ላይ ያለውን የንድፍ አባል እጥፍ ማድረግ ነው፡፡ $2 \times 8 = 16$ ማንጎዎችን ይይዛል

ለ 

<u>ምሳሌ ሐ.</u>

ከታች ያለውን ስዕላዊ ንድፍ መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

ሀ. በ5ኛ ደረጃ ላይ ያለው አባል ስንት ድርድር ሳጥን ይይዛል?

ለ. በ5ኛ ደረጃ ላይ ያለውን አባል በስዕል ግለጹ፡፡



መፍትሔ ፡ ሀ.

- የመጀመሪያው አባል = 1ሳጥን
- ሁለተኛው አባል = 3ሳጥን = 1+2 ይህ ማለት የመጀመሪያው አባል + 2
- ሶስተኛው አባል = 6ሳጥን = 3+3 ይህ ማለት ሁለተኛው አባል + 3
- አራተኛው አባል = 10 ሳጥን = 6+4 ይህ ማለት ሶስተኛው አባል + 4

ስለዝህ በ5ኛ ደረጃ ላይ ያለው አባላቱ = አራተኛው አባላቱ + 5

= 10 + 5 = 15 ሳጥን

ለ. የስዕላዊ ንድፉን አባላት ስንመለከት ከቀዳሚው ስዕላዊ ንድፍ አባል ላይ በላይ ጎንና በቀኝ ጎን ሳጥኖችን ስንደረድር ተከታዩን ስዕላዊ ንድፍ አባል እናገኛለን፡፡



## መልመጃ ሀ

1. ከታች ያለው ስዕላዊ ንድፍ መሰረት በማድረግ ጥያቄዎች መልሱ፡፡

- በ4ኛ ደረጃ ላይ ያለው አባል ስንት ድርድር ሳጥን ይዟል?
- በ4ኛ ደረጃ ላይ ያለውን አባል በስዕል ግለጹ፡፡

ሀ. 

ለ. 

ሐ. 

## 6.3 ቀጣይነትና ተደጋጋሚነት ያላቸዉን የሩቅ አባላት ንድፎችን መተንበይ

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት

- የሚደጋገሙና የሚያድጉ ንድፎችን የሩቅ አባላት መተንበይ

ማስታወሻ:- ተደጋጋሚነት ያለው ንድፍ ሁለት ክፍሎች ሲኖሩት እነሱም ኮር እና አባላት ናቸው:: ኮር ትንሹ የንድፍ ክፍል ሲሆን እራሱን በመደጋገም ንድፉ እንዲቀጥል ያደርጋል::

ምሳሌ ሀ: 

__________________

ከስዕሉ ከስር የተሰመረበት አንድ አንበሳና ሁለት አጋዘን ስዕል በቅደም ተከተል እየደጋገምን ስንስል ተደጋጋሚነት ያለው ንድፍ ይመሰረታል :: ስለዚህ የተሰመረበት ስዕል የንድፉ ኮር ነው::

ምሳሌ ለ 482482482482482....... የዚህን ንድፍ ስንመለከት የ482ን ደጋግሞ በመጻፍ የንድፉን አባላት የሚያስቀጥል ስለሆነ ንድፉ እየተደጋገመ የሚሄድ ንድፍ ይባላል:: የንድፉ ኮር 482 ነው::

ምሳሌ ሐ 

ከላይ ያለውን ንድፍ ስንመለከት በቅደም ተከተል ቲማቲም፣ ዶሮና ማንጎ እየደጋገመ የሚቀጥል ንድፍ ስለሆነ የሚደጋገም ንድፍ እንለዋለን ::

የንድፉ ኮር = 

## መልመጃ ሀ

የሚከተሉትን ንድፎች ኮር በመለየት የሚደጋገሙ ንድፎች መሆናቸውን አብራሩ:

ሀ. 

ለ. 

ሐ. 

<u>ምሳሌ መ</u>

ሀ. 11 12 13 __15 16 __18 ንድፍ ስንመለከት የሚያሳየን የንድፉ አባላት

- የመጀመሪያው አባል = 11
- ሁለተኛው አባል = 12 = 11+1 ይህ ማለት የመጀመሪያው አባል + 1
- ሶስተኛው አባል = 13 = 12+1 ይህ ማለት ሁለተኛው አባል + 1

ይህም የሚያሳየን በቀዳማዩና በተከታዩ አባላት መካከል የ1 ልዩነት ያለ መሆኑን ነው:: ስለዚህ 11 12 13 14 15 16 17 18 ይሆናል

ለ. 20 30 _____ 50 ____70 ንድፉን ስንመለከት የሚያሳየን የንድፉ አባላት በቀዳማዩና በ ተከታዩ አባላት መካከል የ10 ልዩነት ያለ መሆኑን ነው::

ስለዚህ 20 30 40 50 60 70

## መልመጃ ሀ

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ያልተሟሉ የንድፍ አባላትን አሟሉ::

ሀ. 4 7 10 ___ 16 ____22

ለ. 4 5 7 14 19 25 ___

ሐ. 25 35 _____ 55 65 75

<u>ምሳሌ ሠ</u> ከታችያለውን ስዕል በማየት

ሀ . 6ኛ ላይ ያለው የንድፉ አባል ስንት ነጥቦች ይዟል?



1ኛ 2ኛ 3ኛ 4ኛ 5ኛ 6ኛ

መፍትሔ

የ1ኛ አባሉ ብዛት = 1

የ2ኛ አባሉ ብዛት = 3 = የ1ኛ አባሉ ብዛት + 2

የ3ኛ አባሉ ብዛት = 6 = የ2ኛ አባሉ ብዛት + 3

የ4ኛ አባሉ ብዛት = 10 = የ3ኛ አባሉ ብዛት + 4

የ5ኛ አባሉ ብዛት = 15 = የ4ኛ አባሉ ብዛት + 5

ስለዚህ የ6ኛ አባሉ ብዛት = የ5ኛ አባሉ ብዛት + 6 =15 + 6 = 21

<u>ምሳሌ ረ</u>

ሀ.3 7 11 15 19 .... በ10ኛ ደረጃ ያለው የንድፉ አባላት ስንት ነው ?

መፍትሄ

በቀዳማይ እና በተከታይ የንድፉ አባል መካከል ያለውን ዝምድና ስንመለከት ከ3 ይጀምርና ከቀዳማዩ ላይ 4ን በመደመር ተከታዩን እናገኛል፡፡

| ደረጃ | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ | 5ኛ | 6ኛ | 7ኛ | 8ኛ | 9ኛ | 10ኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አባል | 3 | 7 | 11 | 15 | 19 | 23 | 27 | 31 | 35 | 39 |

<u>ምሳሌ ሸ</u>

የሚከተሉትን እያደጉ የሚሄዱ የቁጥር ንደፎችን በመመልከት 50ኛ እና 100ኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ የንድፉን አባላት በተሰጠው ቀመር መሰረት ፈልጉ፡፡

ሀ. 2 4 6 8 10 12 . . .

በ×2 የንድፉ ቀመር ሲሆን "በ" ደግሞ የንድፉ አባል የሚገኝበትን ደረጃ አመልካች መቁጠሪያ ቁጥር ነው፡፡

ለ. 10 20 30 40 50 60 . . .

በ×10 የንድፉ ቀመር ሲሆን "በ" ደግሞ የንድፉ አባል የሚገኝበትን ደረጃ አመልካች መቁጠሪያ ቁጥር ነው፡፡

መፍትሄ

ሀ. የንድፉ ቀመር = በ×2

50ኛ የንድፍ አባሉን ለማግኘት በ×2 ከሚለው ቀመር ላይ 50ን በ "በ" ቦታ ተክቶ ማባዛት ነው፡፡ ስለዚህ 50ኛ የንድፉ አባል = 50×2 =100 ይሆናል

በተመሳሳይ ዘዴ 100ኛ የንድፍ አባል = 100 ×2 =200 ይሆናል

ለ. የንድፉ ቀመር = በ×10

50ኛ የንድፍ አባሉን ለማግኘት በ×10 ከሚለው ቀመር ላይ 50ን በ "በ" ቦታ ተክቶ ማባዛት ነው፡፡ ስለዚህ 50ኛ የንድፉ አባል = 50×10 =500 ይሆናል

በተመሳሳይ ዘዴ 100ኛ የንድፍ አባል = 100 ×10 =1000 ይሆናል

<u>አስተውሉ፡</u>- የአንድን ንድፍ የሩቅ አባል ለማወቅ በቀዳማይ እና በተከታይ የንድፉ አባል መካከል ያለውን ዝምድና መገንዘብ እና መለየት የግድ ነው፡፡

## መልመጃ ለ

1. የሚከተሉትን የንድፍ ጥያቄዎች የጎደሉትን የንድፍ አባላት በባዶ ቦታው ላይ ፃፉ፡፡

ሀ. 0 3 6 9 12 ___ ___ ___

ለ. 4 9 14 19 24 ___ ___ ___

ሐ. 5 10 20 40 80 ___ ___ ___

2. ንድፉ 11 12 14 _______ 21 26 ቢሆን ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ውስጥ በባዶ ቦታው ላይ በግባት ያለበት የቱነው?

ሀ . 17 ለ. 18 ሐ. 19 መ. 20

3. 4 8 12 16 20 . . . በ×4 የንድፉ ቀመር ሲሆን "በ" ደግሞ የንድፉ አባል የሚገኝበትን ደረጃ አመልካች መቁጠሪያ ቁጥር ቢሆን 1000ኛ የንድፍ አባሉን ፈልጉ፡፡

### ከንድፍ ጋር የተያያዙ ፕሮብሌሞች

የንድፍ ፅንሰ ሃሳብ በየእለት ተእለት እንቅስቃሴያችን ስለምንተገብረው እንደመነሻ ከታች ያለውን ምሳሌ ተመልከቱ፡፡

<u>ምሳሌ ሀ</u> 1. አቶ አለሙ በየቀኑ 20ብር ቢያስቀምጡ፤ በ5ኛው ቀን ላይ ጠቅላላ ምን ያህል ገንዘብ ይኖረዋል?

መፍትሔ

በ1ኛው ቀን ያለው ብር = 20 ብር

በ2ኛው ቀን ያለው ብር = 40 ብር = በ1ኛው ቀን ያለው ብር + 20

በ3ኛው ቀን ያለው ብር = 60 ብር = በ2ኛው ቀን ያለው ብር +20

በ4ኛው ቀን ያለው ብር = 80 ብር = በ3ኛው ቀን ያለው ብር + 20

በ5ኛው ቀን ያለው ብር = 100 ብር = በ4ኛው ቀን ያለው ብር + 20

<u>ምሳሌ ለ</u>

1. መምህርት ሮዳስ ለተማሪዎቿ በክፍል ቁጥራቸው ቅደም ተከተል መሰረት ሙዝ፣ ብርቱካንና ማንጎ ማደል ፈልጋ የሚከተለውን ዘዴ ተጠቀመች

| ተራ ቁጥር | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የፍራፍሬ | ሙዝ | ብርቱካን | ማንጎ | ሙዝ | ብርቱካን | ማንጎ | ሙዝ |

ከላይ ባለው ዘዴ ቅደም ተከተል መሰረት

ሀ. 10ኛ ተራ ቁጥር ያለው ተማሪ አህመድ ቢሆን የሚደርሰው የፍራፍሬ አይነት ምንድን ነው?

ለ. 15ኛ ተራ ቁጥር ያለችው ተማሪ ነቢያት ብትሆን የሚደርሳት የፍራፍሬ አይነት ምንድን ነው?

መፍትሔ

| ተራ ቁጥር | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፍራፍሬ | ብርቱካን | ማንጎ | ሙዝ | ብርቱካን | ማንጎ | ሙዝ | ብርቱካን | ማንጎ | ሙዝ |

ስለዚህ፣ ሀ. አህመድ 10ኛ ላይ ስላለ ሙዝ ይደርሰዋል

ለ. ነቢያት 15ኛ ላይ ስላለች ማንጎ ይደርሳታል

## መልመጃ ሐ

1. አቶ ቦጋለ በየቀኑ 15 ብር ቢያስቀምጡ፤ ማስቀመጥ በጀመሩ በ 10ኛው ቀን ጠቅላላ ያስቀመጡት የብር መጠን ምንያክል ነው?

2. መምህር አብይ ለተማሪዎቹ በክፍል ቁጥራቸው ቅደምተከተል መሰረት የትምህርት ቁሳቁስ ማለትም ደብተር፣ መፅሐፍና እስክብሪቶ ማደል ፈልጎ የሚከተለውን ዘዴ ተጠቀመ

| ተራ ቁጥር | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቁሳቁስ | ደብተር | መፅሐፍ | እስክብሪቶ | ደብተር | መፅሐፍ | እስክብሪቶ | ደብተር |

ከላይ ባለው ዘዴ ቅደም ተከተል መሰረት

ሀ. 8ኛ ተራ ቁጥር ላይ ያለው ተማሪ ጌታቸው ቢሆን ምን አይነት የትምህርት ቁሳቁስ ይደርሰዋል?

ለ. 12ኛ ተራ ቁጥር ላይ ያለችው ተማሪ ሀናን ብትሆን ምን አይነት የትምህርት ቁሳቁስ ይደርሳታ?

## የምዕራፍ ስድስት ማጠቃለያ

- የንድፍ ጽንሰ ሀሳብ በውስጡ የነገሮችን ማለትም የቁጥሮችን፣ የስዕሎችን፣ የቀለሞችና የማንኛውንም አይነት የቁሶች ተመሳሳይነት ባለው ዘዴ መስደር እና ማደራጀትን ያካትታል፡፡
- የተሰደረውን ንድፍ እያደገ የሚሄድ ንድፍ መሆኑን ለመለየት የንድፉን አሰዳደር መገንዘብና በመጀመሪያ ላይ የተቀመጠው የንድፍ አባል ቀጥሎ ከተቀመጠው የንድፍ አባል ያነሰ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡
- ስዕላዊ ንድፍ የንድፍ አይነት ሲሆን የንድፍ አባላቱ በስዕል የተቀመጡ ሆነው አንዱ አባል ከሌላኛው አባል በውስጡ በሚይዘው የስዕል ብዛት ይለያያል፡፡ ቅርጽ ያላቸው ስዕላዊ ነገሮችን በመጠቀም ተመሳሳይነት ባለዉ ዘዴ ስዕላዊ ንድፎችን መፍጠር ይቻላል፡፡
- ተደጋጋሚነት ያለው ንድፍ ሁለት ክፍሎች ሲኖሩት እነሱም ኮርና አባላት ናቸው፡፡ ኮርን ትንሹ የንድፍ ክፍል ሲሆን እራሱን በመደጋገም ንድፉ እንዲቀጣል ያደርጋል፡፡

## የምዕራፍ ስድስት ማጠቃለያ መልመጃ

ሀ. የሚከተሉትን የቁጥርና የቅርፃቅርፅ ንድፍ አሟሉ::

1. 0 4 8 ___ __ 20 24 ___32 36 __ 44

2. ♠ ☺ ● ♠ ☺ ●________

3. 18፣ 21፣ 24፣ 27፣ 30፣____፣___ ፣____፣____፣____፣___

4. 26፣ 35፣ 44፣ 53፣___፣ __፣___፣___፣____፣_____፣_____

5. 100፣ 108፣ 116፣ 124፣ 132፣ ___፣___፣___፣_____፣____

# ምዕራፍ 7 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት እና ማካፈል

የመማር ማስተማር ውጤቶች፣ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፣

እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ማባዛት ትችላላችሁ፡፡

እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ማካፍል ትችላላችሁ፡፡

## 7.1 የ1,000 ብዜቶችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ማባዛት

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት፣

- እስከ 10,000 ያሉ የ1000 ብዜቶችን በባለ አንድ ሆሄ ማባዛት

**ተግባር ሀ**

1. እስከ 10,000 ያሉ የ1000 ብዜቶችን ዘርዝሩ፡፡
2. የሚከተሉትን አባዙ፡፡

ሀ. 3,000×3 ለ. 2,000×5 ሐ.6,000×4 መ.4,500×3

<u>ምሳሌ</u> የሚከተሉትን አባዙ፡፡

ሀ.4,000×2 ለ.5,000×5 ሐ.6,000×3

<u>መፍትሔ</u>

ሀ. 4,000×2 የዚህን ውጤታቸው ለማግኘት 2ን በ 4 ማባዛት 2 × 4=8 ከውጤታቸው በስተቀኝ ሶስት ዜሮዎችን መፃፍ፡፡

4,000×2 = 2 × 4 × 1000

= 8000

ለ. 5,000×5 = 25,000

ሐ. 6,000×3 = 18,000

ማስታወሻ

የ1,000 ብዜቶችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ስታባዙ ከተሰጠው የ1,000 ብዜት ዜሮ ያልሆነውን ሆሄ በባለ አንድ ሆሄ ጋር አባዝቶ በስተቀኝ ሶስት ዜሮዎችን መፃፍ።

መልመጃ ሀ

1. የሚከተሉትን አስሉ።

ሀ.1 ×7,000 ለ.3,000× 3 ሐ.6,000× 2 መ .5,000× 3

## 7.2 የ10 እና የ100 ብዜቶችን በባለ አንድ ሆሄ ማካፈል

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት፣

የ10 እና የ100 ብዜቶችን በባለ አንድ ሆሄ ማካፈል

ተግባር ሀ

የሚክትሉትን አስሉ።

ሀ. 890÷10 ለ. 5,500÷5 ሐ. 8,800÷2 መ. 7,200÷3

ምሳሌ ሀ

የሚክትሉትን አስሉ።

ሀ. 700÷10 ለ. 2400÷4 ሐ. 8,000÷4 መ. 4,200÷2

መፍትሔ

ሀ. 700÷10

የ10 ወይም የ100 በዜቶችን ለ10 ስናካፍል የምናገኘው ውጤት የአንድ ቤት ሆሄውን ዜሮን በመተው መፃፍ ነው።

ስለዚህ 700÷10 =70

ለ. 2400÷4 እንዲሁም የ10 እና የ100 በዜቶችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር ስናካፍል ዜሮዎችን በመተው የቀሩተን ቁጥሮች ማካፍለ እና ዜሮዎቹን መፃፍ፡፡

ስለዚህ 2,400÷4 ስናካፍል 24 ÷4=6ን ካገኘን በኃላ ሁለቱን ዜሮዎች እንፅፋልን፡፡ መልሱም 600 ይሆናለ፡፡

ሐ. 8,000÷4 =2000

መ. 4,200÷2=2100

ነገር ግን ዜሮዎችን ትተን ስናካፍል ቀሪ ካለው እንዴት እንደሚካፈል 7.4 ላይ ትማራላችሁ፡፡

**መልመጃ ሀ**

1. የሚከትሉትን አስሉ፡፡

ሀ.800÷10 ለ. 6,000÷3 ሐ.7,200÷2 መ. 6,440÷4

## 7.3 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማባዛት

**የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት፣**

እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማባዛት

እስከ 1000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥር ማባዛት ቀደም ባሉት ምዕራፎች ተመራችኃል፡፡

**ተግባር ሐ**

የሚከተሉተን አስሉ፡፡

ሀ.120×3 ለ. 2,311×6 ሐ. 3,250×2 መ. 650×5

ከላይ የተሰጡትን የማባዛት ጥያቄዎች በተለያየ መንገድ መስራት ይቻላል ፡፡

1ኛ ማባዛት ደጋግሞ መደመር ሲሆን

120×3 = 120+120+120 =360

2ኛ ምዕራፍ 3 ላይ እንደተማራችሁት ሰንጠረዡ በመጠቀም ነው፡፡

3ኛ መንገድ ደግሞ ቁልቁል በመፃፍ ማባዛት ነው፡፡

<u>ምሳሌ ሐ</u>

የሚከተሉተን አስሉ፡፡

ሀ. 1,836×2 ለ. 2,582×3 ሐ. 5,416×3

መፍትሄ

ሀ.1,236×2 በመጀመያ ቁጥሩን ቁልቁል መፃፍ፡፡

ሀ 1836 ×2 =

| የሺ ቤት | የ100 ቤት | የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|---|---|
| 1 | | 1 | |
| 1 | 8 | 3 | 6<br>X2 |
| 3 | 6 | 7 | 2 |

አሰራር

1ኛ . በመጀመሪያ በአንድ ቤት ያለውን 6 ቁጥር በ2 እናባዛለን፡፡ 6x2=12

2ን በአንድ ቤት ስር ፅፈን 1ን በአስር ቤት ሳጥኑ አለን በማለት እንፅፋለን፡፡

2ኛ. በአስር ቤት ያለውን 3 ቁጥር በ2 እናባዛለን፡፡ 3x2=6 ባገኘነው ውጤት ላይ አለን ያልነውን 1 እንደምራለን፡፡ 6+1=7

3ኛ. በመቶ ቤት ያለውን 8 በ2 እናባዛለን፡፡8x2=16

6ን በመቶ ቤት ፅፈን 1ን አለኝ በማለት በሺ ቤት እንፅፋለን፡፡

4ኛ. በመጨረሻ በሺ ቤት ያለውን 1 ቁጥር በ 2 እናባዛለን:: 1x2=2 ባገኘነው ውጤት ላይ አለን ያልነውን 1 እንደምራለን:: 2+1=3

ውጤቱም $\begin{array}{r} 1836 \\ \times 2 \\ \hline 3672 \end{array}$ ከአንድ ቤት በመጀመር እያባዛን ብዜቱ ከአስር ከበለጠ ወደ ሚቀጥለው ቤት አለን በማለት በተቀመጠው ሳጥን እንፅፋለን::

ለ. 2582×3

| የሺ ቤት | የ100 ቤት | የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|---|---|
| 1 | 2 | | |
| 2 | 5 | 8 | 2<br>X3 |
| 7 | 7 | 4 | 6 |
| 2x3+1=7 | 3x5+2 | 8x3=24 | 2x3=6 |

ስለዚህ

2582×3

=7746

ሐ.1486×6

| | የ1000 ቤት | የ100 ቤት | የ10 ቤት | የ1 ቤት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | | | 1 | |
| | 5 | 4 | 1 | 6<br>X3 |
| 5 | 2 | 4 | 8 | |

ስለዚህ

$\begin{array}{r} 1486 \\ \times \\ \hline 15248 \end{array}$

## መልመጃ ሐ

1. የሚከተሉትን አስሉ::

ሀ. $\begin{array}{r} 1248 \\ \times\ 5 \end{array}$ ለ. $\begin{array}{r} 1235 \\ \times\ \ 4 \end{array}$ ሐ. $\begin{array}{r} 3250 \\ \times\ \ 3 \end{array}$ መ. $\begin{array}{r} 8212 \\ \times\ \ 2 \end{array}$

## 7.4 እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ እና በ10 ማካፈል

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት፣

- እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ እና በ10 ማካፈል

**ተግባር መ**

የሚከተሉትን በቡድን በቡድን በመሆን ስሩ።

ሀ.230÷2 ለ. 6,500÷10 ሐ. 825÷10

<u>ምሳሌ መ</u>

1. የሚከተሉትን አስሉ።

ሀ. 7,200÷10 ለ. 8,250÷10 ሐ. 6,789÷10 መ. 8,764÷10

መፍትሔ

ሀ. 7,200÷10 ማንኛውንም ሙሉ ቁጥር ለ10 ስናካፍል አንድ ቤቱ ዜሮ ከሆነ ያለ ቀሪ ይካፈላል። ድርሻውም የአንድ ቤት ዜሮውን በመተው መፃፍ ነው።

ስለዚህ 7200÷10 = 720

ለ. 8,250÷10 ይህም ቁጥር የአንድ ቤቱ ዜሮ ስለሆነ ያለ ቀሪ ይካፈላል። ውጤቱም 825 ይሆናል።

ሐ. 6,789÷10 የአንድ ቤት ዋጋው ዜሮ ካልሆነ ግን ፤አንድ ቤቱ ቀሪ የሆንና ከአንድ ቤት ውጪ ያለው ቁጥር ድርሻ ይሆናል።

ስለዚህ 6789÷10 = 678 እና ቀሪው ደግሞ 9 ይሆናል።

መ.8,764÷10 በተመሳሳይ 8764 የአንድ ቤት ከዜሮ የተለየ ስለሆነ ድርሻው 876 ሆኖ ቀሪው ደግሞ 4 ይሆናል።

## መልመጃ መ

1. የሚከተሉትን አስሉ፡፡

ሀ.3,420÷10    ለ. 9,980÷10    ሐ.1892÷10    መ. 3,888÷10

### ተግባር ሠ

የሚከተሉትን አስሉ፡፡

ሀ.846÷3    ለ.2,438÷3    ሐ.1,897÷8

### ምሳሌ ሠ

የሚከተሉትን አስሉ፡፡

ሀ. 786÷2    ለ.1352÷5    ሐ.7,680÷8    መ. 9834÷4

መፍትሔ

ሀ. 786÷2

ማካፈል ሁልጊዜም የሚጀምረው ከግራ ወደ ቀኝ ነው

7÷2=3 ቀሪ 1 ፣ 2x3=6ን ከ7 በታች እንፅፋለን:: በመቀጠል 7-6=1

```
      3
2 ) 786
    -6
     1
```

በመቀጠል ደግሞም ከ1 ጎን 8ን በማስቀመጥ 18 ለ2 እናካፍላለን:: ድርሻውም 9 በተመሳሳይ ዘዴ 6ንለ 2 እናካፍላለን ማካፈል የሚያልቀው በስተመጨረሻ 0 ወይንም ከአካፋዩ ያነሰ ቁጥር ስናገኝ ነው

```
    293
2 ) 786
    -6
    18
   -18
     6
     6
     0
```

ለ.

```
      270
5 | 1352
    -10
     35
    -35
      2
      0
      2
```

በመጨረሻ የሚቀረው ቁጥር ከአካፋዩ ያነሰ ከሆነ ቀሪ ይሆናል::

ሐ.

```
     960
8 | 7680
    72
     48
     48
      0
      0
      0
```

ማካፈል ስንጀምር ከግራ 7 ለ8 ስለማይካፈል ከ6 ጋር በማድረግ 76ን ለ 8 እናካፍላለን::

መ. 9834÷4

```
      2458
4 | 9834
    8
    18
    16
     23
     20
      34
      32
       2
```

2 ቀሪ እንላለን

ማስታወሻ

ሀ፣ለ፣መ እና በ ሙሉ ቁጥሮች ቢሆኑ ሀ÷ለ=መ ሆኖ ቀሪ በ ከሆነ

ሀ=ለ×መ+በ ሁልጊዜም እውነት ነው::ይህም ማለት የማካፈል ስሌት ማረጋገጥ እንደሚቻል ነው::

<u>ምሳሌ ረ</u> የሚከተሉተን አስሉ:: መልሱንም አረጋግጡ::

ሀ. 7652÷ 6 ለ. 2416÷8 ሐ. 4108÷9 መ. 1034÷ 7

መፍትሔ

ሀ. 7652÷ 6 = 1275 ቀሪ 2 ማረጋገጫ 1275× 6 +2= 7652

ለ. 2416÷8 = 302 ቀሪ0 ማረጋገጫ 302×8+0 = 2416

ሐ. 4108÷9=456 ቀሪ 4 ማረጋገጫ 456× 9 +4= 4108

መ. 1034÷ 7 =147 ቀሪ 5 ማረጋገጫ 147× 7 +5= 1034

## የምዕራፍ ሰባት ማጠቃለያ

- የ1,000 ብዜቶችን በባለ አንድ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ስታባዙ ከተሰጠው የ1,000 ብዜት ዜሮ ያልሆነውን ሆሄ በባለ አንድ ሆሄ ጋር አባዝቶ በስተቀኝ ሶስት ዜሮዎችን መፃፍ፡፡
- ማንኛውንም ሙሉ ቁጥር ለ10 ስናካፍል አንድ ቤቱ ዜሮ ከሆነ ያለ ቀሪ ይካፈላል፡፡ ድርሻውም የአንድ ቤት ዜሮውን በመተው መፃፍ ነው፣
- የአንድ ቤት ሆሄ ዋጋው ዜሮ ካልሆነ ግን አንድ ቤቱ ቀሪ የሆንና ከአንድ ቤት ውጪ ያለው ቁጥር ድርሻ ይሆናል፡፡
- ሀ፣ለ፣መ እና በ ሙሉ ቁጥሮች ቢሆኑ ሀ÷ለ=መ ሆኖ ቀሪ በ ከሆነ
- ሀ=ለ×መ+በ ሁልጊዜም እውነት ነው፡፡ይህም ማለት የማካፈል ስሌት ማረጋገጥ እንደሚቻል ነው፡፡

## የምዕራፍ ሰባት የማጠቃለያ መልመጃ

1.የሚከተሉትን እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልሱ፡፡

ሀ. 560 የመቶ በዜት ሙሉ ቁጥር ነው፡፡

ለ.የ100 ብዜቶች በ10 የካፈላሉ፡፡

ሐ.ሁለት ቁጥሮች ስናካፍል ሁልጊዜም ቀሪው ከአካፋዩ ያንሳል፡፡

2. የሚከተሉትን አስሉ፡፡

ሀ.2410×5 ለ.8712×6 ሐ.1825×9

3. የሚከተሉትን አስሉ፡፡መልሱንም አረጋግጡ፡፡

ሀ.3678÷3 ለ. 8230÷4 ሐ. 5005÷2 መ.3675÷6 ሠ.5685÷8

# ምዕራፍ 8 የመረጃ አያያዝ

የመማር ማስተማር ዉጤቶች ፣ ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፣

- ስዕላዊ ግራፎችን እንዴት እንደሚገለፁ ትረዳላችሁ፡፡
- ስዕላዊ ግራፎችን በነባራዊ ህይወታችሁ ላይ ትተገብራላችሁ፡፡

መግቢያ

መረጃ አያያዝ ማለት መረጃ መሰብሰብ፣ መረጃ ማንበብና መረጃ ማቅረብ ነው፡፡ መረጃ አያያዝ በህይወታችን ላይ በየቀኑ የምናከናውናቸውን ተግባራት ስድሮና ቀምሮ እያወዳደርን ለማስቀመጥ ይጠቅመናል፡፡ መረጃን የተለያየ ዘዴ በመጠቀም ማለትም በስዕል፣ በሰንጠረዥና በሌሎች መንገድ ልንገልፀው እንችላለን፡፡

## 8.1 ስዕላዊ ግራፎች

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት

- የፍራፍሬ ምስሎችን በመጠቀም ስዕላዊ ግራፎችን መስራት

ማስታወሻ፡- መረጃ ስንሰበስብ የምንጠቀምባቸው ዘዴዎች ጥያቄ በመጠየቅ፤ በምልከታ፤ሙከራ በመስራት፤ የተለያዩ ምንጮችን በማንበብ ነው፡፡

ተግባር ሀ

1. በክፍል ዉስጥ የሚገኙ ጓደኞቻችሁ የሚወዱትን የጨዋታ አይነት ጠይቁና መዝግቡ፡፡
1. ትምህርት ቤት ስትሄዱ የሚያስፈልጋችሁን የትምህርት መሳሪያ መዝግቡና ለክፍል ጓደኞቻችሁ በስዕል አቅርቡ፡፡
2. ከታች ያለው ሰንጠረዥ የሚገልፀው አበበ ለጓደኞቹ የሰጠውን የአናናስ ብዛት ነው፡፡ሰንጠረዡን በመመልከት የሚከተሉትን ጥያቄዎችን መልሱ፡፡

   ሀ. አበበ አናናስ በብዛት የሰጠው ለማን ነው?

   ለ. አበበ ትንሽ አናናስ የሰጠው ለማን ነው?

| የጓደኞቹ ስም | የአናናስ ብዛት በስዕል |
|---|---|
| ገብሬ |  |
| ዝናሽ |  |
| ሰሚራ |  |

**ማስታወሻ**

- ቀላል ስዕላዊ ግራፍ ተጠቅሞ ድርጊቶችን ወይም ክስተቶችን ለማሳየት መጀመሪያ መርጃዎችን መሰብሰብ እና ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡ ስዕላዊ ግራፍ እዉነታዎችን ወይም ድርጊቶችን በቀላሉ እንድንረዳ ያደርጋል፡፡ ስዕላዊ ግራፍ የተለያዩ መጠን ያላቸውን ነገሮች በስዕል ሊወክል ይችለል

<u>ምሳሌ ሀ</u> በአንድ የህፃናት መጫወቻ መሸጫ ሱቅ በአንድ ቀን የሸጣቸው የመጫወቻ እቃዎች በስዕል ከታች ያለውን ይመስላሉ፡፡

| የእቃው ስም | የእቃው ብዛት በስዕል |
|---|---|
| አሻንጉሊት |  |
| ሞተር ሳይክል |  |
| ዳክዬ |  |
| መኪና |  |

ሀ. ባለሱቁ በብዛት የሸጠው የዕቃ ስም ጥቀሱ፡፡

ለ. በብዛት ያልተሸጠው ዕቃ ስም ጥቀሱ፡፡

ሐ. በኩል መጠን የሸጣቸው የዕቃዎች ስም ጥቀሱ፡፡

መፍትሔ፡- ሀ. ዳክዬ ለ. ሞተር ሳይክል ሐ. አሻንጉሊትና መኪና

**ማስታወሻ፡- ስዕላዊ ግራፍ ማለት አንድን መረጃ በስዕል መግለፅ ማለትነው፡፡**

## መልመጃ ሀ

1. ከታች ያለው ሰንጠረዥ የሚያሳየን አይናለም ከሰኞ እስከ ዓርብ የተከለችውን የችግኞች ብዛት ነው፡፡ ስለዚህ ሰንጠረዡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

ሀ. አይናለም ብዙ ችግኝ የተከለችው በየትኛው ቀን ነው?

ለ. አይናለም ትንሽ ችግኝ የተከለችው በየትኛው ቀን ነው?



2. ከታች ያለው ሰንጠረዥ የሚገልፀው ፋጡማ ለጓደኞቿ የሰጠችውን የአፕል ፍሬ ብዛት ነው፡፡

| የጓደኞቿ ስም | የአፕል ፍሬ ብዛት በስዕል |
|---|---|
| ሜሮን |  |
| ሙሀመድ |  |
| ሚኪያስ |  |

ከላይ ያለውን ሰንጠረዥ በመመልከት የሚከተሉትን ጥያቄዎችን መልሱ፡፡

ሀ. ፋጡማ አፕል በብዛት የሰጠችው ለማን ነው?

ለ. ፋጡማ ትንሽ አፕል የሰጠችው ለማን ነው?

## 8.2 ስዕለዊ ግራፎችን ማንበብና መፃፍ

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃቶች

- መረጃን ከስዕላዊ ግራፍ ላይ ማንበብ
- በጣም ትልቁ፣ ትንሹንና የተደጋገመ መረጃ መለየት
- በትልቁና በትንሹ መካከል ያለዉን የመረጃ ልዩነት መናገር
- ባር ግራፎችን መስራትና ማንበብ

አንድን ስዕላዊ ግራፍ ዝርዝር ሁኔታ ለማንበብና ለመፃፍ የስዕሉን አይነት፣ መጠንና የተሰሩበትን ቁስ ወይም ባህሪያቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ተግባር ሀ

1. ከታች ያለው ስዕላዊ ግራፍ ልጆች በምሳ ሰዓት ላይ የሚጠጡትን መጠጥ ይገልፃል፡፡

ሀ. በስዕሉ መሰረት ወተት የሚጠጡ ልጆች ብዛት ስንት ናቸው?

ለ. በስዕሉ መሰረት ውሀወይም ወተት የሚጠጡት ልጆች ብዛት ስንት ናቸው?

የመጠጥ አይነት — የልጆች ብዛት በስዕል

ወተት



ጭማቂ



ውሀ



2. .ከታች ያለው ስዕላዊ ግራፍ ተማሪዎች የሚወዱትን ፍራፍሬ ይገልፃል፡፡

የፍራፍሬ አይነት — የተማሪ ብዛት

ማንጎ



አፕል



ሙዝ



ብርቱካን



ቁልፍ  = 2 ተማሪን ይወክላል  = 2 ተማሪን ይወክላል

 = 2 ተማሪን ይወክላል  = 2 ተማሪን ይወክላል

ከላይ ባለው ስዕላዊ ግራፍ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

ሀ. ማንጎ የሚወዱ ተማሪዎች ብዛት ስንት ነው?

ለ. ሙዝ የሚወዱ ተማሪዎች ብርቱካን ከሚወዱ ተማሪዎች በስንት ያንሳሉ?

ሐ. አፕል የሚወዱ ተማሪዎች ማንጎ ከሚወዱ ተማሪዎች በስንት ይበልጣሉ?

ማስታወሻ፡- የአንድን ስዕላዊ ግራፍ ስናነብ የምንከተለው መንገድ

- የስዕሉን አይነት መለየት፣ ስዕሉ የወከለውን መጠን መለየት የአንዱ የስዕል አይነት ከሌላኛው የስዕል አይነት ያለውን ዝምድና በቁጥር መፃፍ

ምሳሌ ሀ

ልዑል፣ ዘራይ፣ ሀምለት እና ጀሚላ ከቦንቱ የተበረከተላቸውን የበአል ስጦታ ብዛት ከታች ባለው ስዕላዊ ግራፍ ተገልጿል፡፡

ስም የስጦታ ብዛት

ልዑል

ዘራይ

ሀምለት

እናያ



ፍንጭ፡-  = 2 ስጦታ ይዟል

ከላይ ባለው ስዕላዊ ግራፍ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

ሀ. በብዛት ስጦታ የደረሰው ማን ነው?

ለ .ከጀሚላና ከሀምለት የበለጠ ስጦታ የወሰደ ማነው?

ሐ. ዘራይና ልዑል በጠቅላላ የወሰዱት ስጦታ ብዛት ስንት ነው?

መ. 6 ስጦታ የደረሰው ማነው?

ሠ.የዘራይ ስጦታ ብዛት ከ ሃምለት ስጦታ በስንት ይበልጣል?

መፍትሄ

ሀ. ዘራይ፤ ምክንያቱም ስዕላዊ ግራፉ ላይ ዘራይ 7×2 =14 ስጦታ ደርሶታል

ለ. እናያ ምክንያቱም ስዕላዊ ግራፉ እንደሚያሳየን እናያ 12 ስጦታ ሲደርሳት ሀምለት ግን 6 ስጦታ ደርሷታል፡፡

ሐ. 22 ስጦታ ምክንያቱም ስዕላዊ ግራፉ እንደሚያሳየን ዘራይ 14 ስጦታና ልዑል 8 ስጦታ ስለደረሳቸው፤ 14ስጦታ + 8ስጦታ = 22 ስጦታ

መ. ሀምለት ሠ. የዘራይስጦታ - የሀምለት ስጦታ =14 - 6 = 8

<u>ምሳሌ ለ</u>

አንድ የመኪና መሸጫ ካምፓኒ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ የተሸጡ የመኪናዎች ብዛት እንደሚከተለው በስዕላዊ ግራፍ ተቀምጧዋል፡፡

ቀን የመኪናዎች ብዛት

ሰኞ 

ማክሰኞ 

ረቡዕ 

ሐሙስ

ዓርብ

ቅዳሜ



1.ብዙ መኪናዎች የተሸጡበት በየትኛው ቀን ነው? ብዛቱ ስንት ነው?

2.ብዛታቸው እኩል የሆኑ መኪናዎች የተሸጡበት ቀን ዘርዝሩ?

3.ብዛታቸው በጣም ትንሽ መኪናዎች የተሸጡበት በየትኛው ቀን ነው?

4.በሁሉም ቀናቶች ጠቅላላ የተሸጡት የመኪና ብዛት ስንት ነው?

<u>መፍትሔ</u>

1.ከግራፉ እንደምትመለከቱት ብዙ መኪናዎች የተሸጡበት ቀን ማክሰኞ ነው፡፡

ከፍንጩ ላይ የ1 መኪና ስዕል 2 የተሸጡ መኪናዎችን ስለሚወክል 7 የመኪያ ስዕሎች 14 የተሸጡ መኪኖችን ይወክላል ስለዚህ 2×7 =14

2.ሰኞ እና ረዕቡ 3.ቅዳሜ 4. 54 ይሆናለ

## መልመጃ ሀ

1. ከታች ያለው ስዕላዊ ግራፍ በተለያዩ ሳምንታት ሄለን የሰራችውን የአሻንጉሊት ብዛት ይገልፃል፡፡ከታች ባለው ስዕላዊ ግራፍ መሰረት ጥያቄዎችን መልሱ፡፡

ሳምንት አሻንጉሊት

1ኛ ሳምንት

2ኛ ሳምንት



3ኛ ሳምንት 

4ኛ ሳምንት 

ፍንጭ  = 4 አሻንጉሊትን ይወክላል

ሀ. ሄለን 40 አሻንጉሊት የሰራችው በየትኛው ሳምንት ነው?

ለ. ሄለን ትንሽ አሻንጉሊት የሰራችው በየትኛው ሳምንት ነው?

ሐ. ሄለን በ4ኛው ሳምንት የሰራችው ከ3ኛ ሳምንት ከሰራችው በስንት ያንሳል?

መ. ሄለን በአጠቃላይ ባሉት ሳምንታት ስንት አሻንጉሊት ሰራች?

2. ሲፈን ያላትን የኩሽና እቃዎች አይነትና ብዛት ከታች ባለው ስዕላዊ ግራፍ ተገልጿል፡፡

የዕቃ አይነት ብዛት

ሲኒ 

ዝርግ ሳህን 

ድስት 

ከላይ ያለውን ስዕል በመመልከት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

ሀ. የእያንዳንዱን የኩሽና እቃ ብዛት ዘርዝሩ፡፡

ለ. የሲኒው ብዛት ከድስቱ ብዛት በስንት ይበልጣል?

3. ከታች ያለው ስዕላዊ ግራፍ በ2013 ዓ.ም በእትጌ መነን የልጃገረዶች አዳሪ ሁለተኛ ት/ቤት የነበሩ የሴት ተማሪዎችን ብዛት ይገልፃል፡፡




ከላይ ያለውን ስዕላዊ ግራፍ መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

ሀ. በያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ያለው የተማሪ ብዛት ስንት ነው?

ለ. የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት ከ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት በስንት ይበልጣል?

ሐ. የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት ከ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት በስንት ያንሳል?

## ባር ግራፍ

ባር ግራፍ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በቀላሉ ለማወዳደር የሚጠቅም የግራፍ አይነት ነው::ባር ግራፍ ቋሚ እና አግዳሚ ውስን መስመሮች በማገናኘት የሚሰራ ግራፍ ነው:: በቋሚ መስመሩ የመረጃ ብዛት ሲፃፍ በአግድም መስመሩ የመረጃ አይነት ይፃፋል::

ምሳሌ ሐ

| ነሀሴ 2013 ዓ. ም | |
|---|---|
| **ቀን** | **የሞቱ ሰዎች ብዛት** |
| 25 | 5 |
| 26 | 1 |
| 27 | 4 |
| 28 | 8 |
| 29 | 3 |

ከላይ ያለው ሰንጠረዥ በኢትዮጵያ በነሀሴ 2013 ዓ.ም ከ25/11/2013 ዓ.ም እስከ 29/11/2013 ዓ.ም ለተከታታይ 4 ቀናቶች በኮሮና ቫይረስ የሞቱ ሰዎች ብዛት የሚያሳይ ሰንጠረዥ በመጠቀም ባር ግራፍ ስሩ::

መፍትሔ:- ቁጥሮች በቋሚው መስመር ላይ ሲፃፉ እንዲሁም ቀናቶች በአግዳሚ መስመሩ ይፃፋሉ::



ምሳሌ መ

የሚከተለው ባር ግራፍ ከ1ኛ እስከ 4ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎችን ብዛት ያሳያል፡፡




የክፍል ደረጃ

ከላይ ያለውን ባር ግራፍ በማየት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

ሀ. የእያንዳንዱን ክፍል ተማሪዎች ብዛት ፃፉ?

ለ. በጣም ብዙ ተማሪዎች ያሉት በየትኛው ክፍል ነው?

ሐ .ትንሽ ቁጥር ተማሪዎች ያለው የትኛው ክፍል ነው?

መ. በአጠቃላይ ከ1ኛ እስከ 4ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ስንት ናቸው?

መፍትሄ

ሀ. 1 ኛ ክፍል 200፣2ኛ ክፍል 250፣3ኛ ክፍል 350፣ 4 ኛ ክፍል 150 ናቸው፡፡

ለ. በ3ኛ ክፍል

ሐ. በ4ኛ ክፍል

መ.950 ናቸው

## መልመጃ ለ

1. የሚከተሉትን መረጃዎች በመጠቀም ባር ግራፍ ሳሉ።

| የአትሌቶች ስም | ያገኙት የኦሎምፒክ ሜዳሊያ ብዛት |
|---|---|
| ሻለቃ ሃይሌ ገብረስላሴ | 2 |
| ቀነኒሳ በቀለ | 4 |
| ጥሩነሽ ዲባባ | 6 |
| መሰረት ደፋር | 2 |

2. ከታች የምትመለከቱት ባር ግራፍ የሚገልፀው ተማሪዎች በምሳ ሰአት የሚጠጧቸው የመጠጥ አይነቶች ናቸው ።




የመጠጥ አይነቶች

ከላይ ያለውን ባር ግራፍ በማየት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

ሀ. በብዛት የሚተጣው የትኛው መጠጥ ነው?

ለ.ሻይ የሚጠጡት ሚሪንዳ ከሚጠጡት በስንት ይበልጣሉ?

ሐ.ፋንታ የሚጠጡት ተማሪዎች ብዛት ስንት ናቸው?

መ.አጠቃላይ የተማሪዎች ብዛት ስንት ነው?

## የምዕራፍ 8 ማጠቃለያ

- ቀላል ስዕላዊ ግራፍ ተጠቅሞ ድርጊቶችን ወይም ክስተቶችን ለማሳየት መጀመሪያ መረጃዎችን መሰብሰብ እና ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡
- ስዕላዊ ግራፍ እዉነታዎችን ወይም ድርጊቶችን በቀላሉ እንድንረዳ ያደርጋል
- ስዕላዊ ግራፍ የተለያዩ መጠን ያላቸውን ነገሮች በስዕል ሊወክል ይችላል
- አንድን ስዕላዊ ግራፍ ዝርዝር ሁኔታ ለማንበብና ለመፃፍ የስዕሉን አይነት፣ መጠንና የተሰሩበትን ቁስ ወይም ባህሪያቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡
- የአንድን ስዕላዊ ግራፍ ስናነብ የምንከተለው መንገድ የስዕሉን አይነት መለየት፤ስዕሉ የወከለውን መጠን መለየትና የአንዱ የስዕል አይነት ከሌላኛው የስዕል አይነት ያለውን ዝምድና በቁጥር መፃፍ፡፡
- ባር ግራፍ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በቀላሉ ለማወዳደር የሚጠቅም የግራፍ አይነት ነው፡፡ባር ግራፍ ቋሚ እና አግዳሚ ውስን መስመሮች በተገናኙበት የሚሰራ ግራፍ ነው፡፡ በቋሚ መስመሩ የመረጃ ብዛት ይፃፋል፡፡በአግድም መስመሩ የመረጃ አይነት ይፃፋል፡፡

## የምዕራፍ 8 ማጠቃለያ መልመጃ

1. ከሰኞ እስከ ሐሙስ የተሸጡ የአበባዎችን ብዛትእንደሚከተለው በስዕላዊ ግራፍ ተቀምጠዋል፡፡

የተሸጡበት ቀን የአበባዎች ብዛት

ሰኞ

ማክሰኞ

ረቡዕ

ሐሙስ



ፍንጭ  = 2 አበባዎችን ይወክላል

ከላይ ያለውን ስዕላዊ ግራፍ መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ.

ሀ. በጣም ትንሽ የአበባ መጠን የተሸጠበት ቀንመቼ ነው?

ለ. ከፍተኛ የአበባ መጠን የተሸጠበትን ቀንጥቀሱ?

2. የሚከተለው ሰንጠረዥ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ለመሔድ ሚጠቀሙባቸው የመጓጓዣ መንገዶች መረጃ ያሳያል፡፡

የመጓጓዣ አይነት የተማሪዎች ብዛት

አውቶቡስ



የቤት መኪና 

በእግር 

<u>ፍንጭ</u>  =5 ተማሪዎች  = 3 ተማሪዎች  = 2 ተማሪዎች

ከላይ ባለው ስዕላዊ ግራፎች መሰረት

ሀ. በአውቶቡስ የሚጓዙ ተማሪዎች ብዛት ስንት ነው?

ለ. በእግር የሚጓዙ ተማሪዎች ብዛት ስንት ነው?

ሐ. በቤት መኪና የሚጓዙ ተማሪዎች ብዛት ስንት ነው?

መ. በአውቶቡስ የሚጓዙት በቤት መኪና ከሚጓዙ ተማሪዎች ብዛት በስንት ይበልጣል? በአጠቃላይ የተማሪዎች ብዛት ስንት ነው?

2. በአንድ ቀበሌ ውስጥ በ1 ዓመት የተወለዱ ልጆች በሚከተለው ስዕላዊ ግራፍ ተቀምጧዋል፡፡

የተወለዱበት ወር — የልጆች ብዛት

መስከረም 

ጥቅምት 

ህዳር 

ታህሳስ 




ፍንጭ  = 4 ህፃናትን ብዛት ወክሏል ከላይ ያለውን ስዕላዊ ግራፎች መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::

ሀ. በእያንዳንዱ ወር የተወለዱት ህፃናት ብዛት ስንት ነው?

ለ. በጠቅላላ በአንድ ዓመት ውስጥ የተወለዱ ህፃናት ብዛት ስንት ነው?

ሐ. በታህሳስ ወር የተወለዱት ህፃናት ብዛት በነሀሴ ወር ከተወለዱት ህፃን ብዛት በስንት ያንሳል?

3. የሚከተለው ባር ግራፍ የሚያሳየው ተማሪዎች የሚወዱትን የት/ም አይነት ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ ነው::




ከላይ ያለውን ባር ግራፍ በመልከት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::

ሀ. እንግሊዘኛ  የሚወዱ ተማሪዎች ብዛት ስንት ነው?

ለ. አብዛኛው ተማሪዎች የሚወዱት የትምህርት አይነት ምንድን ነው?

ሐ.በአጠቃላይ መረጃውን የሰጡ ተማሪዎች ብዛት ስንት ነው?

4. ከታች የምትመልከቱት ባር ግራፍ ከመጋቢት 8/2012 ዓ.ም እስንከ መጋቢት 12/2012 ዓ.ም አለማችን ላይ በኮሮና ቫይረስ የሞቱ ሰዎች ብዛት የሚያሳይ ነው:: ባር ግራፉን በመጠቀም  የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::




ሀ. ከፍተኛ  ኮሮና ቪይረስ የተያዙበት ቀን የቱ ነው?

ለ.ዝቅተኛ  ኮሮና ቫይረስ የተያዙበት ቀን የቱ ነው?

ሐ.ከ800 በላይ በቫይረሱ የተያዙበት ቀን ዘርዝሩ?

5. የትምህርት ቤታችሁን ሴት መምህራን ፣ወንድ መምህራን ፣ሴት የአስተዳደር ሰራተኞች እንዲሁም ወንድ የአስተዳደር ሰራተኞች ቁጥር በመውሰድ ባር ግራፍ ስሩ::

# ምዕራፍ 9 የጂኦሜትሪ ምስሎች

የመማር ማስተማር ውጤቶች ፡ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፣

- ምጥጥን መስመር ያላቸውንና የሌላቸውን ምስሎችን ትረዳላችሁ።
- የጂኦሜትሪ ምስሎችን በጎናቸው ቁጥር መሰረት መለየት ትችላላችሁ።
- የጂኦሜትሪ ምስሎችን ባህሪያት ትለያላችሁ።

**መግቢያ**

የጂኦሜትሪ ምስሎች የምንላቸው ነጥቦችና የተለያዩ መስመሮች አንድ ላይ ሆነው የሚሰሩት ምስል ነው። በዚህ ምዕራፍ የጂኦሜትሪ ምስሎችን ማንሸራተት፣ማዞር እና ማንፀባረቅ መለየት እንዲሁም ምጥጥን ያላቸው እና ምጥጥን የሌላቸውን መለየት፣ በጎናቸው መሰረት መሰየም እንዲሁም የጂኦሜትሪ ምስሎችን ማዕዘን፣ ጠርዝ እና የፊት ገፅታ መለየት እና መሰየም።

## 9.1 ማንሸራተት፣ማዞር እና ማንፀባረቅ በታወቀ ማዕዘን መተግበር

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት

- ማንሸራተት፣ማዞር እና ማንፀባረቅ በታወቀ ማዕዘን መተግበር

ተግባር ሀ የሚከተሉትን ተግባራት መስታወት ፊት ለፊት በመሆን ስሩ።

1. መስታወት ፊት ለፊት ቆማችሁ ቀኝ እጅ ስታነሱ ፤ መስታወት ውስጥ ያለው የእናንተት ምስል የትኛውን እጅ ነው የሚያነሳው?
2. በድጋሚ ቀኝ አይናችሁን ጨፍኑ፣መስታወት ውስጥ ያለው የእናንት ምስል የትኛው አይን ነው የተጨፈነው?



3. ምስሉን ደጋግማችሁ ካያችሁ መስታወት የምታፀዳው እናት በግራ እጇዎ እያፀዳች እንደሆነ ነው የሚያሳየው ነገር ግን መስታወት ውስጥ የሚታየው ምስል ግን በቀኝ እጇዋ ነው የምታፀዳው።

ምስሉ ማንሸራተት፣ማዞር እና ማንፀባረቅ መሆኑን ለዩ፡፡

ማስታወሻ:- የአንድ ምስል ስፋት እና ቅርፁ ሳይቀየር ከነበረበት ቦታ ሲንቀሳቀስ ሊንሸራተት፣ ወይም ሊታጠፍ ይችላል እንዲሁም አንድ ምስል ተንሸራተተ የምንለው ከነበረበት ቦታ ወደ ፊት፣ወደ ኋላ፣ወደ ታች ወይም ወደላይ ምስሉን በመግፋት ቦታ ስንቀይር ተንሸራተተ እንለዋለን።

ምሳሌ: ሀ



ከምስሉ እንደምትመለከቱት ከግራ ያለውን ሳጥን ከነበረበት ቦታ ወደ ፊት በማንቀሳቀስ በቀኝ ያለውን ሳጥን እናገኛለን ። ይህም በመንሸራተት ፅንሰ ሀሳብ ወደ ቀኝ ተንሸራተተ ይባላል፡፡

ምሳሌ ለ



ከላይ ያለው ምስል የሚያሳየው የመጀመሪያው ሶስት ማዕዘን ከነበረበት ወደ ቀኝ መንሸራተቱን ነው።

ማንፀባረቅ አንድን ነገር በመስታወት ምስሉን ስንመለከተው የሚታየን ምስል የተገለበጠ ነው።የአንድን ምስል ፅብረቃ ለማወቅ አንዱ ለሌላኛው በመስታወት ውስጥ የሚፈጠር ራር ተመሳሳይ ነው።

ምሳሌ:ሐ



ማዞር አንድ ምስል የመሽከርከር ባህሪ ካለው የምስሉ ዞረ እንላለን ።

ምሳሌ:መ



ምሳሌ

| | | |
|---|---|---|
| መንሸራተት |  |  |
| ማንፀባረቅ |  |  |
| ማዞር |  |  |

## መልመጃ ሀ

የሚከተሉትን ስዕሎች ማንሸራተታት፣ ማዞር ወይም ማንፀባረቅ ምሳሌዎች ናቸው በማለት መልሱ።

ሀ. 

ለ. 
ሐ. 

መ 
ሠ 
ረ 

## 9.2 ምጥጥን ቅርፅ ያላቸው እና የሌላቸውን መለየት

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት

- ምጥጥን የሆኑ እና ያልሆኑ ቅርፃችን መለየት

<u>ምሳሌ ሀ</u> የሚከተሉትን ስዕሎች በመመልከት ጥያቄዎችን መልሱ፡፡




ከላይ ካሉት ስዕሎች መካከል ከመስመሩ በግራ እና በቀኝ እኩል ክፍል የሌለው የቱ ነው?

መፍትሔ

ከላይ የተመለከታችኋቸው ስዕሎች ከተሰመረው መስመር በቀኝ እና በግራ ያለውን ስዕል ስናወዳድር ሀ፣ ለ እና ሐ ላይ ያሉ ምስሎች በቀኝ እና በግራ ያለው የስዕሉ ክፍል ተመሳሳይ ሲሆን መ ላይ ያለው ስዕል ግን ከመስመሩ ግራ እና ቀኝ ያለው የስዕሉ ክፍል የተለያየ ነው፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሀ፣ ለ እና ሐ ምስሎች ምጥጥን ያላቸው ምስሎች ይባላሉ ነገር ግን መ ላይ ያለው ስዕል ምጥጥን የሌለው ምስል ነው፡፡

ማስታወሻ፡- <u>ምጥጥን ቅርፅ ያላቸው</u> ምስሎች ቢያንስ በአንድ መስመር በተለያየ ጎን ያሉት ክፍሎች ተመሳሳይ ቅርፅ ሲኖራቸው ነው፡፡

<u>ምሳሌ፡</u> 


ተመሳሳይ ካልሆኑ <u>ምጥጥን ቅርፅ የሌላቸው</u> ይባላሉ፡፡

ምጥጥን ቅርፅ የሌላቸው ምስሎች ከአንድ መስመር በተለያየ ጎን ያለው የስዕሉ ክፍል የተለያየ ሲሆን ነው፡፡



ምሳሌ ሀ ከሚከተሉት ውስጥ ምጥጥን ቅርፅ ያላቸው እና ምጥጥን ቅርፅ የሌላቸው በማለት ለዩ፡፡

ሀ. 

ለ. 

ሐ. 

መ 

ሠ. 



ሰ. 

መፍትሔ

- ለ እና ሠ የምጥጥን ቅርፅ አላቸው፡፡ ምክንያቱም በተሰጠው ነጠብጣብ መስመር ግራ እና ቀኝ ያሉት የስዕሉ ክፍሎች ተመሳሳይ ናቸው፡፡
- ሐ የምጥጥን ቅርፅ አለው ምክንያቱም በተሰጠው ነጠብጣብ ከታች እና ላይ ያለው የስዕሉ ክፍል ተመሳሳይ ስለሆነ ነው፡፡
- ሰ የምጥጥን ቅርፅ አለው ምክንያቱም ከባህሩ በታች የሚታየው የተራራው ሙሉ ገፅታ ነው ስለዚህ ከላይ ያለው የተራራው ገፅታ ከባህሩ በታች በፅብረቃ ይታያል
- ሀ የምጥጥን ቅርፅ የለውም ምክንያቱም በነጠብጣብ መስመሩ በግራ እና በቀኝ ካሉት የስዕሉ ክፍሎች የአሻንጉሊቱን አፍንጫው ጋር በቀኝ እና በግራ የተለያየ ነው፡፡
- መ የምጥጥን ቅርፅ የለውም ምክንያቱም በነጠብጣብ መስመሩ በግራ እና በቀኝ ካሉት የስዕሉ ክፍሎች የአሻንጉሊቱን አፍንጫ ላይ በቀኝ እና በግራ የተለያዩ ናቸው፡፡ በተጨማሪ ደግሞ በግራ ያለው የጆሮው ክፍል ቀኝ ካለው የተለየ ነው፡፡
- ረ የምጥጥን ቅርፅ የለውም ምክንያቱም በነጠብጣብ መስመሩ በግራ እና በቀኝ ካሉት የቤቱ ክፍሎች በቀኝ እና በግራ የተለያየ ነው፡፡

## መልመጃ ለ

ከሚከተሉት ውስጥ በተሰጠው መስመር ምጥጥን ቅርፅ ያላቸው እና የምጥጥን ቅርፅ የሌላቸው በማለት ለዩ።

ሀ.



ለ.



ሐ.



መ.



ሠ.



ረ.



ሰ.



ቀ.



በ.



## 9.3 በጎናቸው መሰረት የጂኦሜትሪ ምስሎችን መለየት እና መሰየም

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት

- የጂኦሜትሪ ምስሎችን በስም መጥራት

### ተግባር ሐ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን ስሩ።



1. የደብተራችሁ ጎን ብዛት ስንት ነው?
2. የመማሪያ ክፍላችሁ ስንት ጎን አለው?
3. የምትመለከቷት ኮከብ ስንት ጎን አላት?

ማስታወሻ

የአንድን ጂኦሜትሪ ምስል ጎን ስንቆጥር እያንዳንዱን ቀጥታ መስመት መቁጠር ይኖርብናል ፡፡ አንድ ቀጥታ መስመር ማለት በሁለት መለያያ መካከል ያለው የመስመሩ ክፍል ነው፡፡

ከስዕሉ እንደምትመለከቱት ሁለቱ ቀስቶች የሚያመለክቱት የመስመሩንመለያያ ነው ፡፡ በሁለቱ መለያያ መካከል ያለው መስመር የጂኦሜትሪ ምስሉ አንድ ጎን ነው፡፡






ሀ፣ለ እና ሐ የጂኦሜትሪ ምስሉ መለያያ ናቸው፡፡

በእያንዳንዳቸው መለያያ መካከል ያለው መስመር የጂኦሜትሪው ምስል ጎኖች ይባላሉ፡፡ስለዚህ በጂኦሜትሪ ምስሉ የምትመለከቱት ሶስት ጎን

ስላለው ጎነ ሶስት በማለት እንጠራዋለን፡፡

<u>ምሳሌ ለ</u>

| የጂኦሜትሪ ምስል | የጂኦሜትሪ ምስሉ ስም | የጎን ብዛት | የመለያያ ብዛት |
|---|---|---|---|
|  | ጎነ አራት | አራት<br>እነሱም ሀለ፣ሀመ ለሐ እና ሐመ ናቸው:: | አራት መለያያ<br>እነሱም ሀ፣ለ፣ሐ እና መ |
|  | ጎነ ስድስት | ስድስት<br>ጎን ሀለ፣ለሐ፣ሐመ፣ መሠ፣ሠረ እና ረሀ | ስድስት<br>መለያያ<br>ሀ፣ለ፣ሐ፣መ፣ሠእናረ |

**ማስታወሻ**

የአንድ ጂኦሜትሪ ምስል የመለያያ እና የጎን ብዛታቸው እኩል ነው::

## መልመጃ ሐ

1. የሚከተሉትን ስዕሎች በመመልከት ሰንጠረዡን አሟሉ።

| የጂኦሜትሪ ምስል | የጂኦሜትሪ ምስሉ ስም | የጎን ብዛት | የመለያያ ብዛት |
|---|---|---|---|
|  | ጎነ አምስት | 5 | 5 |
|  | | | |
|  | | | |
|  | | | |

## 9.4 የጂኦሜትሪ ቅርፆችን ባህሪያት ማደራጀትና መሰየም

የንዑስ ርዕስ የመማር ብቃት

- የጂኦሚትሪ ምስሎችን ባህሪያት መገንዘብ

### ተግባር መ

በቡድን በቡድን በመሆን ስሩ።

1. ጠጣር ጂኦሜትሪች ምስሎች ምን እንደሚመስሉ እና እንዴት እንደምንለያቸው ተወያዩ።

2. የመማሪያ ክፍላችሁ ስንት ጠርዝ እና ማዕዘን አለው?

**ማስታወሻ፡-** ጠጣር ጂኦሜትሪች ምስሎች የምንላቸው ርዝመት፣ወርድ እና ቁመት ያላቸው ምስሎች ናቸው። ወይም ደግሞ ጠጣር ነገሮች የምንላቸው የሚዳሰሱ እና የሚጨበጡ ነገሮች ናቸው።

ምሳሌ ሐ የሚከተለውን ምስል በመጠቀም ጠርዝ፣ማዕዘን እና ገፅ ለዩ::







መፍትሔ

ሀ. የጠጣር ጂኦሜትሪክ ምስል ጠፍጣፋው ክፍል የጂኦሜትሪ ምስሉ ገፅ ይባላል ሁለት ገፆች የሚገናኙበት መስመር ጠርዝ ሲሆን ሶስት እና ከሶስት በላይ ጠርዞች የሚገናኙበት ደግሞ ማዕዘን ይባላል::




የጎን ገፅ ብዛት= 6 የጠርዝ ብዛት = 12 የማዕዘን ብዛት = 8




ከስዕሉ እንደምትረዱት ሶስት ገፆች ይታያሉ ቀሪዎቹ 3ቱ ደግሞ ከሚታዩት በተቃራኒ የሚገኙ ናቸው::ማዕዘናት ደግሞ ከላይ አራት ከታች አራት ማዕዘናት በአጠቃላይ 8 ማዕዘናት አሉ:: እንዲሁም 12 የጠርዝ ብዛት አሉ:: የቾክ መያዣ በመውሰድ ምን ያክል ማዕዘን፣ጠርዝ እንዲሁም ገፅ እንዳለው በመቁጠር አረጋግጡ::

ለ. 


❖ <u>የጎን ገፅ ብዛት= 7</u>

5ቱ ዙሪያውን ያሉት ገጾች ሲሆኑ ሁለቱ ደግሞ ከታች እና ከላይ ያሉት ናቸው ::

❖ የጠርዝ ብዛት = 15

5ቱ ቋሚ ጥርዞች ፣5ቱ የላይኛው ገፅ ጠርዞቸ እንዲሁም 5 የታችኛው ገፆች ጠርዞች ናቸው::

❖ የማዕዘን ብዛት = 10

5ቱ የላይኛው ገፅ ላይ ሲገኙ 5ቱ ደግሞ የታችኛው ገፅ ላይ ይገኛሉ በምሳሌ 1 ቁጥር በሰዕሉ የሚያመለክተው አይነት ነው::

## መልመጃ መ

ከታች ያለውን ሰንጠረዥ ሙሉ

| የጂኦሜትሪ ምስል | የማዕዘን ብዛት | የጠርዝ ብዛት | አጠቃላይ የገፅ ብዛት |
|---|---|---|---|
|  | | | |
|  | | | |
|  | | | |
|  | | | |

## የምዕራፍ 9 ማጠቃለያ

- አንድ ምስል ቦታውን ሲቀይር ማንሸራተታት፣ ማዞር ወይም ማንፀባረቅ የሚሉት ለውጦችን ልይዝ ይችላል።

አንድ ምስል ተንሸራተተ የምንለው ከነበረበት ቦታ ወደ ፊት፣ወደ ኋላ፣ወታች፣ወላይ በተለያየ አቅጣጫ ምስሉን በመግፋት ቦታ ስንቀይር ተንሸራተተ እንለዋለን።

ማንፀባረቅ አንድን ነገር በመስታወት ምስሉን ስንመለከተው የሚታየን ምስል የተገለበጠ ነው።የአንድን ምስል ግልበጣ ለማወቅ አንዱ ለሌላኛው በመስታወት ውስጥ የሚፈጠር ምስል ነው የሚመስሉ።

ማዞር አንድ ምስል የመሽከርከር ባህሪ ካለው የምስሉ እጥፋት ነው።

- ምጥጥን የሆኑ እና ያልሆኑ ቅርፃችን መለየት
- ጠጣር ጂኦሜትሪች ምስሎች የምንላቸው ርዝመት፣ወርድ እና ቁመጥ ያላቸው ምስሎች ናቸው። ወይም ደግሞ ጠጣር ነገሮች የምንላቸው የሚዳሰሱ እና የሚጨበጡ ነገሮች ናቸው።
  - የጠጣር ጂኦሜትሪክ ምስል ጠፍጣፋ ክፍል የጂኦሜትሪ ምስሉ ገፅ ይባላል ።
  - ሁለት ገፆች የሚገናኙበት መስመር ጠርዝ ይባላል።
  - ሶስት እና ከሶስት በላይ ጠርዞች የሚገናኙበት ደግሞ ማዕዘን ይባላል።

## የምዕራፍ 9 የማጠቃለያ መልመጃ

1. የሚከተሉትን ስዕሎች ማንሸራተት፣ ማንፀባረቅ ወይም ማዞር ምሳሌዎች ናቸው በማለት መልሱ፡፡



ሀ.



ለ.



ሐ.



መ.



ሠ.

2. ምጥጥን የሆኑ እና ያልሆኑ ቅርፆች በማለት መልሱ፡፡



ሀ



ለ



ሐ.



መ.



ሠ.



ረ

3. የጂኦሜትሪ ምስሎችን ጠርዝ፣ማዕዘን እና ገፅ ብዛት ፃፉ፡፡

ሀ

ጠርዝ ብዛት=______

የማዕዘን ብዛት=___

የገፆች ብዛት = ___



ለ

ጠርዝ ብዛት=______

የማዕዘን ብዛት=___

የገፆች ብዛት = ___



# ምዕራፍ 10 ልኬት፣ ርዝመት፣ መጠነቁስ እና ይዘት

የመማር ማስተማር ውጤቶች፣ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፣

- ተማሪዎች ርዝመት ፣መጠነቁስና ይዘትን ይረዳሉ፣ለእያንዳዳቸው ትክክለኛ የመለኪያ ምድብ ትለያላችሁ ::
- መሰረታዊ የመለኪያ አሀዶች የመለካት ጥቅሞች ይረዳሉ፣ባህላዊ እና ሜትሪክ ሲስተም ጋር መሰረታዊ የመለኪያ ምድቦች ጋር በደንብ ትተዋወቃላችሁ::
- ልኬቶችን በመጠቀም ቀላል የምድብ ቅይይሮችን ትሰራላችሁ::

መግቢያ

ልኬት ማለት የአንድ ነገር መጠን ወይም ብዛት ነው፡፡ከዚህ ምዕራፍ የርዝመትን፣ የመጠነቁስንና የይዘትን ልኬት በተለያየ የልኬት መሳሪያዎችና በተለያየ አሃዶች በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

## 10.1 ርዝመትን ፣በሚ.ሜ፣በሳ.ሜ፣በሜ እና በኪ.ሜ መለካት

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት

- የርዝመት መለኪያ ምድቦችን መለየት

ተግባረ ሀ

1. ከዚህ በታች ያሉትን ስዕሎች ተመልከቱና ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መልሱ::



ቡለን



ማስመሪያ

ሀ. ከማስመሪያው እና ከቡለኑ በርዝመቱ የሚበልጠው የቱ ነው?

ለ. ርዝመቱን በምን ለክታችሁ አወቃችሁ? ያወቃችሁበትን መንገድ አብራሩ::

2. የሚከተሉትን መሳሪያዎች ባህላዊ ወይም ዘመናዊ የርዝመት መለኪያ በማለት ለዩ ::




ማስታወሻ:- ባህላዊ የርዝመት መለኪያ ዘዴዎች አሁንም እያገለገሉ ቢገኙም ወጥነት ስለሌላቸው መሰረታዊ የርዝመት መለኪያ ዘዴዎችን መጠቀም የተሻለ ነው። ከእነዚህም ከመሰረታዊ የመለኪያ ምድቦች መካከል ሚሊ ሜትር፣ሳንቲ ሜትር፣ሜትር እና ኪሎ ሜትር ይገኙበታል::ርዝመታቸው አነስተኛ የሆኑ ነገሮችን ርዝመት ለመለካት የምንጠቀመው ምድብ ሚሊ ሜትርና ሳንቲ ሜትር ሲሆን፤ ርዝመታቸው ከፍ ያሉ ነገሮችን ርዝመትና የቦታዎችን ርቀት ለመለካት ፣ሜትርና ኪሎ ሜትር እንጠቀማለን። ለምሳሌ የእርሳስ ርዝመት፣የላፒስ ርዝመት የመሳሰሉትን በሳ.ሜ ስንገልፅ የሰው ቁመት፣የመስኮት በር ቁመት፣ዴስክ የመሳሰሉትን ደግሞ በሜትር እና በሳንቲ ሜትር እንገልፃለን እንዲሁም የመንገድን ርቀት ለመለካት ደግሞ ኪሎ ሜትርን እንጠቀማለን።

- ሚሊ ሜትር በአጭር ሲፃፍ ሚ.ሜ ይሆናል::
- ሳንቲ ሜትር በአጭር ሲፃፍ ሳ.ሜ ይሆናል::
- ሜትር በአጭር ሲፃፍ ሜ ይሆናል::
- ኪሎ ሜትር በአጭር ሲፃፍ ኪ.ሜ ይሆናል::

ምሳሌ ለ የሚከተሉትን ልኬቶች አንብቡ።

ሀ. 

ለ. 

መፍትሔ፡ ልኬትን በማስመሪያ ሲለኩ ከግራ በመጀመር የቀኝ መጨረሻ ማንበብ።

ሀ. 7 ሳ.ሜ ለ. 5 ሳ.ሜ ከ5 ሚ.ሜ ወይም 5 ከ ግማሽ ሳ.ሜ

**መልመጃ ሀ**

1. የሂሳብ ደብተራችሁን ጠርዝ በማስመሪያ ለኩ እና ዉጤቱን በሳንቲ ሜትር አስቀምጡ።
2. ከትምህርት ቤት እስከ ቤታችሁ ያለውን ርቀት በምን መለካት ይቻላል?
3. በሁለት ከተሞች መካከል ያለውን ርቀት በምን መለካት ይቻላል?
4. የጊታሩን ርዝመት አንብቡ።



## 10.2 የርዝመት አሀዶችን ወደ አንስተኛ አሀድ መቀየር

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት

➢ የርዝመት አሀዶችን ወደ አንስተኛ አሀድ መቀየር

ማስታወሻ :- በርዝመት መለኪያ ምድቦች መካከል ያለው ዝምድና

1 ሳ.ሜ = 10 ሚ.ሜ

1 ሜ = 100 ሳ.ሜ

1 ኪ.ሜ = 1000 ሜ

ርዝመትን ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ ምድብ ለመቀየር

ከኪሎ ሜትር ወደሜትር ለመቀየር በ 1000 ማባዛት::

ከ ሜትር ወደሳንቲ ሜትር ለመቀየር በ 100 ማባዛት::

ከ ሳንቲሜትር ወደ ሚሊ ሜትር ለመቀየር በ 10 ማባዛት::

<u>ምሳሌ ሐ</u>

1. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች ሙሉ::

ሀ.4 ሳ.ሜ= ——ሚ.ሜ  ለ.8 ሜ = —— ሳ.ሜ

ሐ. 2 ኪ.ሜ= —— ሜ  መ .5ሜ = ——ሳ ሜ

መፍትሔ

ሀ.4ሳ.ሜ = 4×10 ሚ.ሜ

= 40 ሚ.ሜ

ለ. 8ሜ = 8×100ሳ.ሜ

= 800 ሳ.ሜ

ሐ. 2 ኪ.ሜ =2×1000ሜ

=2000ሜ

መ .5ሜ =5×100 ሳ ሜ

= 500ሳ ሜ

## መልመጃ ሀ

1. የሚከተሉትን ከአንደኛው ወደ ሌላኛው ምድብ ቀይሩ፡፡

ሀ. 3 ሜ= ——ሳ.ሜ ለ. 6 ኪ.ሜ =———ሜ

ሐ. 7ሳ.ሜ =———ሚ.ሜ መ. 3 ሜ=—ሚ.ሜ

## 10.3 መጠነቁስ በሚሊግራም፣ ግራም፣ ኪሎ ግራም እና በኩንታል መለካት

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት

- የትናንሽ ቁሶችን መጠነቁስ መለካት

ተግባር ሐ 1. ተማሪዎች እያንዳንዳችሁ መጠነቁስ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

2. መጠነቁሳችሁን በምን አወቃችሁ ፤የአወቃችሁበትን መንገድ ተወያዩ፡፡

ማስታወሻ :- የመጠነቁስ አሀዶች በአጭሩ ሲፃፉ

- ሚሊ ግራም በአጭር ሲፃፍ ሚ.ግ ይሆናል፡፡
- ግራም በአጭር ሲፃፍ ግ ይሆናል ፡፡
- ኪሎ ግራም በአጭር ሲፃፍ ኪ.ግ ይሆናል፡፡

ሚዛን የአንድን እቃ መጠነቁስ ለመለካት የሚያገለግል መሳሪያ ነው፡፡

- ግራም ቀላል መጠነቁስ ያላቸውን ነገሮች ለመለካት የምንጠቀምበት የመጠነቁስ መለኪያ ምድብ ነው፡፡
- ኪሎ ግራም መጠነቁሳቸው ከፍ ያሉ እቃዎችን ለመለካት የምንጠቀምበት የመጠነቁስ መለኪያ ምድብ ነው፡፡

ምሳሌ መ   ከታች የምትመለከቱትን የብርቱካን መጠነቁስ አንብቡ።

የምትመለከቱት ሚዛን ዲጂታል ሚዛን ሲሆን በቀጥታ ቁጥር ጠቋሚውን ስናነብ መጠነቁሱ 300 ግራም ነው፡፡



## 10.4 የመጠነቁስ አሀዶችን ወደ አነስተኛ አሀድ መቀየር

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት

- የመጠነቁስ አሀዶችን ወደ አነስተኛ አሀድ መቀየ

በመጠነቁስ መለኪያ ምድቦች መካከል ያለ ዝምድና

1000 ሚ.ግ = 1 ግ

1000 ግ= 1 ኪ.ግ

100 ኪ.ግ = 1 ኩንታል

መጠነቁስን ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ ምድብ ለመቀየር

ከኩንታል ወደ ኪ.ግ ለመቀየር በ 100 ማባዛት።

ከኪሎ ግራም ወደ ግራም ለመቀየር በ 1000 ማባዛት።

ከ ግ ወደ ሚሊ ግራም ለመቀየር በ 1000 ማባዛት።

ምሳሌ መ

1. የሚከተሉትን ከግራም ወደ ሚሊ ግራም ለውጡ።

ሀ. 3 ግ ለ.5 ግ

2. የሚከተሉትን ከኪሎ ግራም ወደ ግራም ለውጡ።

ሀ. 6 ኪ.ግ ለ. 2 ኪ.ግ

3. የሚከተሉትን ከኩንታል ወደ ኪሎ ግራም ለውጡ።

ሀ.4 ኩንታል ለ.8 ኩታል

መፍትሔ 1. ሀ. 3ግ = 3×1000 ሚ.ግ ለ. 5ግ = 5×1000 ሚ.ግ

= 3000 ሚ.ግ = 5000 ሚ.ግ

2. ሀ. 6 ኪ.ግ = 6×1000 ግ = 6000 ግ ለ. 2 ኪ.ግ = 2×1000 ግ = 2000 ግ

3. ሀ. 4 ኩንታል = 4×100 ኪ.ግ ለ. 8 ኩንታል = 8×100 ኪ.ግ

= 400 ኪ.ግ = 800 ኪ.ግ

## መልመጃ ሀ

1. የሚከተሉትን ከግራም ወደ ሚሊ ግራም ለውጡ።

ሀ. 2 ግ ለ. 6 ግ ሐ. 9 ግ

2. የሚከተሉትን ከኪሎ ግራም ወደ ግራም ለውጡ።

ሀ.3 ኪ.ግ ለ.8 ኪ.ግ ሐ. 9 ኪ.ግ

3. የሚከተሉትን ከኩንታል ወደ ኪሎ ግራም ለውጡ።

ሀ. 6 ኩንታል ለ. 15 ኩንታል ሐ. 20 ኩንታል

4. አንድ የጭነት መኪና 10 ኩንታል ጤፍ ፣30 ኩንታል ስንዴ እና 15 ኩንታል ምስር ጭኖ ቢጓዝ መኪናው በአጠቃላይ የጫነው ስንት ኩንታል ነው?

5.በስእሉ የሚታየው የእቃው መጠነቁስ ስንት እንደሆነ ደምራችሁ አስቀምጡ::




6.አንድ የሸንኩርት ነጋዴ 15 ኩንታል ወደ ገበያ ይዞ ቢወጣ እና 12ቱን ኩንታል ቢሸጥ ስንት  ኩንታል ሸንኩርት ይቀረዋል?

## 10.5 ይዘትን በሚሊ ሊትር እና በሊትር መለካት

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት

- ይዘት በሚሊ ሊትር እና በሊትር መለካት

ተግባር ሀ

1.የተለያዩ ፈሳሾችን ለመያዝ የምትጠቀሙባቸውን እቃዎች ዘርዝሩ::

2.በየአካባቢያችሁ የምትጠቀሙትንየይዘት መለኪያ መሳሪያዎችን ዘርዝሩ::

ማስታወሻ

- አንድ የፈሳሽ መያዣ እቃ ሊይዝ የሚችለው ከፍተኛ የፈሳሽ መጠን የእቃው ይዘት ይባላል::
- ሚሊ ሊትር(ሚ.ሊ) አነስተኛ የፈሳሽ መጠንን ለመለካት የምንጠቀምበት የፈሳሽ መለኪያ ምድብ ነው::
- ሊትር(ሊ) ከፍተኛ የፈሳሽ መጠን ለመለካት የምንጠቀምበት ምድብ ነው::

## 10 .6 የይዘትአሃዶችን ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ መቀየር

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት

➢ የይዘት አሃዶችን ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ መቀየር

1000 ሚሊ ሊትር = 1 ሊትር

ምሳሌ ሀ    የሚከተሉትን ከሊትር ወደ ሚሊ ሊትር ቀይሩ::

ሀ. 2ሊ= 2×1000ሚ.ሊ. = 2000ሚ.ሊ.

ለ. 4ሊ. = 4×1000ሚ.ሊ. = 4000ሚ.ሊ.

ሐ.13ሊ. = 13×1000ሚ.ሊ. = 13000ሚ.ሊ.

**መልመጃ ሀ**

1.የሚከተሉትን ወደ ሚሊ ሊትር ቀይሩ::

ሀ. 5 ሊትር    ለ. 8 ሊትር    ሐ. 9 ሊትር    መ.12ሊ.

ርዝመት፣ መጠነቁስና ይዘት የያዙ ተግባራዊ የቃላት ፐሮብሌሞች

**ተግባር ሀ**

1. አንድ ባለሱቅ 280 ሜ ርዝመት ያለው የኤሌክትሪክ ጥቅል ሽቦ አለው፤ለአንዱ ደንበኛ 35ሜ፣ለሌላው ደንበኛ 24 ሜ ሸጠ::

ሀ. በአጠቃላይ ምንያክል የኤሌክትሪክ ሽቦ ሸጠ?

ለ. በጥቅሉ ምንያክል ሽቦ ይቀረዋል?

2 አንድ ነጋዴ ቅዳሜ 500 ኪ.ግ ፣ እሁድ ደግሞ 135 ኪ.ግ ስንዴ ሸጧል፤ በሁለቱ ቀን ውስጥ ስንት ኪ.ግ ስንዴ ሸጠ?

<u>ምሳሌ ለ</u>

1. የአንድ ቁም ሳጥን 45 ሳ.ሜ ቁመት አለው፣ሌላ ቁም ሳጥን ደግሞ 32 ሳ.ሜ ቁመት አለው፣ሁለቱ አንዱ በአንዱ ላይ ቢደራረቡ ሳጥኖቹ ምንያክል ቁመት ይኖራቸዋል?

2. አበበ 3 ኪሎ ግራም ፍራፍሬ የሚመዝን እና ከድር ደግሞ 2000 ግራም የሚመዝን ፍራፍሬ ቢይዙ ከባድ ፍራፍሬ የያዘው ማን ነው?

3.ሳራ 400 ሚ.ሊ ዘይት፣500ሚ.ሊ ውሀ እና 2000 ሚ.ሊ ወተት ገዛች በአጠቃላይ የገዛችው ስንት ሚሊ ሊትር ነው?

መፍትሔ 1 አጠቃላይ የተደራረበው ቁም ሳጥን ቁመት ለማግኘት የሁለቱን ቁመት መደመር ነው

ስለዚህ 45 ሳ.ሜ +32 ሳ.ሜ = 77 ሳ.ሜ ይሆናል ማለት ነው::

2.መጀመሪያ በኪሎ ግራም የተሰጠውን ወደ ግራም መቀየር

3 ኪ.ግ = 3×1000ግ = 3000ግ

3000ግ >2000ግ ስለዚህ አበበ ከባድ ፍራፍሬ ይዟል::

3. 400ሚ.ሊ+ 500 ሚ.ሊ+ 2000ሚ.ሊ = 2900 ሚ.ሊ

## መልመጃ ለ

1.የአለም ቤት ከትምህርት ቤት 5 ኪ.ሜ እርቀት ላይ ሲሆን የአለሙ ቤት ከትምህርት ቤት 7 ኪ.ሜ ይርቃል፡፡ከት/ቤት የማን ቤት ሩቅ ነው?በምንያክል ?

2.ከበደ 8ኪ.ግ ሩዝ ገዛ፣ ሜሮን ደግሞ 7 ኪ.ግ ሩዝ ገዛች፡፡ ከበደና ሜሮን በአጠቃላይ ምንያክል ኪ.ግ ሩዝ ገዙ?

3.አንድ ጠርሙስ 800 ሚሊ ሊትር ዘይት ይዟል፣ ጠርሙሱ ወድቆ 175 ሚሊ ሊትር ዘይት ፈሰሰ፤በጠርሙሱ ውስጥ ምንያክል ሚሊ ሊትር ዘይት ይቀራል?

4.አንድ ባልዲ 15 ሊትር ውሀ ሲይዝ ሌላ ባልዲ ደግሞ 9 ሊትር ይይዛል በሁለቱ ባልዲ ውስጥ ያለውን አጠቃላይ የውሀ መጠን ፈልጉ?

5.የሀና መጠነቁስ 36 ኪ.ግ እና የሮዛ መጠነቁስ 33 ኪ.ግ ነው፤የሁለቱ መጠነቁስ ሲደመር ስንት ነው?

6.አንድ ጥቅል ገመድ 827 ሜትር ርዝመት አለው 315 ገመድ ተቆርጦ ጥቅም ላይ ቢውል ምንያክልየገመድ ርዝመት ይቀራል?

## የምዕራፍ 10 ማጠቃለያ

➢ የርዝመት መለኪያ መደበኛ አሀድ

ሚሊሜትር፣ሴንቲ ሜትር፣ሜትር እና ኪሎ ሜትር ናቸው።

ርዝመቱ ወይም ርቀቱ ምንያክል ትልቅ ወይም ትንሽ እንደሆነ ለመወሰን እነዚህን መለኪያዎች እንጠቀማለን።

- በመጠነቁስ መለኪያ ምድቦች መካከል ያለ ዝምድና

  1000 ሚ.ግ =1 ግ፤ 1000 ግ= 1ኪ.ግ፤ 100 ኪ.ግ = 1 ኩንታል

- ሚዛን የአንድን እቃ መጠነቁስ ለመለካት የሚያገለግል መሳሪያ ነው
- አንድ የፈሳሽ መያዣ እቃ ሊይዝ የሚችለው ከፍተኛ የፈሳሽ መጠን የእቃው ይዘት ይባላል።
- ሚሊ ሊትር(ሚ.ሊ) አነስተኛ የፈሳሽ መጠንን ለመለካት የምንጠቀምበት የፈሳሽ መለኪያ ምድብ ነው።
- ሊትር(ሊ)ና ጋሎን ከፍተኛ የፈሳሽ መጠን ለመለካት የምንጠቀምበት ምድብ ነው።

## የምዕራፍ 10 ማጠቃለያ መልመጃ

1. የሚከተሉትን ምድቦች ቀይሩ::

   ሀ.32 ሜ ወደ ሳ.ሜ  ለ.9 ኪ.ግ ወደ ግ  ሐ. 4ሊ ወደ ሚ.ሊ

2. ባዶ ቦታውን በትክክለኛ ምልክት < ፣ > ወይም = ሙሉ::

   ሀ.1000 ግ ____1000ሚ.ግ  ለ.4ግ______4000ሚ.ግ

   ሐ.4ሜ______2000ሳ.ሜ

3. የሚከተሉትን ምድቦች ቀይሩ::

   ሀ.70ሜ ወደ ሳ.ሜ  ለ. 9ሜ ወደ ሳ.ሜ  ሐ.5 ኩንታል ወደ ኪ.ግ

4. የሚከተሉትን ሊትር ወደ ሚሊ ሊትር ቀይሩ::

   ሀ.5 ሊትር  ለ. 7ሊትር  ሐ.9 ሊትር  መ. 10 ሊትር

5. ድልድይ ለመስራት ሁለት የእጨት ጣውላዎች ባለ15ሜትር እና 20 ሜትር ርዝመት ያላቸው ቢቀጣጠሉ የድልድዩ ጠቅላላ ርዝመት ስንት ነው?

6. ከታች ባለው ስዕል መሰረት ከሀ እና ለ መጠነቁስ የትኛው ይበልጣል?



# ምዕራፍ 11 የኢትዮጵያ ገንዘብ

**የመማር ማስተማር ዉጤቶች ፣ ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፣**

- ኢትዮጵያ የተለያዩ የገንዘብ ኖቶች እንዳሏት ትረዳላችሁ፡፡
- አንድ የገንዘብ ኖት ምንዛሬ ወደ ሌላ የገንዘብ ኖት ምንዛሬ እንዴት መለወጥ (መቀየር) እንዳለባቸዉ ትረዳላችሁ፡፡
- የኢትዮጵያን ገንዘብ በእለት ተእለት ህይወታችሁ ትጠቀማላችሁ፡፡

መግቢያ ገንዘብ በእያንዳንዱ የህይወታችን ክፍል ስለሚያስፈልገን እንደሀገር በጥንቃቄና በጣም ብዙ የሀገር በጀት ወጥቶበት የሚታተም ስለሆነ ይህ በጣም ብዙ ወጭ የወጣበት የመገበያያ የብር ኖትና የሳንቲም ስንጠቀምና ስናስቀምጥ እንዳይጠፋና እንዳይቀደድ ልንጠነቀቅለት ይገባል ማለት ነው፡፡ በገንዘብ የተለያዩ ነገሮችንማለትም ልብስ፣ ምግብ፣ ቤት፣መኪና፣ መፅሀፍ፣ የቤት እቃዎችና ሌሎችንምየምንፈልጋቸውን እቃዎች እንገዛበታለን፡፡

ገንዘብ ማለት ሰዎች በመደራደርና በመግባባት እቃዎችን ወይም አገልግሎትን ለማግኘት የምንጠቀምባቸው የብሮች ወይም የሳንቲም ናቸው፡፡

## 11.1 የገንዘብ ምንዛሬ ምድብ መቀያየር

**የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት**

- ሣንቲሞችን መገንዘብ
- የሳንቲሞችን ጥቅም መረዳትና መገንዘብ
- የሳንቲሞችን ስብስብ ማወዳደር
- ለአንድ በተሰጠ የገንዘብ መጠን ተመሳሳይና የተለያዩ አይነት ሳንቲሞችን መፈለግ
- ለአንድ ለተሰጠ የገንዘብ መጠን ተመጣጣኝ ሳንቲሞችን መፈለግ
- የገንዘብ ምንዛሪ ማድረግ

**ተግባር ሀ**

1. ኢትዮጵያ በአሁኑ ሰዓት እየተጠቀመችባቸው ያሉትን የብር ኖቶች ዘርዝሩ፡፡
2. ኢትዮጵያ በአሁኑ ሰአት እየተጠቀመችባቸው ያሉትን ሳንቲሞች ዘርዝሩ፡፡
3. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በመሆን ስሩ

ሀ. አንድ የ10 ብር ኖት ስንት ባለ 5 ብር ኖት እና ባለ1 ብር ኖት ይሆናል?

ለ. ሁለት የ 50 ብር ኖት ስንት ባለ 10 ብር ኖት ይሆናል?

**ማስታወሻ**

እያንዳንዱ የብር ኖትና ሳንቲም ከላዩ ላይ በተፃፈው ቁጥር ልክ የዋጋ ተመን አለው፡፡

ኢትዮጵያ ከ 2012 ዓ.ም ጀምሮ እየተጠቀመችበት ያለው የብርና የሳንቲም አይነቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

### ሀ. የብር ኖት አይነቶች

አምስት ብር




አስር ብር




ሀምሳ ብር




አንድ መቶ ብር




ሁለት መቶ ብር




### ለ. ሳንቲሞች

አንድ ሳንቲም



ሀያአምስት ሳንቲም



አምስት ሳንቲም



ሀምሳ ሳንቲም



አስር ሳንቲም



የአንድ ብር ሳንቲም



ሀ. የብር ኖት ያላቸው ዝምድና

ማስታወሻ:- በብር ኖቶች መካከል ያለ ዝምድና

- 1ባለ 200 ብር ኖት = 2 ባለ 100 ብር ኖት
- 1ባለ 200 ብር ኖት = 4 ባለ 50 ብር ኖት
- 1ባለ 200 ብር ኖት = 20 ባለ 10 ብር ኖት
- 1 ባለ 100 ብር ኖት = 2 ባለ 50 ብር ኖት
- 1 ባለ 50 ብር ኖት = 5 ባለ 10 ብር ኖት

ምሳሌ ሀ

ሀ. ሁለት የ50 ብር ኖቶች ስንት ባለ 5 ብር ኖቶች ይመነዘራል?

ለ. አራት የ200 ብር ኖቶች ስንት ባለ 100 ብር ኖቶች ይመነዘራል?

ሐ. ሶስት የ 10 ብር ኖቶች ስንት ባለ 1 ብር ኖቶች ይመነዘራል?

መፍትሄ

ሀ. አንድ ባለ 50 ብር ኖት = 10 ባለ 5 ብር ኖት ስለሆነ

ሁለት የ50 ብር ኖት = 2× አንድ ባለ 50 ብርኖት= 2× 10 ባለ 5 ብር ኖት

= 20 ባለ 5 ብር ኖት

ለ. አንድ ባለ 200 ብር ኖት = 2 ባለ 100 ብር ኖት ስለሆነ

አራት የ200 ብር ኖት = 4× አንድ ባለ 200 ብርኖት= 4×2 ባለ 100 ብር ኖት

= 8 ባለ 100 ብር ኖት

ሐ. አንድ ባለ 10 ብር ኖት = 10 ባለ 1 ብር ኖት ስለሆነ

ሶስት የ10 ብር ኖት = 3× አንድ ባለ 10 ብር ኖት = 30 ባለ 1ብር ኖት

## መልመጃ ሀ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

ሀ. ስድስት የ100 ብር ኖቶች ስንት ባለ10 ብር ኖቶች ይመነዘራሉ?

ለ. አምስት የ10 ብር ኖቶች ስንት ባለ 5 ብር ኖቶች ይመነዘራሉ?

ሐ. ሁለት የ200 ብር ኖቶች ስንት ባለ 50 ብር ኖቶች ይመነዘራሉ?

ለ. ሳንቲሞች ያላቸው ዝምድና

### ተግባር ለ

ሀ. አንድ ባለ 50 ሳንቲም ስንት ባለ 10 ሳንቲም ይሆናል?

ለ. ሶስት ባለ 25 ሳንቲም ስንት ባለ 5 ሳንቲም ይሆናል?

ማስታወሻ ፡- ሳንቲሞች ያላቸው ዝምድና

- 1ባለ 1ብር = 2 ባለ 50 ሳንቲም
- 1ባለ 50 ሳንቲም = 2 ባለ 25 ሳንቲም
- 1 ባለ 50 ሳንቲም = 5 ባለ 10 ሳንቲም
- 1ባለ 10 ሳንቲም = 2 ባለ 5 ሳንቲም
- 1ባለ 5 ሳንቲም = 5 ባለ 1 ሳንቲም

<u>ምሳሌ ለ</u>

ሀ. አምስት ባለ 50 ሳንቲም ስንት ባለ 25 ሳንቲም ነው?

ለ. አስር ባለ 5 ሳንቲም ስንት ባለ 1 ሳንቲም ነው?

መፍትሄ

ሀ. 1 ባለ 50 ሳንቲም = 2 ባለ 25 ሳንቲም ስለሆነ

አምስት ባለ 50 ሳንቲም = 5× 1 ባለ 50 ሳንቲም

= 5 × 2 ባለ 25 ሳንቲም = 10 ባለ 25 ሳንቲም

ለ. አንድ ባለ 5 ሳንቲም = አምስት ባለ 1 ሳንቲም

አስር ባለ 5 ሳንቲም = 10 × 1 ባለ 5 ሳንቲም

= 10 ×5 ባለ 1 ሳንቲም= 50 ባለ 1 ሳንቲም

## መልመጃ ለ

1. የሚከተሉትን የምንዛሪ ጥያቄዎች መልሱ፡፡

ሀ. ሁለት ባለ 50 ሳንቲም ________ ባለ 5 ሳንቲም ይዟል

ለ. ሶስት ባለ 25 ሳንቲም ________ ባለ 5 ሳንቲም ይዟል

ሐ. ዘጠኝ ባለ 10 ሳንቲም ________ ባለ 1 ሳንቲም ይዟል

ሐ. የብር ኖት ከሳንቲሞች ጋር ያለው ዝምድና

**ተግባር ሐ**

1. የሚከተሉትን ምንዛሬዎች አስሉ፡፡

ሀ. አንድ ባለ 5 ብር ኖት ስንት ባለ 50 ሳንቲም ይሆናል?

ለ. አንድ ባለ 50 ብር ኖት ስንት ባለ 50 ሳንቲም ይሆናል?

ማስታወሻ:- የብር ኖት ከ ሳንቲሞችጋር ያለው ዝምድና

- አንድ ባለ 200 ብር ኖት = አራት መቶ ባለ 50 ሳንቲም
- አንድ ባለ 100 ብር ኖት = ሁለት መቶ ባለ 50 ሳንቲም
- አንድ ባለ 50 ብር ኖት = መቶ ባለ 50 ሳንቲም
- አንድ ባለ 10 ብር ኖት = አርባ ባለ 25 ሳንቲም
- አንድ ባለ 5 ብር ኖት = ሀምሳ ባለ 10 ሳንቲም

ምሳሌ ሐ

1. የሚከተሉትን ምንዛሪዎች አስሉ፡፡

ሀ. አስር ባለ 5 ብር ኖት ስንት ባለ 50 ሳንቲም ይሆናል?

ለ. ሁለት ባለ 100 ብር ኖት ስንት ባለ 25 ሳንቲም ይሆናል?

ሐ. በ 150 ብር ውስጥ ስንት ባለ 50 ሳንቲም ይኖራሉ?

መፍትሄ

ሀ. አንድ ባለ 5 ብር = 10 ባለ 50 ሳንቲም ስለሆነ

አስር ባለ 5 ብር ኖት = 10 × አንድ ባለ 5 ብር ኖት

= 10 × 10 ባለ 50 ሳንቲም = 100 ባለ 50 ሳንቲም

ለ. አንድ ባለ 100 ብር ኖት = 400 ባለ 25 ሳንቲም ስለሆነ

ሁለት ባለ 100 ብር ኖት = 2 × አንድ ባለ 100 ብር ኖት

=2 × 400 ባለ 25 ሳንቲም = 800 ባለ 25 ሳንቲም

ሐ. አንድ ብር = 2 ባለ 50 ሳንቲም ስለሆነ

150 በር = 150×2 ባለ 50 ሳንቲም = 300 ባለ 50 ሳንቲም

## መልመጃ ሐ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::

   ሀ. 320 ብር ስንት ባለ 10 ሳንቲም ይዟል?

   ለ. አርባ ባለ 25 ሳንቲም ስንት ባለ 5 ብር ኖት ይዟል?

   ሐ. ስልሳ ባለ 50 ሳንቲም ስንት ባለ 10 ብር ኖት ይዟል?

## 11.2 ገንዘብን ማወዳደር

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት

- ገንዘብን ማወዳደር
- የገንዘብ ፅንሰ ሀሳብ ያላቸውን የቃላት ፕሮብሌሞች መፍታት
- ገንዘቦችን መቁጠር እና ማወዳደር

### ተግባር መ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በመሆን ስሩ::

ሀ. በየሳጥኑ ያሉትን የብር መጠኖች ፃፍ:: በመቀጠል ደግሞ 〈፣〉 ወይም= ምልክቶችን በመጠቀም አወዳድሩ::



ለ. የአንድ ጥንድ ነጠላ ጫማ ዋጋ 360 ብር ቢሆን ሁለት ባለ አንድ መቶ እና አንድ ባለ ሁለት መቶ ብር ጫማውን ለመግዛት በቂ ነው? የጫማው ዋጋ ወይስ ብሩ ይበልጣሉ አወዳድሩ::

ምሳሌ ሀ

1. ሀ. በየሳጥኑ ያሉትን የብር መጠኖች ፃፍ:: በመቀጠል ደግሞ 〈 ፣ 〉 ወይም= ምልክቶችን በመጠቀም አወዳድሩ::



ለ.



2. ሚኪያስ ጆሮ ላይ የሚደረግ ማዳመጫ በ200 ብርና የሙዚቃ ማጫወቻ ቴፕ በ800 ብር ቢገዛ ጠቅላላ ሁለቱን እቃዎች በስንት ብር ገዛቸው?

3. ሀያት 2 ኪሎ ግራም ሸንኩርት በ40 ብር ገዝታ ሸንኩርት ለገዛችው ነጋዴ 100 ብር ብትሰጠው ነጋዴው ለሀያት ስንት ብር መመለስ አለበት?

4. ትግስት ሁለት ተመሳሳይ ዋጋ ያላቸው የመኪና አሻንጉሊቶች በ100 ብር ብትገዛ የአንዱ አሻንጉሊት ዋጋ ስንት ነው?

መፍትሄ

1. ሀ. 55 እና 30 ብሮች ናቸው:: ስለዚህ 55>30

ለ.210 እና 211 ብሮች ናቸው ::ስለዚህ 210<211

2. ጆሮ ላይ የሚደረግ ማዳመጫ ዋጋ= 200 ብር

የሙዚቃ ማጫወቻ ቴፕ ዋጋ = 800 ብር

ጠቅላላ የሁለቱ እቃዎች ዋጋ = ማዳመጫ ዋጋ+ ቴፕ ዋጋ

= 200 ብር + 800 ብር = 1000 ብር

3. ሀያት ለሸንኩርትያወጣችው = 40 ብር

ሀያት ለነጋዴ የሰጠችው =100 ብር

100 ብር - 40 ብር = 60 ብር ይመልስላታል

4. የሁለት አሻንጉሊቶች ዋጋ = 300 ብር

የአንድ አሻንጉሊት ዋጋ = የሁለት አሻንጉሊቶች ዋጋ ÷ 2 =100 ÷2= 50 ብር

## መልመጃ መ

ሀ. የሚከተሉትን የቃላት ፕሮብሌሞች ስሩ

1. የአንድ ፓኬት ብስኩት ዋጋ 12 ብር ቢሆን የ4 ፓኬት ብስኩቶች ዋጋ ስንት ነው

2. ጀሚላ በ600 ብር ዶሮ፣ በ 400 ብር ቅቤና በ50 ብር ዳቦ ብትገዛ ለዶሮ፣ ለቅቤና ለዳቦ በጠቅላላ ያወጣችው የብር መጠን ስንት ነው?

3. የ1ኪሎ ግራም ባቄላ ዋጋ 120 ብር ቢሆን አስካለ 6 ኪሎ ግራም ባቄላ ለመግዛት ስንት ብር ያስፈልጋታል?

4. አለም አራት ተመሳሳይ ዋጋ ያላቸው ብርጭቆዎች በ 80 ብር ብትገዛ የእያንዳንዱ ብርጭቆ ዋጋ ስንት ነው?

## የምዕራፍ 11 ማጠቃለያ

- እያንዳንዱ የብር ኖትና ሳንቲም ከላዩ ላይ በተፃፈው ቁጥር ልክ የዋጋ ተመን አለው።
- በብር ኖትና መካከል ያለ ዝምድና

  1ባለ 200 ብር ኖት = 2 ባለ 100 ብር ኖት

  1ባለ 200 ብር ኖት = 4 ባለ 50 ብር ኖት

  1 ባለ 100 ብር ኖት = 2 ባለ 50 ብር ኖት

  1 ባለ 50 ብር ኖት = 5 ባለ 10 ብር ኖት

  1 ባለ 10 ብር ኖት = 10 ባለ 1 ብር ኖት
- የተለያዩ ሳንቲሞች ያላቸው ዝምድና

  1ባለ 1ብር = 2 ባለ 50 ሳንቲም

  1 ባለ 50 ሳንቲም = 5 ባለ 10 ሳንቲም

  1ባለ 10 ሳንቲም = 2 ባለ 5 ሳንቲም

  1ባለ 5 ሳንቲም = 5 ባለ 1 ሳንቲም
- የቃላት ፕሮብሌሞችን ለመስራት የቃላት ፕሮብሌሙን ማንበብና መገንዘብ፤ ፕሮብሌሙን ወደ ቁጥር መቀየር፤ የቁጥር ጥያቄውን ማስላትና ያገኘነውን መልስ ከፕሮብሌሙ ጋር ማመሳከር።

## የምዕራፍ 11 ማጠቃለያ መልመጃ

1. የሚከተሉትን ምንዛሪዎች አስሉ፡፡

   ሀ. ሁለት ባለ 50 ብር ኖት ስንት ባለ 50 ሳንቲም ይሆናል?

   ለ. ስድስት ባለ 10 ብር ኖት ስንት ባለ 25 ሳንቲም ይሆናል?

   ሐ. በ 250 ብር ውስጥ ስንት ባለ 10 ሳንቲሞች ይኖራሉ?

2. አንድ ካፌ የሚሸጠው የትልቁ ፒዛ ዋጋ 150 ብር ሲሆን የትንሹ ፒዛ ዋጋ 110 ብር ነው፡፡ በትልቁና በትንሹ ፒዛ ዋጋ መካከል ያለው ልዩነት ስንት ነው?

3. የአንድ ደናት ዋጋ 25 ብር ቢሆን የ5 ደናት ዋጋ ስንት ይሆናል?

4. የአንድ ጠርሙሶች ለስላሳ መጠጥ ዋጋ 15 ብር ቢሆን የ20 ጠርሙስ ለስላሳ መጠጥ ዋጋ ስንት ይሆናል?

5. የአንድ ሲኒ ቡና ዋጋ 8 ብር ቢሆን የ30 ሲኒ ቡና ዋጋ ስንት ይሆናል?

6. አቶ ሰይድ 100 ብር እኩል ለ5 ልጆቹ ቢያካፍላቸው እያንዳንዳቸው ስንት ብር ይደርሳቸዋል?

7. የ1ኪሎ ግራም ቲማቲም ዋጋ 20 ብር ቢሆን የ8 ኪሎ ግራም ቲማቲም ዋጋ ስንት ይሆናል?

# ምዕራፍ 12 የኢትዮጵያ ጊዜ

የመማር ማስተማር ዉጤቶች፣ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፣

- የኢትዮጵያ የጊዜ (የሠዓት) አቆጣጠር ማንበብ ትራዳላችሁ ::
- አንድ የጊዜ ምድብ ወደ ሌላ የጊዜ ምድብ መለወጥ ትችላላችሁ።
- የኢትየጵያ ጊዜን መሰረት ያደረገ ተግባራዊ ፕሮብሌሞች ትተገብራላችሁ።

**መግቢያ**

ሰዓት ጊዜን ለመጠቆም፣ለመቁጠር፣ ለመለካት እና ከጊዜ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለማከናወን የምንጠቀምበት መሳሪያ ነው:: ይህ መሳሪያ ከሠው ልጆች ግኝቶች ሁሉ ቀደምቱ ሲሆን ከቀን ያነሰ የጊዜ አሀድ በማስፈለጉ የተጀመረ ነው::

## 12.1 ሰዓቶችን ማንበብ

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት

- የሰዓትና የደቂቃ አመልካቾችን መለየት

**ተግባር ሀ**

1. ተማሪዎች ወደ ት/ቤት መሄጃና ከት/ቤት መውጫ ጊዜያችሁን መድረሱን በምን ማወቅ ትችላላችሁ?

ማስታወሻ:- ሰዓትን ስናነብ በብዛት ሁለት አይነት ሰዓቶችን እናገኛለን::እነሱም ዲጅታል ሰዓትና አናሎግ(የሚዞር) ሰዓት ናቸው::

ሀ. ዲጅታል ሰዓት

ማስታወሻ

- ዲጅታል ሰዓት ምንም አይነት ቆጣሪ ዘንግ የሌለው ሲሆን ሰዓትን ቀጥታ በቁጥር ይገልፃል፡፡
- ዲጅታል ሰዓት ላይ ሰዓት አመልካች ቁጥርና ደቂቃ አመልካች ቁጥር ሲኖሩ በሁለቱ ቁጥሮች መካከል ሁለት ነጥቦች (:) ያሉ ሲሆን በነጥቡ በግራ በኩል ያለው ቁጥር ሰዓቱን ሲገልጽ በቀኝ በኩል ያለው ቁጥር ደግሞ ደቂቃውን ይገልፃል፡፡

ምሳሌ ሀ




ሲነበብ ስድስት ሰዓት ከ ሰላሳ ደቂቃ ይባላል

ምሳሌ ለ




ሲነበብ ስምንት ሰዓት ከሃምሳ ሁለት ደቂቃ ይባላል

ለ. አናሎግ(የሚዞር) ሰዓት

ማስታወሻ

- አናሎግ ሰዓት አንዱ የሰዓት አይነት ሲሆን የፊት ለፊት ገፁ ላይ ከ1 እስከ 12 ያሉ ቁጥሮች በእኩል እርቀት ላይ ዙሪያውን የተቀመጡ ሲሆን በእያንዳንዱ ተከታታይ ቁጥሮች መካከል የ5 ደቂቃ ልዩነት ሲኖር አጠቃላይ በውስጡ 60 ደቂቃ ይዟል፡፡ በተጨማሪም በውስጡ የሚሽከረከሩ ዘንጎች ያሉት ሲሆን አጭሩና ወፍራሙ ዘንግ ሰዓት አመልካች ዘንግ ሲሆን ረዘምና ቀጠን ያለው ደግሞ ደቂቃ አመልካች ዘንግ ነው፡፡



*አናሎግ ሰአት ስናነብ መከተል ያለብን መንገዶች*

1. የሰአት ቆጣሪ ዘንጉ ጫፍ የሚያመለክትበትን ቁጥር በማየት ሰዓቱን ማንበብ
   - የሰዓት ቆጣሪ ዘንጉ ጫፍ ቁጥር ላይ ካረፈ ያረፈበትን ቁጥር መፃፍ
   - የሰዓት ዘንጉ ጫፍ በቁጥር መካከል ካረፈ ሰዓቱ ትንሹ ቁጥር ይሆናል
2. የደቂቃ ቆጣሪ ዘንጉ ጫፍ የሚያመለክትበትን ቁጥር በማየት ደቂቃውን ማንበብ
   - የደቂቃ ቆጣሪ ዘንጉ ጫፍ ቁጥር ላይ ካረፈ ያረፈበትን ቁጥር በ5 በማባዛት ደቂቃው ስንት እንደሆነ ማወቅ
   - የደቂቃ ቆጣሪ ዘንጉ ጫፍ በቁጥር መሃል ካረፈ ትንሹን ቁጥር በመውሰድ በ5 ማባዛትና ውጤቱን ትንሹ ቁጥር ካለበት እስከ ደቂቃ ቆጣሪ ዘንጉ ያሉትን ቀጫጭን መስመሮች በመቁጠር ካገኘነው ውጤት ላይ በመደመር ደቂቃውን ማግኘት፡፡
3. በተራ ቁጥር 1እና2 ያነበብነውን አንድ ላይ በማድረግ መፃፍ፡፡



አስታውሱ

አናሎግ ሰዓት በውስጡ የሚሽከረከሩ ዘንጎች ያሉት ሲሆን የሚሽከረከሩበት አቅጣጫም በስዕሉ ላይ እንደሚታየው ነው፡፡

<u>ምሳሌ ሀ</u> የሰዓት ቆጣሪ ዘንጉ ጫፍ




የሚያመለክትበት ቁጥር 10 ስለሆነ ሰዓቱ 10 ሲሆን የደቂቃ ቆጣሪ ዘንጉ ጫፍ የሚያመለክትበትን ቁጥር 2 ስለሆን ደቂቃው 2×5 = 10 ደቂቃ ይሆናል፡፡

ስለዚህ ሲነበብ 10 ሰዓት ከ 10 ደቂቃ ይሆናል ማለት ነው፡፡




ምሳሌ ለ:- የሰዓት ቆጣሪ ዘንጉ ጫፍ

የሚያመለክትበት ቁጥር በ2 እና በ3 ሲሆን

ትንሹ ቁጥር 2 ስለሆነ ሰዓቱ 2 ሲሆን

የደቂቃ ቆጣሪ ዘንጉ ጫፍ በ4 እና በ5

መካከል ስለሆነ ትንሹን ቁጥር 4 በመውሰድ 5×4 = 20 ደቂቃ

ከ4 ቁጥር ካለበት እስከ ደቂቃ ቆጣሪ ዘንጉ ያሉት ቀጫጭን መስመሮች 2 ደቂቃ ያሳያል::

ስለዚህ 20 ደቂቃ + 2ደቂቃ = 22 ደቂቃ ይሆናል

ስለዚህ ከላይ ያለው ሰዓት ሲነበብ 2 ሰዓት ከ22 ደቂቃ ይሆናል::

አስተውሉ:- በ2ኛ ክፍል እንደተማራችሁት 15 ደቂቃን ሩብ ሰዓት ብለን ስንጠራው 30 ደቂቃን ደግሞ ግማሽ ሰዓት የምንለው ሲሆን 45 ደቂቃን ሩብ ጉዳይ በማለት እንጠራለን:: ለምሳሌ 1:15 ሲነበብ አንድ ሰዓት ከሩብ ይባላል፣ 3:30 ሲነበብ 3 ሰዓት ተኩል ይባላል ፣ 4:45 ሲነበብ ለ5 ሩብ ጉዳይ ይባላል::

**መልመጃ ሀ**

1. የሚከተሉትን ሰዓቶች ካነበባችሁ በኋላ ያነበባችሁትን ፃፉ::

ሀ.




ለ.




## 12.2 ሰዓትና ደቂቃዎች

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት

- ሰዓቶችን ወደ ደቂቃ መቀየር

**ተግባር ለ**

1. 1ሰዓት ከ40 ደቂቃ ስንት ደቂቃ ይሆናል?
2. 4 ሰዓት ስንት ደቂቃ ይሆናል?
3. 95 ደቂቃ ስንት ሰዓት ከስንት ደቂቃ ይሆናል?

ማስታወሻ:- 1 ሰዓት = 60 ደቂቃ ሲሆን ሰዓትን ወደ ደቂቃ ለመቀየር የተሰጠውን ሰዓት በ60 ማባዛት ነው

ምሳሌ ሀ. 3 ሰዓት = 3×60 ደቂቃ =180 ደቂቃ ይሆናል

ለ. 7 ሰዓት = 7×60 ደቂቃ = 420 ደቂቃ ይሆናል

ሐ. 4 ሰዓት ከ10 ደቂቃ = 4×60 ደቂቃ + 10 ደቂቃ

= 240 ደቂቃ + 10 ደቂቃ = 250 ደቂቃ

መ. 300 ደቂቃ = 60 ደቂቃ + 60 ደቂቃ +60 ደቂቃ +60 ደቂቃ +60 ደቂቃ

= 1ሰዓት + 1ሰዓት + 1ሰዓት + 1ሰዓት + 1ሰዓት

= 5 ሰዓት

ሠ. 210 ደቂቃ = 60 ደቂቃ + 60 ደቂቃ +60 ደቂቃ + 30 ደቂቃ

= 1 ሰዓት + 1 ሰዓት + 1 ሰዓት + 30 ደቂቃ

= 3 ሰዓት ከ 30 ደቂቃ

**አስተውሉ**

የተሰጠን ደቂቃ ከ60 ደቂቃ ካነሰ በደቂቃው ይቀመጣል:: ከ60 ደቂቃ ከበለጠ በ60 ደቂቃ በመመደብ እያንዳንዱን 60 ደቂቃ 1 ሰዓት በማድረግ ወደ ሰዓት መቀየር::

## መልመጃ ለ

1. የሚከተሉትን ጥያቂቃዎች በምሳሌው መሰረት መልሱ፡፡

ሀ. 75 ደቂቃ = __1____ ሰዓት + ___15____ ደቂቃ

ለ. 195 ደቂቃ = _______ ሰዓት + ________ ደቂቃ

ሐ. 175 ደቂቃ = _______ ሰዓት + ________ ደቂቃ

መ. 320 ደቂቃ = _______ ሰዓት + ________ ደቂቃ

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ወደ ደቂቃ ለውጡ፡፡

ሀ. 2 ሰዓት =____ደቂቃ   ለ. 6 ሰዓት =____ደቂቃ   ሐ. 10 ሰዓት = ____ደቂቃ

### 12.3 ቀናት፣ ሳምንታት፣ ወራትና ዓመታት

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት

- አመታትን ወደ ወራት፣ ሳምንታት እና ቀናት መቀየር

ተግባር ሐ

1. ተማሪዎች እድሜያችሁን በወርና በቀን በመቀየር ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

ማስታወሻ

- 1 ቀን = 24 ሰዓት
- 1ሳምንት = 7 ቀን
- 1ወር = 30 ቀን ጳጉሜን ሳይጨምር ምክንያቱም ጳጉሜ በውስጧ 5 ቀን ሲኖራ በ4 ዓመት አንዴ 6 ቀን ትሆናለች
- 1 ዓመት =365 ቀን ሲሆን በ4 ዓመት አንዴ 366ቀን ይሆናል

ምሳሌ ሀ

1. 5 ቀናት ስንት ሰዓት ይሆናል?

   5 ቀናት = 5×24 ሰዓት = 120 ሰዓት ምክንያቱም 1ቀን = 24 ሰዓት

2. 10 ሳምንታት ስንት ቀናት ይሆናል?

   10 ሳምንታት = 10 × 7 ቀን = 70 ቀን ምክንያቱም 1ሳምንት = 7ቀን

3. 6 ወር ስንት ቀናት ይሆናል?

   6 ወር = 6 × 30 ቀን = 180 ቀን ምክንያቱም 1ወር = 30 ቀን

4. 42 ቀናት ስንት ሳምንታት ይሆናል?

   42 ቀናት = 7 ቀን + 7 ቀን + 7 ቀን + 7 ቀን + 7 ቀን + 7 ቀን

   = 1ሳምንት+1ሳምንት+1ሳምንት+1ሳምንት+1ሳምንት+1ሳምንት

   = 6 ሳምንት

## መልመጃ ሐ

1. የሚከተሉትን ሳምንታት ወደ ቀናት ለውጡ፡፡

   ሀ. 11 ሳምንት ለ. 15 ሳምንት ሐ. 3 ወር መ. 9 ወር

2. የሚከተሉትን ቀናት ወደ ሳምንታት ለውጡ፡፡

   ሀ. 98 ቀን ለ. 189 ቀን ሐ. 7 ቀን

## 12.4 የኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር

የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት

- የኢትየጵያ የዘመን አቆጣጠርን መለየት

ተግባር መ

1. በቡድን በመሆን የኢትዮጵያን የዘመን አቆጣጠር ስንት ወር እንዳለውና የወሮች ስም እነማን እንደሆኑ ዘርዝሩ፡፡

ማስታወሻ

- የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር 13 ወራት ሲኖሩት ከእነዚህ ውስጥ አስራ ሁለቱ ወራት እያንዳንዳቸው 30 ቀናቶች ሲኖራቸው አንዱ ወር ማለትም ጳጉሜ በውስጡ 5 ወይም 6 ቀናቶች ይዟል፡፡
- ጳጉሜ የወር ስም ሆኖ በነሐሴ እና በመስከረም ወራት መካከል የሚገኝ ከአስራ ሦስቱ የኢትዮጵያ ወራት አቆጣጠር ውስጥ የመጨረሻውና የአስራ ሦስተኛው ወር ስም ነው፡፡
- የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት መስከረም 1 ይጀምራል፡፡
- በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በሳምንት 7 እለታት ሲኖሩ እነሱም ሰኞ፣ ማክሰኞ፣ ረቡዕ፣ ሀሙስ፣ ዓርብ፣ ቅዳሜና እሁድ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ወራቶች

| | 1ኛው | 2ኛው | 3ኛው | 4ኛው | 5ኛው | 6ኛው | 7ኛው |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ወር | መስከረም | ጥቅምት | ህዳር | ታህሳስ | ጥር | ይካቲት | መጋቢት |

| | 8ኛው | 9ኛው | 10ኛው | 11ኛው | 12ኛው | 13ኛው |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ወር | ሚያዚያ | ግንቦት | ሰኔ | ሀምሌ | ነሃሴ | ጳጉሜ |

### ተግባር ሠ

የሚከተለውን የዘመን መቁጠሪያ በመጠቀም ጥያቄዎችን መልሱ።

የመስከረም 2015 ዓ.ም የዘመን መቁጠሪያ

| ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | አርብ | ቅዳሜ | እሁድ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1 |
| 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 |
| 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 |
| 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 |
| 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 | 29 |
| 30 | | | | | | |

1 እንቁጣጣሽ

17 የመስቀል በአል

27 የመውሊድ በአል

ሀ. እንቁጣጣሽ 2015 ዓ.ም በምን እለት እንደሚውል ፃፉ?

ለ. በ2015 ዓ.ም የመውሊድ በዓል በምን እለት እና ቀን እንደሚውል አመልክቱ?

ሐ. በተለየ የቀለሙት ቀናት ምን ያመለክታሉ?

መ. 13/01/2015 ዓ.ም በምን እለት እንደሚውል አመልክቱ?

### ማስታወሻ

- የዘመን መቁጠሪያ ያለፈውን እንዲሁም ገና የሚመጣውን ማንኛውንም ቀን ማንበብ የምንችልበት የዘመን መቁጠሪያ ነው።
- ዘመን መቁጠሪያ በመጠቀም ቀን ለመፈለግ ወይም ለማመልከት በመጀመሪያ ዓመት ምህረቱን መፈለግ በመቀጠል ወሩን ከመስከረም እስከ ጳጉሜ ካሉት መምረጥ እና ቀኑን በማየት ወደ ላይ በመሄድ ከሰኞ እስከ እሁድ ካሉት በየትኛው እለት እንደሚውል ማወቅ ይቻላል።

**ምሳሌ ሀ**

የየካቲት 2013 ዓ.ም የወሩ ቀናትን የሚገልፅ የዘመን መቁጠሪያ በመመልከት ከታች ያሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

| ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | አርብ | ቅዳሜ | እሁድ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 |
| 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 |
| 22 | 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 |
| 29 | 30 | | | | | |

23
አድዋ በአል

ሀ .የካቲት 11 ምን እለት እንደሚውል የዘመን መቁጠሪያው ላይ አመልኩቱ?

ለ.የካቲት 23 ምን እለት እንደዋለ ከዘመን መቁጥሪያው ፃፉ::

ሐ. በየካቲት ወር ውስጥ ስንት ሰኞዎች ነበሩ?

መ. በየካቲት ወር ውስጥ ስንት ሐሙሶች ነበሩ?

መፍትሔ

| ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | አርብ | ቅዳሜ | እሁድ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 |
| 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 |
| 22 | 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 |
| 29 | 30 | | | | | |

ሀ. የካቲት 11 እንደምትመለከቱት ሐሙስ እለት ይውላል

ለ. የካቲት 23 እንደምት መለከቱት ማክሰኞ እለት ይውላል:: የተለየ መደብ ያለው ቀን የበዓላት ቀናቶች ናቸው:: የሃይማኖት ወይም ሀገራዊ በአላት ሊሆኑ ይችላሉ::

የካቲት 23 የአድዋ በአል ነው:: የአድዋ በአል ማለት ጣሊያን በ 1888 ዓ.ም ዘመን አቆጣጠር ኢትዮጵያን ለመውረር በመጣች ጊዜ የኢትዮጵያ ህዝብ የጣሊይንን የሰለጠነ ወታደር አልገዛም በማለት በወኔ በአንድነት የኢጣሊያን ጦር አድዋ ተራራ ላይ ድል ያደረገኝበት ቀን ነው::

ሐ. በ1፣ በ8፣ በ15፣ በ22 እና በ29 ሰኞ እለት እንደነበረ ነው የሚያሳየው።

መ. በ4 ፣ በ11 ፣ በ18 እና በ25 ሐሙስ እለት እንደነበረ ነው የሚያሳየው።

ሠ. አሁን ያለው ዓመት ምህረት ሲቀነስ 1888 ዓ.ም

## መልመጃ መ

1. ኢትዮጵያ ስንት ወራቶች አሏት?

2. የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት የሚጀምረው በየትኛው ወር ነው?

3. ጳጉሜ የሚገኘው በ____ እና በ _____ ወሮች መካከል ነው፡፡

4.

የየካቲት 2020 ዓ.ም

| ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | አርብ | ቅዳሜ | እሁድ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 |
| 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 |
| 20 | 21 | 22 | 23 | 24 | 25 | 26 |
| 27 | 28 | 29 | 30 | | | |

23 = የአድዋ በአል

18 = ኢድ ዓል ፈጥር

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከላይ ባለው የዘመን መቁጠሪያ መሰረት መልሱ።

ሀ. በ2020 ዓ.ም የካቲት 20 በምን ዕለት እንደሚውል ፃፉ?

ለ. 08/02/2020 ዓ.ም የሚውልበትን ዕለት ፃፉ?

ሐ.2020 ዓ.ም የአድዋ በአል የሚውልበትን ዕለት ፃፉ?

## ጊዜን መሰረት ያደረጉ የቃላት ፕሮብሌሞች

**ተግባር ረ**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በመሆን ስሩ፡፡

1. በቀን ምን ያህል ሰዓት ትጫወታላችሁ?
2. ከቤታችሁ ተነስታችሁ ት/ቤት ለመደረስ ስንት ሰዓት ይወስዳል?
3. በሳምንት ስንት ቀናቶች ወደ ት/ቤት ትሄዳላችሁ?

<u>ምሳሌ ሀ</u>

1. ዘነበና ቢላል በተመሳሳይ አመት የተወለዱ ሲሆን ዘነበ ጥር 2 ሲወለድ ቢላል ደግሞ ጥር 28 ቢወለድ ከቢላልና ከዘነበ በዕድሜ የሚበልጠው ማን ነው?የቢላልና የዘነበ እድሜ ልዩነት ስንት ቀን ነው?
2. ፀገነት ሶስት ሰዓት ከ30 ብትጀምርና አራት ሰዓት ከሰላሳ ብትጨርስ የቤት ስራዋን ለመጨረስ ስንት ሰዓት ወሰደባት?
3. ታምራት ከመተኛቱ በፊት ከሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት ተኩል ፊልም ቢያይ ፊልሙን ለማየት የወሰደው ጊዜ ስንት ሰዓት ነው?

   **መፍትሔ**

   1. ቀድሞ የተወለደው በእድሜ ትልቅ ስለሆነ ዘነበ በእድሜ ትልቁ ነው፡፡
      28 -2 = 26 ስለዚህ የእድሚያቸው ልዩነት 26 ቀናቶች ናቸው፡፡
   2. 4 ሰዓት ከ30 ደቂቃ - 3 ሰዓት ከ30 ደቂቃ

      =(4×60 + 30)ደቂቃ -(3×60 +30)ደቂቃ

= 270 ደቂቃ - 210 ደቂቃ

= 60 ደቂቃ = 1ሰዓት

3. (3×60 + 30)ደቂቃ -(2×60 )ደቂቃ

= 210 ደቂቃ - 120 ደቂቃ

= 90 ደቂቃ

= 60 ደቂቃ+30 ደቂቃ

= 1ሰዓት ከ 30 ደቂቃ

## መልመጃ ሠ

1. ሶፊያ የአትክልት ስፍራውን ለመኮትኮት 3 ሰዓት የሚወስድባት ቢሆንና አትክልቱን መኮትኮት የጀመረችው ከጥዋቱ 1 ሰዓት ላይ ቢሆን ስንት ሰዓት ላይ አትክልቱን ኮትኩታ ትጨርሳለች?
2. ሳራ በኤሌክትሪክ ምድጃ ውሀ ለማፍላት 30 ደቂቃ ይወስድባታል፡፡ ጠዋት ሁለት ተኩል ላይ ውሀውን አፍልታ የኤሌክትሪክ ምድጃውን ብታጠፋ ሳራ ስንት ሰዓት ላይ ነበር የኤሌክትሪክ ምድጃውን የለኮሰችው?

## የምዕራፍ 12 ማጠቃለያ

- ዲጅታል ሰዓት ምንም አይነት ቆጣሪ ዘንግ የሌለው ሲሆን ሰዓትን ቀጥታ በቁጥር ይገልፃል።
- ዲጅታል ሰዓት ላይ ሰዓት አመልካች ቁጥርና ደቂቃ አመልካች ቁጥር ሲኖሩ በሁለቱ ቁጥሮች መካከል ሁለት ነጥቦች (:) ያሉ ሲሆን በነጥቡ በግራ በኩል ያለው ቁጥር ሰዓቱን ሲገልጽ በቀኝ በኩል ያለው ቁጥር ደቂቃን ይገልፃል።
- አናሎግ ሰዓት አንዱ የሰዓት አይነት ሲሆን የፊት ለፊት ገፁ ላይ ከ1 እስከ 12 ያሉ ቁጥሮች በእኩል ርቀት ላይ ዙሪያውን የተቀመጡ ሲሆን በእያንዳንዱ ተከታታይ ቁጥሮች መካከል የ5 ደቂቃ ልዩነት ሲኖር አጠቃላይ በውስጡ 60 ደቂቃ ይዟል። በተጨማሪም በውስጡ የሚሽከረከሩ ዘንጎች ያሉት ሲሆን አጭሩና ወፍራሙ ዘንግ ሰዓት አመልካች ዘንግ ሲሆን እረዘምና ቀጠን ያለው ደቂቃ አመልካች ዘንግ ነው።

## የምዕራፍ 12 የማጠቃለያ መልመጃ

1. የሚከተሉትን ሰዓቶች ካነበባችሁ በኋላ ያነበባችሁትን ፃፉ፡፡

ሀ 


ለ. 


2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዶ ቦታዎች ሙሉ፡፡

   ሀ. 135 ደቂቃ = ______ ሰዓት + _______ ደቂቃ

   ለ. 330 ደቂቃ = ______ ሰዓት + _______ ደቂቃ

   ሐ. 8 ሰዓት = ______ደቂቃ

   መ. 12 ሰዓት = ______ደቂቃ

3. የኢትዮጵያን ቀናቶችና ወራቶችን ዘርዝሩ፡፡
4. ግርማ አንድ ረድፍ ችግኝ ለመትከል ሁለት ሰዓት ቢወስድበት አራት ረድፍ ችግኝ ለመትከል ስንት ሰዓት ይወስድበታል?